# ከፈንጂ፣ ከሚፈነዱ ጦር መሣሪያዎችና ከተራ የሚፈነዱ ዕቃዎች አደጋ መከላከያ መጽሐፍ



UNMAS

ይህን መጽሐፍ በመጠቀም ሊከሰት ለሚችል ማንኛወም አይነት የሞት፣ የአካል መጉደልና/ወይም የንብረት ጉዳት የተባበሩት መንግስታትም ሆነ ሌሎች ተባባሪ ድርጅቶች ኃላፊነቱን አይወስዱም።

ይህን መጽሐፍ በሚመለከት ማናኛውም ጥያቄ ወይም እስተያየት ከዚህ በታች በቀረበው አድራሻ ሊላክ ይችላል፥

የተባበሩት መንግስታት የፈንጅ መከላከል አገልግሎት (የተመፈመአ)
ኒው ዮርክ, NY 10017 USA

ኢማይል፥ mineaction@un.org
ዌብሳይት፥ www.mineaction.org

© የተባበሩት መንግስታት 2008 (3ኛ እትም)
መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው

**የሽፋናን ፎቶዎች**
መደብ፣ የተመድ ፎቶ/ሌዞን ፋውንቴን
የተመፈመአ ፎቶ/ማርክ ቫይላንት

**የፈንጅ ምልክቶች**
ሽፋንና ገጽ 8, 9, 36, 37, 56, 57, 76, 77, 88, 89, 96, 97
ዋና ዘት

**አርታኢ**
ቶማስ ኢንኬ

**ዲዛይንና የገጽ አቀማመጥ**
ማከንዚ ክሮን

# በተባበሩት መንግስታት
# ከፈንጂ፣ ከሚፈነዱ ጦር መሣሪያዎችና ከተራ የሚፈነዱ ዕቃዎች አደጋ
# መከላከያ መጽሐፍ

የተባበሩት መንግስታት
የተባበሩት መንግስታት የፈንጂ መከላከል አገልግሎት (የተመፈመአ)
ኒው ዮርክ፣ NY 10017 USA
ኢሜይል፥ MineAction@un.org
ዌብሳይት፥ www.mineaction.org

**በተቀባሪ ፈንጂዎችና ሌሎች የሚፈነዱ ጎጂ ነገሮች እንዲሁም ተራ በሚፈነዱ ዕቃዎች በተበከሉ አካባቢዎች ለሚሠሩ ሰዎች የተዘጋጀ መመመሪያ**

# ማውጫ


ምስጋና 5

መግቢያ 6

## 1 የሥጋት ምንጭ 9

1.1 ፈንጂዎች 11
1.2 ያልፈነዱ መሣሪያዎች 19
1.3 የተተወ መሣሪያ 32
1.4 ተራ የሚፈነዱ መሳሪያዎችና ስውር ወጥመዶች 33

## 2 አደገኛ ቦታዎችን መለየት 37

2.1 የማስጠንቀቂያ ምልክቶች 38
2.2 የማስጠንቀቂያ ፍንጮች 42
2.3 የውጊያና የወታደራዊ እንቅስቃሴ ምልክቶች 45
2.4 አካባቢያዊ ምልክቶች የሞቱ እንስሳትና ያልተለመዱ ዕቃዎች 49
2.5 የአካባቢ ሁናቴ 53

## 3 መሠረታዊ የደህንነት ምክሮች 57

3.1 ለአደጋ አጋላጭ ባህርይ 59
3.2 ስለፈንጂዎችና ስለሚፈነዱ የጦርነት ቅሪቶች የተለመዱ አባባሎች 62
3.3 ለድርጅቶች የሚሆን ምክሮች 64
3.4 ለግለሰቦች የሚሆኑ የደህንነት ምክሮች 66

## 4 የድንገተኛ አደጋ ጊዜ የአፈጻጸም መመሪያ 77

4.1 በሚፈነዳ ነገር በተበከሉ ቦታዎች ወይም ፈንጂ ባለባቸው ቦታዎች የአደጋ ጊዜ መመሪያ 78
4.2 የተፈዐ ጥቃት የአደጋ ጊዜ መመሪያ 84

## 5 የአደጋ ተጎጂን መርዳት 89

5.1 ምንነቱ ካልታወቀ ፍንዳታ ቦታ መውጣት 91
5.2 የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ አሰጣጥ 92

## አባሪዎች 97

ሀ1 የጉዞ ካርዶች አጠቃ 98
ሀ2 ለተሽከርካሪ ተጨማሪ መከላከያ ለመስጠት የሚወሰዱ እርምጃዎች 106
ሀ3 5/25 ሜትር ፍተሻ 108
ሀ4 ሌሎች የስጋት ምንጮች 109
ሀ4.1 አገልግሎቱን የጨረሰ ዩራኒየም
ሀ4.2 ባዮሎጂካዊና ኬሚካላዊ መሣሪያዎች
ሀ5 ከአደገኛ ቦታ የማምለጫ ርቀት መመሪያ 114
ሀ6 እነ ዘጠኞ 114
ሀ7 መፍትሔ ቃላት 116
ሀ8 የሚዘወተሩ ምኅጻረ ቃላት 120
ሀ9 የተጨማሪ መረጃ ምንጮች 120

በአደጋ ጊዜ የሚያገለግሉ አድራሻዎች 125

ማስታወሻዎች 126



**ሥዕል 1**
የደህንነት ርቀትን መጠበቅ የአፍጋኒስታን መንደር ነዋሪዎች የመሳሪያ ድምሰሳን ሲመለከቱ።
የተመአመአ ፎቶ/ቶማስ ኢንኬ

# ምስጋና

ይህ መጽሐፍ በ1997 የፈንጂ አደጋን ስለመከላከል ኬር በተባለ ድርጅት በተዘጋጀና በታተመ መጽሃፍ ላይ ተመሥርቶ በተባበሩት መንግስታት በ2005 ዓ.ም. የተዘጋጀው የፈንጂና ያልፈነዱ መሣሪያዎችን አደጋ የመከላከል ሶስተኛ እትም መጽሃፍ ነው። መጽሀፉ ወቅታዊ የሆኑ ጽንሰሃሳቦችን ለማካተት እንዲችል ርእሱ ሳይቀር መሠረታዊ የሆነ ማሻሻያ ተደርጎበታል። በተጨማሪም በፈንጂ ማምከን፣ በሚፈነዱ ጦርመሳሪያዎች አወጋገድ እና በተራ የሚፈነዱ እቃዎች አወጋገድ እንዲሁም በድንገተኛ አደጋ ህክምና ዙሪያ አዳዲስ አሰራሮችንም ከግንዛቤ ውስጥ አስገብቷል። በተራ የሚፈነዱ ዕቃዎች አማካኝነት እየጨመረ የመጣው ስጋት አሁን ባሉት ምእራፎች ላይ ተጨማሪ ነገሮች እንዲካተቱ አድርጓል።

ፈንጂዎች፣ የሚፈነዱ የጦርነት ቅሪቶች እና ተራ የሚፈነዱ እቃዎችን አደጋ ለመከላከል በተዘጋጀው በዚህ መጽሃፍ ውስጥ የተካተቱት መረጃዎች የተሰበሰቡት በተባበሩት መንግስታት የህጻናት መርጃ ድርጅት (ዩኒሴፍ) በ1999 ዓ.ም. ከተዘጋጀው አለም አቀፍ የፈንጂና ያልፈነዱ የጦር መሣሪያዎች ግንዛቤ ማስጨበጫ መመሪያ፣ በድረ-ገጽ www.mineactionstandards.org በተባበሩት መንግስታት በታተመው የፈንጅ መከላከል መመሪያ ነው። የፈንጂዎች፣ የሚፈነዱ የጦርነት ቅሪቶች እና የተራ የሚፈነዱ ዕቃዎች አደጋ ለመከላከል የሚውለው ይህ መጽሐፍ የተባበሩት መንግስታት የፈንጂ መከላከል አገልግሎት (ተመፈመአ) አካል የሆነው የፈንጂ ደህንነት ፕሮጀክት አካል ነው።

# መግቢያ

ተቀባሪ ፈንወጂዎችና ሌሎች እንደ ተዘነጉ ተተኳሾች እና ወታደራዊ ቁሳቁሶች፣ ያልፈነዱ መሳሪያዎችና የሚፈነዱ የጦርነት ቅሪቶች ያሉ አደገኛ የሚፈነዱ ነገሮች እንዲሁም ተራ የሚፈነዱ ዕቃዎች በመላው አለም አደጋ የሚደቅኑ ናቸው።

ይህ መጽሀፍ ከፈንጂዎችና ከሚፈነዱ አደገኛ ነገሮች ጋር የተገናኘ ሥራ ለመስራት እንደማስተማሪያ ሆኖ የሚያገለግል አይደለም። በፈንጂዎች፣ በሚፈነዱ የጦርነት ቅሪቶች እና በተራ የሚፈነዱ እቃዎች አደጋ በተደቀኑባቸው ህብረተሰቦች ከነዚህ ነገነሮች ጋር የተያያዘ ስራ ለመስራትም እንደመመሪያ የሚያገለግልም አይደለም። ይልቁንም ዓላማው የፈንጂዎችን፣ የሚፈነዱ የጦርነት ቅሪቶችን እንዲሁም ተራ የሚፈነዱ ዕቃዎችን አደጋ በሚመለከት ለነዚህ ነገሮች ለደጋ በተጋለጡ ስፍራዎች ለሚሰሩ ድርጅቶችና ግለሰቦች ግንዛቤና መሠረታዊ የደህንነት መረጃ መስጠትና እንሱንም በሚከተሉት መለኩ ማገዝ ነው፥

- ትክክለኛ የደህንነት አጠባበቅ መመሪያን ለመመስረት
- ከፈንጂዎች፣ ከሚፈነዱ የጦርነት ቅሪቶች (ፈጦቅ) እና ከተራ የሚፈነዱ ዕቃዎች (ተፈዕ) ጋር የሚኖረውን ንክኪ ለመከላከል እና
- በአደጋ ጊዜ ተገቢ እርምጃዎች እንዲፈጸሙ ማስቻል።

የሚፈነዱ ነገሮችን መቅረብ መቼም ቢሆን አደገኛ ስለሆነ መታቀብ ይገባል። ፈንጂዎችን፣ ፈጦቅ እና ተፈዕ መንካት የሚችለው ስልጠና የወሰደ ባለሙያ ብቻ መሆን አለበት።

በዚህ መጽሀፍ የተካተተው መረጃ በጣም አጠቃላይ የሆነና አንዳነዱ በተተወሰኑ አውዶች ሊተገበር/ሊደረግ የማይችል ሊሆን ይችላል። ስልሆነም እንደየአገሩ ተጨባጭ ሁኔታ፣ መረጃ እና አካባቢያዊ የስጋት ትንተና መሠረት ሊተገበር ይገባል።በተጨማሪም ይህ መጽሀፍ ብቻውን ብቁ ሆኖ እንዲያገለግል ተደርጎ የተዘጋጀ አይደለም። ነገር ግን ተገቢው ስልጠና ባለው ባለሙያ ስለሚፈነዱ ገነሮች ለሚደረግ ገለጻ አጋዥ ሆኖ ሊያገለግል ይገባል።

## ይህን ያውቃሉ?

ከጥር 2007 ዓ.ም. ጀምሮ 162 አባል ሀገሮች በፀረ-ሰው ፈንጂዎች ላይ ማእቀብ እንዲጣል ተስማምተው ፈርመዋል (ስምምነቱ በእንግሊዝኛ ምህጻረ ቃል ኤ.ፒ.ኤም.ቢ.ቲ. ወይም የኦታዋ ስምምነት ተብሎ ይታወቃል)። አንድ አባል ሀገር ፈርማለች ግን ገና ተግባራዊ ነቱን አላጸደቀችም። የፈረሙት አባል ሀገራት ፀረ-ሰው ፈንጂዎችን ከመጠቀም፣ ከማጠራቀም፣ከማምረት፣ ከማዘዋወር ለመታቀብና በየሀገሮቻቸው ያሉትንም ለማጥፋት ተስማምተዋል። በተጨማሪም በስምምነቱ መሠረት የፈንጂ ጉዳተኞች እርዳታ የማግኘት መብትንም አካቷል።

በተቻለ መጠን የዚህ መጽሀፍ አንባቢዎች በየአካባቢው የሚሰሩ ባለሙያዎችን ምክርና መመሪያ ሊያገኙ ይገባል።

መጽሀፉ በአምስት ዋና ዋና ክፍሎችና አባሪዎች የተከፋፈለ ነው።

**ክፍል 1**

**በፈንጂዎችና በሌሎች የሚፈነዱ አደገኛ ነገሮች ማለትም ፈጦቅና ተፈዕ አማካኝነት ስለሚደርስ ስጋት መረጃ ይሰጣል።**

**ክፍል 2**

**አንድ አደጋ ሊያስከትል የሚችል ነገር እንዴት መለየት እንደሚቻል ምክር ይሰጣል**

**ክፍል 3**

**አደጋ ሊያስከትል ከሚችል ነገር እንዴት መታቀብና ራስን ከአደጋ መጠበቅ (ደህንነትን መጠበቅ እንደሚቻል ምክርና መረጃ ይሰጣል።**

**ክፍል 4**

**በተተዒሸ ነገሮች በሚገኙበት አካባቢ ራስዎን ቢያገኙ ማድረግ ስለሚገባዎ ነገር ማብራሪያ ይሰጣል።**

**ክፍል 5**

**አደጋ በተከሰተ ጊዜ ምን መደረግ እንዳለበት መሠረታዊ መረጃ ይሰጣል።**

አባሪዎች ጉዞ በሚደረግበት ጊዜ መከናወን ስላለባቸው ጉዳዮች፣ ስለሌሎች የስጋት ምንጮች ማለትም አገልግሎቱን ስለጨረሰ ዩራኒየም፣ስለኬሚካላዊና ባዮሎጂካዊ ተተኳሾች መረጃ ይሰጣሉ፤ ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢ ለመፍጠርም ዘዴዎችን ይጠቁማሉ።

ስምመነቱ በተግባር መዋል ከጀመረበት እ.ኤ.አ ከ1999 ዓ.ም. ጀምሮ የፀረ-ሰው ፈንጂ ጥቅም ላይ ማዋል እየቀነሰ መጣ። ነገር ግን ጥቂት ሀገሮች (ስምመነቱን ያልፈረሙ) ፀረ-ሰው ፈንጂን መጠቀምና ማከማቸት በመጀመራቸው በ59 ሀገሮችና በ4 አካባቢዎች ቀደም ብለው በተካሄዱና አሁን እየተካሄዱ ባሉ ግጭቶች ምክንያት ሰፊ ቦታዎቻቸው በፈንጂ ወጥመዶች ተበክለዋል።[1] ፀረ-ሰው ፈንጂዎች ግጭት ተካሂዶባቸው በነበሩ ስፍራዎች የሚሰሩ ሰዎች ላይ የከፋ አደጋ ከሚፈጥሩት አስጊ ነገሮች የሚመደቡ ናቸው።

[1] የፈንጂና የክለስተር ተተከዋሽ ቁጥጥር፣

# ክፍል 1

## የስጋት ምንጭ



**ሊቢያ**

ተመራመአ ፎቶ/ ጂዮቫኒ ዲፊደንቲ

# የስጋት ምንጭ

የጦርነት ግጭት ተካሄዶባቸው በነበሩ ቦታዎች የሚሰሩ ሰዎች በፈንጂ ፣ ባልፈነዱ ወይም በተተው የሚፈነዱ መሳሪያዎች ፣ በተተው የወታደራዊ ተሽከርካሪዎች እና ቁሳቁሶች እንዲሁም በተራ የሚፈነዱ እቃዎች አማካኝነት ለሚከሰት አደጋ የተጋለጡ ናቸው። (ማስታወሻ ፈጦቅ የሚለው ስያሜ ያልፈነዱ የጦር መሣሪያዎችን እና የተዘነጉ የሚፈነዱ የጦር መሣሪያዎችን ያጠቃልላል፤ ግን ፈንጂዎችን አያጠቃልልም፤ ስለ ብያኔው ሙዳየ ቃላቱን በአባሪ 6 ይመልከቱ)። ማንኛውም የሚፈነዳ እቃ ሁሉ ግጭቱ ከቆመ ከአመታት በኋላም ቢሆን ወደፕሮጀክት ስፍራዎች መድረስን ሊያግዱ ወይም ለደህንነት ስጋት ሊደቅኑ ይችላሉ። በነዚህ ቦታዎች ላይ በሚሠራበት ጊዜ፣ ድርጅቶችና ግለሰቦች በጦርነት ጊዜና ከጦርነት በኋላ በቦታው ላይ የተተው የተለያዩ የጦር መሣሪያዎች ፊዚካል ሥጋት ሊፈጥሩ እንደሚችሉ ማወቅ ይኖርባቸዋል።

ራስዎን ለመከላከል፤ ስጋት ስለሚፈጥረው ነገር ግንዛቤ ሊኖርዎትና ተገቢ የመከላከል እርምጃ ሊወስዱ ይገባል። ይህ ክፍል ፈንጂዎችን፣ ፈጦቅን፣ ተፈዕን ለመለየት፤ እንዴት እንደሚሰሩ የሚያስከትሉት ውጤት (ጉዳት) ምን ሊሆን እንደሚችል ያብራራል። ሁሉንም አይነት ፈንጂዎች፣ ፈጦቅ እና ተፈዕ በዚህ መጽሀፍ መግለጽ አይቻልም፤ ስለዚህም የተለመደ ግንዛቤን መሠረት ማድረግ ይገባል። እንደአጠቃላይ ህግ ምንጊዜም ቢሆን የማይታወቁ እቃዎች ሲገኙ በጥርጥሬ ሊታዩ ይገባል። የተወሰኑ የተለመዱ የስጋት ምንጮች ገለጻ ይቀጥላል።

## ይህን ያውቃሉ?

**ፈንጂ የሚለው ቃል በእንግሊዝኛ “mine” የሚባል ሲሆን ምንጩም *mina* የሚለው የላቲን ቃል ነው። ትርጉሙም “ በጉድጓድ ውስጥ የተቀበረ” ማለት ሲሆን በመጀመሪያ የነበረው ትርጓሜም ሚኒራሎችን ከመሬት ውስጥ ቆፍሮ ማውጣትን ነበር። ቃሉን በኋላ ሥራቸው ከወታደራዊ ድንበሮች ምሽጎችና ጉድጓዶች ፍንጂዎችን መቆፈር የሆኑ፣ ግድግዳዎችን ለማፈራረስ ከስር የሚቀብሩ ወታደራዊ መሃንዲሶች ተውሰውታል። ዘመናዊ የሚቀበሩ ፍንጂዎች የሚፈነዱ ወጥመዶች ናቸው፤ ታሪካዊ አመጣጣቸው ግን ከ2500 አመታት በፊት ጀምሮ ጥንታዊ ሰራዊቶች ይጠቀሙባቸው ከነበሩ እንደ ተተከሉ ጦሮችና ችካሎች ካሉ ከማይፈነዱ ወጥመዶች ነው።**

ክሮል፣ ኤም.። የፈንጂዎች ታሪክ፣ 1998
(Croll, M., History of Landmines. 1998)

## 1.1 ፈንጂዎች

ፈንጂዎች ተሽከርካሪዎችን ለመጉዳት፣ ወይም ሰዎችን ለማቁሰል፣ ለመግደልና ተግባራቸውን ለመገደብ ታስበው የሚሰሩ የሚፈነዱ መሣሪያዎች ናቸው።ፈንጂዎች የተጠመዱ ፈንጂዎች በተጎጂዎች ተቁሞባቸው ወይም ተረግጠው ሊፈነዱ አልያም በቀጥተኛ ግፊት፣ ማስፈንጠሪያ ገመድ፣ አጋድሎ በቆመ ብረት፣ በማስነሻ መቆጣጠሪያ ወይም ከነዚህ በተወሰኑት ጥምረት ምክንያት ሊፈነዱ ይችላሉ። ከዚህ በተጨማሪም በእጅ ሊያዙ በማይችሉ እቃዎች አማከኝነት ተጠቅልለው ለማስወገድ አስቸጋሪ ተገርገው ሊጠመዱ ይችላሉ። ወይም የሚፈነዱበት ጊዜ ተቀጥሮላቸው የተሞላው ጊዜ ሲያልቅ ሊፈነዱ ይችላሉ።

ፈንጂዎች ለመከላከል የሚያገለግሉ የጦር መሣሪያዎች ናቸው፡ ጠቃሚ የሆነ ወታደራዊ ቦታን ለመከላከል ያገለግላሉ፤ ወይም በጠላት ወታደሮች ላይ ጉዳት በማድረስና ቁሳሶችን በመደምሰስ የጠላትን እንቅስቃሴ ያዘገያሉ። ለማጥቃትም ሊያገለግሉ ይችላሉ፤ በተለይም በግጭት ቦታዎች መሠረተልማቶችን በመደምሰስ ሲቪል ማህበረሰቡ ወደቤቱ፣ ወደእርሻ ቦታው፣ ወደውሃ መቅጃው፣ ወደመንገዶች፣ ወደትምህርት ቤቶች፣ ወደጤና ተቋማት እና ወደሌሎች ተፈላጊ አቅርቦቶች እንዳይሄዱ በማቀብ ሽብር ለመፍጠር ያገለግላሉ። ፈንጂዎች ብዙ ጊዜ የተፈዕ መሥሪያ ሆነውም ያገለግላሉ። በተጎጂ አማካኝነት እንዲፈነዱ በሚደረጉ በፈንጂዎች ውስጥ ፍንዳታውን የሚያስነሳው ንጥረነገር በማስፈንጠሪያው ወይም በራሱ በፈንጁ ላይ ተደርገጎ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል።

ፈንዎች ከሞላ ጎደል ሁልጊዜ ለማየትና ለመለየት አስቸጋሪ እንዲሆኑ ተደብቀው እና ከአካባቢው ጋር እንዲመሳሰሉ ተደርገው ነው የሚጠመዱት። ብዙ ጊዜ በሳር ወይም በህንጻ፣ ችካል ወይም ዛፍ ላይ ተጣብቀው ይቀበራሉ። በመደበኛ ጦርነት ወቅት ፈንጂዎች ብዙ ጊዜ የሚቀመጡት በመንገዶች እና በስትራቴጂክ ቦታዎች ላይ ለመድረስ ፈተና ይሆኑ አንድ ሰልታዊ በሆነ መልክ ነው የሚቀመጡት። በአዳዲስ ፈንጂ በተቀበረባቸው ቦታዎች፣ የፈንጂ መገኛ ቦዎች በካርታ ላይ ሊመዘገቡ ይገባል።[2] ሆኖም ይህ ሁልጊዜ አስተማማኝ አይደለም።



ስዕል 1.1
**በፈንጂዎች የተበከሉ ቦታዎች፣ ማስፈንጠሪያ ወጥመዶች እና የሚፈነዱ የጦር መሳሪያ ቅሪቶች በመለው ዓለም አንዳንድ ጊዜ ግጭቱ ከተካሄደ ከረጅም ጊዜ በኋላም ሊገኙ ይችላሉ።**

የተመፈመአ ፎቶዎች/ቶማስ ኢንክ

[2] ስለፈንጂዎች፣ ወጥመዶችና ሌሎች መሳሪያዎች አጠቃቀም ክልከላዎችና ገደቦች የተሸሻለው ፕሮቶኮል፣ ጄኔቫ፣ እ.ኤ.አ. 03 ህዳር 1996።

ሁሌም ማለት ያቻላል፤ በቋሚነት በሚንቀሳቀሱ ወታደራዊ ክፍሎች ቦታና ጊዜ ሳይለዩ ሊጠመዱ ይችላሉ። አንዳንድ ፈንጂዎች ግን በአየር ወይም በሌላ መሣሪያ አማካኝነት በሰፊ ቦታ ላይ ግልጽና ወጥነት በሌለው መልክ ተበታትነው ሊቀመጡ ይችላሉ።

በአሁኑ ጊዜ በውጊያ በተሰማሩ ወታደራዊ ኃይሎች (ወይም በነሱ ተቃዋሚዎች) የተሰሩ ከ600 በላይ የሆኑ የሚቀበሩ የፍንጂ አይነቶችና ብዙተራ ፈንጂዎች አሉ። እነሱምበሁለት ታላላቅ ምድቦች ይመደባሉ፡ ፀረ-ሰው እና ብዙ ጊዜ ፀረ-ታንክ ተብለው የሚታወቁት ፀረ- ተሽከርካሪ ፈንጂዎች።

## 1.1.1 ፀረ-ሰው ፈንጂዎች

ፀረ-ሰው ፈንጂ ሰው ሲኖር፣ሲቀርብ ወይም ሲነካው እንዲፈነዳ ተደርጎ ሰዎችን አቅም ለማሳጣት፣ አካል ለማጉደል፣ ለማቁሰል ወይም ለመግደል የተሠራ ነው። ፀረ-ሰው ፈንጂዎች ብዙ ጊዜ የሚፈነዱት ሲቆምባቸው ወይም ማስፈንጠሪያ ሽቧቸው ሲነካ ነው። ግን የተወሰነ ጊዜ ጠብቀው የሚፈነዱ ወይም በመቆጣጠሪያ ዘዴ አማካኝነት እንዲፈነዱ ሊደረጉ ይችላሉ።

ፀረ-ሰው ፈንጂዎች በመሬት ላይ፣ ተቀብረው ወይም ከመሬት በላይ (ከሆነ ነገር ጋር) ተጣብቀው ሊገኙ የሚችሉ መጠናቸው ትንሽ የሆኑና የተለያዩ ቅርጾች ያሏቸው ናቸው። ብዙ ጊዜ ከአካባቢው ጋር እንዲመሳሰሉ የሚደበቁ ሲሆን የሚሠሩትም ከእንጨት፣ ከፕላስቲክ ወይም ከብረት ነው።

ፈንጂ ተቀብሮባቸዋል ተብለው የሚጠረጠሩ ቦታዎች ሁሉ ሊከለከሉና ሊጠበቁ ይገባል። አንዴ ከፈነዱ፣ ፀረሰው ፈንጂዎች በፍንዳታቸው ወይም በፍንጣሪያቸው አማካኝነት የሞትና ከባድ የመቁሰል አደጋ ያደርሳሉ። የሚመደቡትም ጉዳት በሚያስከትሉበት መንገድ መሠረት ነው፤ ባለብናኝና ጭስ፣ ባለፍንጣሪ፣ ባለትንንሽ ቅርጽ ተከፋይ።[3]

### ማስነሻ ትእዛዝ

በርቀት መቆጣጠሪያ አማካኝነት ሌላ ሁለተኛ ሰው ፈንጁን የሚያፈነዳበት ሂደት ነው። ይህ ሰው አስፈንጣሪ ተብሎ ይጠራል።

### በትእዛዝ ማስነሳት

ሰው ሲቆምበት፣ መኪና ሲነዳበት፣ ቢጋጭ ወይም በሌላ ተመሳሳይ ድርጊት የሚነሳ (የሚፈነዳ)

### የማክሸፊያ መከላከያ

ፈንጂው ሲያዝ ወይም ሲነካ እንዲፈነዳ የሚያደርግና በፀረ-ሰውና በፀረ-ታንክ ፈንጂዎች ላይ የሚገጠም መሣሪያ። የማክሸፊያ መከላከያዎች ፈንጂዎችን የማጽዳት ሥራን ለመከላከል ታስበው የተዘጋጁ ናቸው። የማክሸፊያ መከላከያዎች ከፈጦቅ ወይም ከተፈዐ ላይም ሊገጠሙ ይችላሉ።

[3] ለምሳሌ የካናዳ ሲ3ኤ2 ፀረ-ሰው ፈንጂ



1.1 ፈንጂዎች
1.1.1 ፀረ-ሰው ፈንጂዎች

### 1.1.1.1 ብላስት ፀረ-ሰው ፍንጂዎች

ብላስት ፀረ-ሰው ፍንጂዎች ብዙ ጊዜ በጣም ርካሽና በአለማችን በብዛት የሚገኙ ናቸው። ብዙ ጊዜ እንደመረገጥ ባሉ አካላዊ ንክኪዎች አማካኝነት በሚደረግ ግፊት እንዲፈነዱ ተደርገው የተሰሩ ናቸው። አብዛኞቹ የነዚህ አይነት ፈንጂዎች ብዙ ጊዜ ከሞት ይልቅ እንደ አካል መጉደል አይነት የከፋ ጉዳት ያስከትላሉ።

በአጠቃላይ ብላስት ፈንጂዎች የሲሊነደር ቅርጽ ያላቸው ሲሆኑ ከ7 እስከ 16 ሳሜ የሚደርስ ዲያሜትርና ከ5 እስከ 10 ሳሜ የሚደርስ ቁመት አላቸው። ነገር ግን፣ እንዳነድ ብላስት ፈንጂዎች አራት ማዕዘን ቅርጽ ወይም የጫማ ማስቀመጫ ካርቶን የመሰለ ቅርጽ አላቸው። መጠናቸውም ከ10 በ18 ሳሜ እስከ 15 በ30 ሳሜ ይደርሳል። ብዙዎቹ ፀረ-ሰውፈንጂዎች አንጻራዊ በሆነ መልክ ጥቂት የሚፈነዳ ንጥረ ነገር አለቸው፤ብዙ ጊዜ ከ100 ግራም ያነሰ ነው። ይህ የታመቀ ብላስት ንጥረነገር ነው ለሞትና ለጉዳት የሚዳርገው።

### ንጥል ጥናት

ፈንጂዎች በመለው ዓለም በዐለማችን አካባቢ ሰዎችን አካል በማጉደልና በመግደል ያለማቋረጥ የዘለቁ አደገኛ የሚፈነዱ መሣሪያዎች ናቸው። የሽፋናቸውን መጠን ማወቅ ይችሉ አንድ በኢንተርኔት በ2007-8 የተከሰተ የፈንጂ አደጋ (Landmine Accidents 2015) ብለው ቢፈልጉ ማግኘት ይችላሉ።

ክሮል ኤም.። የፈንጂዎች ታሪክ ፣ 1988 (Croll, M., History of Landmines. 1998)

ስዕል 1.2
ይህ ትንሽ ፈንጂ እግርን መበጣጠስ ይችላል። 10 ሳሜ አካባቢ የሚደርስ ዲያሜትር ያለው ሲሆን ከተቀበረ ለማየት አይቻልም (ግራ)። በፈንጂ አመካኝ የተሰበሰቡ ተመሳሳይ ፈንጂዎች (ቀኝ)።
የተመፈመአ ፎቶዎች/ቶማስ ኢንኬ





አንዳንድ ብላስት ፈንጂዎች እስካሁን ከብረትና ከእንጨት ቢሰሩም፤ አብዛኞቹ የሚመረቱት በፕላስቲክ ነው። ይህም ውሃ እንዲቋቋሙ ወይም ውሃ የማይገባባቸው እንዲሆኑ ስላደረጋቸው በውሃ ውስጥም ሆነውም ቢሆን አደጋ ያደርሳሉ። ፈንጂዎች ከተቀመጡባቸው ቦታዎች ላይ በከባድ ዝናብ ምክንያት ከፈንጂ ነጻ ወደሆኑ ቦታዎች መወሰዳቸው ወይም በውሃ መውረጃዎች ተላልፈው ብዙ ኪሎሜትሮችን ርቀው ከሄዱ በኋላ ወደዳር ተተፍተው መገኘታቸው ያልተለመደ ነገር አይደለም።የብላስት ፈንጂዎች ቀለም ብዙ ጊዜ ጠቆር ያሉ፣ ወይራ መልክ፣ አረንጓዴ፣ ግራጫ፣ ቡኒ ወይም የነዚህ ቅልቅል ሊሆን ይችላል።

ከሚቀበሩ ብላስት ፈንጂዎች በተጨማሪ በጣም የሚታወቁ የፈንጂ አይነቶች በአየር ወይም በመበተኛ መሳሪያ አማካኝነት የሚበተኑት ‹‹ቢራቢሮ›› ፍንጂዎች (ወይም ተመሳሳይ አይነት) ናቸው (ስለክለስትር ቦምቦች የሚያትተውን ምዕራፍም ይመልከቱ)። ወዲያውኑ ከተደረሰባቸው እነዚህ ፈንጂዎች የሚገኙት በመሬት ላይ በብዛት ተከማችተው ነው። ከወራትና ከዓመታት በኋላም ቢሆን ነጠላ ፈንጂዎች ነጻ ነው በተባሉ ቦታዎች ላይም ሊገኙ ይችላሉ። ቢራቢሮ ፈንጂዎች ያልተለመዱ ቅርጾች ቅልቅል የሆኑና ብዙ ጊዜ ህጻናትና አዋቂዎችን እንዲስቡ ልዩና የሚስብ ቀለም ያላቸው ናቸው።







ስዕል 1.3
ሳጥን መሰል ፀረ-ሰው ፈንጂ ተመሳሳይ ፈንጂዎች በመለው ዓለም ይገኛሉ።
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢነኬ

ስዕል 1.4
እነዚህ ከአየር የተወረወሩ <<ቢራቢሮ>> ፒ.ኤፍ. ኤም-1 ፈንጂዎች ሲነኩ ሊፈነዱ ይችላሉ፣አፍጋኒስታን።
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢነኬ

ስዕል 1.5
እነዚህ ከአየር የተወረወሩ <<ቢራቢሮ>> ፒ.ኤፍ. ኤም-1 ፈንጂዎች ሲነኩ ሊፈነዱ ይችላሉ፣አፍጋኒስታን።
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢነኬ

## 1.1.1.2 ተፈናጣሪ ፀረ-ሰው ፈንጂ

ተፈናጣሪ ፈንጂዎች ብዙ ጊዜ በሚፈነዱበት ጊዜ በሚወረውሩት ፍንጣሪ አማካኝነት ብዙ ሰዎችን ለመግደል እንዲችሉ ተደርገው የተሠሩ ናቸው። አብዛኞቹ እንደዚህ ያሉ ፈንጂዎች የብረት ሽፋን ያላቸው ፣ ወይም ኳስ መሳይ ፍንጣሪ ወይም የብረት ቁርጥራጮችን የሚፈጥ ሽፋን አላቸው። እነዚህም ፈንጂ በሚፈነዳበት ጊዜ ወደ ገዳይ ተወንጫፊነት ይለወጣሉ።

ሦስት አይነት የተፈናጣሪ ፈንጂ አይነቶች አሉ፡ ተሰኪ ፈንጂዎች፣ አቅጣጫ ውስን ፈንጂዎች፣ ነጣሪ ተፈናጣሪ ፈንጂዎች።





### > 1.1.1.2.1 ተሰኪ ፀረ-ሰው ፈምጂዎች

በጣም ብዙ ጊዜ የሚኙት የፀረ-ሰው ፍንጂዎች አደገኛ የፀረ-ሰው ፍጂዎች ናቸው። እነዚህም ፈንጁ ከመሬት በላይ 20 ሳሜ እስኪሆን ድረስ ወደመሬት በሚተከሉ የእንጨት ወይም የብረት ችካሎች ላይ እንዲሰኩ ተደርገው የተሰሩ ናቸው። እንዲሁም በዛፍ ላይ ሊጣበቁም ይችላሉ። አብዛኛውን ጊዜ ትንሽ ነገር መስለው ይታያሉ፤ ማለትም የእንጨት ችካል ሆኖ ላዩ ላይ ትንሽ የብረት ሲሊንደር ያለባቸውና የሚፈነዳው አካል ከአናታቸው ያለባቸው። ብዙ ጊዜ አረንጓዴ ይቀባሉ፣ ወይም ያለተቀቡ እንጨትና ብረት መልክ ሊኖራቸው ይችላል። የሚዝጉ የብረት ሽፋኖች ፈንጂዎችን ለመለየት ቀላል ያደርጋሉ፣ በተለይ ረጃጅም ዛፎች ባሉበት አካባቢ።

ተሰኪ ፈንጂዎችበ በተሳቡ ወይም በተቆረጡ ጊዜ ሊያፈነዱ በሚችሉ በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ሽቦዎች የተሰኩ ናቸው። እነዚህ ሽቦዎች ለመታየት ስማይችሉ በመንገድ ላይ ወይም በመተላለፊያዎች ላይ ሊዘረጉ እንዲሁም እንደ ዛፍ ወይም ሌላ ፈንጅ ካሉ ሌላ ጠንካራ ነገሮች ጋር ሊያያዙ ይችላሉ።

አንዴ ከፈነዱ የብረት ፍንጣሪዎች በ360 ዲግሪ ራዲየስ እየተምዘገዘጉ በ4 ሜትር ራዲየሰ ውስጥ ያለከለላ ያለ ማንኛውም ሰው ላይ የሞትና የከፋ አደጋ ሊያደርሱ ይችላሉ ። አንድ ተራ ፀረ-ሰው ፈንጂ - የሩሲያ ስሪቱ ፒ.ኦ.ኤም. ዜድ-2ኤም- ሲፈነዳ በ10 ሜትር ራዲየስ ውስጥ የከፋ ሊባል የሚችል አደጋ የሚያደርስ ነውጥ ሊፈጥር ይችላል። ከዚህም በላይ የፍንጣሪዎች መጠንና ስርጭት መለያየት የሚያደርሱትን አደጋ ውጤት ለመተንበይ አስቸጋሪ የደርገዋል። ታላላቅ ፍንጣሪዎች እስከ 100 ሜትር ወይም ከዚያ በላይ በሆነ ርቀት ጉዳት ወይም ሞት ሊያስከትሉ ይችላሉ።[4]

ከጊዜ በኋላ ተሰኪ ፈንጂዎች ከተሰኩበት ሊወድቁ ወይም ሊለያዩ ይችላሉ። እንዲህ መሆናቸው አደገኛነታቸውን አይቀንሰውም፤ በአንዳንድ ሁኔታዎች ማስፈንጠሪያው ሽቦ የማይታይ ከሆነ የበለጠ አደገኛ ይሆናሉ።

[4] የርቀቶች መጠን ምንጭ፡ ኮሊን ኪንግ፣ የየጄን ፈንጂዎች እና የፈንጂማጽዳት እንዲሁም የጄን የሚፈነዱ መሳሪያዎች አወጋገድ ጸሃፊ ነው

### ማስፈንጠሪያ ሽቦ (ወጥመድ)

ፈንጂን፣ ወጥመድን ወይም ተራ የፈነዳ ዕቃና ለማሰነሳት (ለማፈንዳት) የሚያገለግል ቀጭን፣ የማያብረቀርቅ ሽቦ ወይም ገመድ ነው። ማስፈንጠሪያ ሽቦ (ወጥመድ) ብዙ ጊዜ በቦታው የሚያልፍ ሰው እንዲነካውና የሚፈነዳውን መሳያ እንዲያስነሳ ለማድረግ ከመሬት ላይ ዝቅ ብሎ ይጠመዳል። ማስፈንጠሪያ ሽቦዎች ጥቅም ላይ ሲውሉ ከፈንጂዎች እስከ 30 ሜትር ርቀት ድረስ ሊዘረጉ ይችላሉ።



ስዕል 1.6
ደንበኛ የተሰኪ ፈንጂና የማስፈንጠሪያ ሽቦ አጠቃቀም፡ በመንገድ ጫፍ ላይ ተጠምዶና ተደብቆ የተተወና በእጽዋት የተሸፈነ መሳሪያ።
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢለኬ

### > 1.1.1.2.2 ሁል አቅጣጫ ተፈናጣሪ ፀረ-ሰው ፈንጂዎች

በሁሉም አቃጣጫ የሚፈናጠሩ (ወይም «የክሌይሞር» አይነት) ተፈናጣሪ ፀረ-ሰው ፈንጂዎች ወደአንድ ወደተወሰነ አቅጣጫ ችምችም ያሉ ፍንጣሪዎችን እንዲወረውሩ ተደርገው የተሰሩ ፍንጂዎች ናቸው።አብዛኞቹ የሚመስሉት ባለደጋን አራት ማእዘን ወይም ክብ ሳጥን ሆነው ውፍረታቸው የአንድ መጠነኛ መጽሀፍ ያህላል። ሳጥኑ በሁለት ጥንድ እግሮች ወይም መቀመጫ ላይ የሚያርፍ ሆኖ በአጠቃላይ ወይራ መልክ፣ ጥቁር ወይም ቡኒ ይቀባል።

አቅጣጫ ይዘው የሚፈናጠሩ ፀረ-ሰው ፈንጂዎች በአብዛኛው በትእዛዝ የሚፈነዱ ናቸው፤ሆኖም በማስፈንጠሪያ ሽቦ ወይም በግፊት ፈጣሪ ሰሌዳዎች ሊፈነዱ ይችላሉ። እንዲህ አይነት ፈንጂዎች አንዴ ከፈነዱ አግድም በ60 ዲግሪ ደጋንና በ2 ሜትር ከፍታ ይሸፍናሉ። አብዛኞቹ በሚሸፍኑ ቦታ ከ50 ሜትር በላይ ከባድ ጉዳት ወይም ሞት ለማስከተል ብቁ ተደርገው ነው የተሰሩት።

ሌሎች የፈንጂ አይነቶች ትልልቅና ክብቅርጽ ያላቸው የጥቃት ሽፋናቸውም እንደጠመንጃ ተኩስ ሾጣጣ ቅርጽ ያለው ኮን የሚሸፍን ነው። ፈንጂዎቹ ሰዎችን የመግደል፣እንዲሁም አካለጉዳተኛ የማድረግ ወይም አካላቸው ለስላሳ የሆኑ የመንገደኞችን ተሽከርካሪ የመደምሰስ ብቃታ ላቸው።

### > 1.1.1.2.3 ታሳሪ ባለተፈናጣሪ ፀረ-ሰው ፈንጂ

ታሳሪ ፈንጂዎች በተለምዶ የሚቀበሩና ከማስፈንጠሪያ ሽቦ ጋር የሚያያዙ ናቸው። አብዛኞቹ ታሳሪ ፈንጂዎች ነጠላ ቲዩብ ቅርጽ ያለው ፊዩዝ ወይም በአናት በኩል ባሉ ብዙ ቀዳዳዎች የተያያዘ ፊዩዝ ያላቸው ባለሲሊንደር ቅርጽ አላቸው። በዋናነት 10 ሳሜ የሚሆን ዲያሜትርና 28 ሳሜ የሚሆን ከፍታ አላቸው። ታሳሪ ፈንጂዎች ብዙ ጊዜ ጠቆር ያሉ፣ ወይራ መልክ፣ ጥቁር፣ ቡኒ እና አረንጓዴ ቀለም ሊቀቡ ወይም ቀለም ላይቀቡ ይችላሉ። ከተወሰኑ ዓመታት በኋላ የብረቱ ሽፋን ስለሚዝግ ፈንጂዎቹን ለመለየት አስቸጋሪ ያደርጋቸዋል።







ስዕል 1.7
ተሰኪ ፀረ-ሰው ፈንጂ።
ማስፈንጠሪያውን ሽቦ ማየት ይችላሉ።
የተመፈመአ ፎቶ

ሥዕል 1.8
መካከል፥ ‹‹ሳንጃ›› መሰል ፈንጂ ኤም.ኦ.ኤን-50።ወደአንድ-ብዙ ጊዜ መንገዶችና ጎዳናዎች ላይ- አቅጣጫ ብቻ ፍንጣሪዎችን የሚተኩስ።ብዙ ፈንጂዎች እርስበርስ ሊያያዙ ይችላሉ፤ በዛፍ ላይ ሊቀመጡም ይችላሉ! ከታች፥ የሳንጃ መሠል ፈንጂ ፔዞ-ፐሬዝር መለኪያ።
የተመፈመአ ፎቶ



1.1 ፈንጂዎች
1.1.1 ፀረ-ሰው ፈንጂዎች

ታሳሪ ፈንጂዎ ብዙ ጊዜ የሚፈነዱት በማስፈንጠሪያ ሽቦ ወይም በጫና/ ግፊት ምክንያት ነው። በሚፈነዱበት ጊዜ የመጀመሪያው ፍንዳታ ዋናው ፍንዳታ ከመጀመሩ በፊት ፈንጁን ወደላይ በደረት ልክ ያነሳዋል። በዋናው ፍንዳታ ጊዜ የብረት ፍንጣሪዎች 360 ዲግሪ አግድም ራዲየስ ይወረወራሉ። በአሠራራቸው ልዩነት ምክንያት የፍንጣሪዎች ብዛት፣ መጠን፣ የስርጭት ሁኔታ በጣም ይለያያሉ፤ ግን ዋነኛ ጣሳሪ ፈንጂ በ25 ሜትር ቅርበት ቀሳፊ (ገዳይ) ሲሆን እስከ 100 ሜትር የከፋ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል።

### > 1.1.1.2.4 ሾጣጣ ፀረ-ሰው ፈንጂዎች

ሾጣጣ ፀረ-ሰው ፈንጂዎች በአብዛኛው የሚቀበሩ ናቸው። ሲሊንደር መሳይ ቅርጽ ያላቸው ሲሆኑ ወደመሬት ሰርስረው እንዲገቡ የሚያስችላቸው ሹል ጫፍና በአፈር ውስጥ ተመቻችተው እንዲቀመጡ የሚያደርጋቸው ጠፍጣፋ ሰሌዳ አላቸው። ባለ 5 ሳሜ ዲያሜትርና ባለ 12 ሳሜ ከፍታ ሲሆኑ ቀለማቸውም ብዙ አይነት ሊሆኑ ያችላሉ፤ በአብዛኛው ግን ቢጫ ወደ ብርቱካናማ፣ አረንጓዴ ወይም ጥቁር ናቸው።

በፀረ-ሰው ፍንጂዎች ላይ መቆም ፊዩዛቸውን ያቀጣጥለዋል (ተጎጂ በሚያፈነዳቸው ፈንጂዎች)። በአጠቃላይ እንዲህ አይነት ፀረ-ሰው ፈንጂ ተጎጂውን ለመግደል ታስቦ የሚሠራ አይደለም። ውስጣቸው በሚገኘው ትንሽ መጠን ያለው የሚፈነዳ ንጥረ ነገር የሚተኮሰው ስለት ያለው ፍንጣሪ ከውስጠኛው የእግር ክፍል በቁርጭምጭሚት አልፎ የሰዎችን እግር በመጉዳት እስከ ጉልበት ይደርሳል። ውጤቱም ከጉልበት በላይ መቆረጥ ወይም የረጂም ጊዜ ህክምና የሚያስፈልገው ጉዳት ይሆናል።

## 1.1.2 ፀረ-ተሽከርካሪ ፈንጂዎች

ፀረ-ተሽከርካሪ ፈንጂዎች (ፀተፈ) ብዙ ጊዜ ፀረ-ታንክ ፈንጂች ተብለው የሚጠሩ ሲሆን የሚሰሩትም ተሽከርካሪዎችን ለማሰናከል ወይም ለመደምሰስ ነው። እንደ ፀረ-ሰው ፈንጂ (ጠሰፈ) የሚፈነዱት በአብዛኛው በከባድ ክብደት አማካኝነት በሚደርስባቸው ጫና፣ በርቀት መቆጣጠሪያ ወይም በዝንብል ብረት (ቀጥ ያለ



ስዕል 1.9
ታሳሪ ፈንጂዎች መጀመሪያ ሲነኩ 1 ሜትር ያህል ያዘሉና ሲፈነዱ በጣም የከፋ አደጋ የሚያስከትሉ።
የተመፈመአ ፎቶ/ ቶማስ ኢንኬ

**ማስታወሻ፥ የማስፈንጠሪያ ሽቦን በፍፁም አይንኩ፣ አይቁሙበት**

ማስፈንጠሪያ መሳይ) መነቃነቅ አማካኝነት በሚከሰት የማግኔት ተጽእኖ ነው። ከብርጭቆ የተሰራ ፋይበር ገመድም ትንንሽና ፀረ-ታንክ ሮኬት መተኮስ የሚችሉ የተጠመዱ ፈንጂዎችን ለማስፈንዳት ሊያገለግል ይችላል። ገመዶቹ በሁለቱም ጎን ከ2 እስከ 40 ሜትር ባለ ርቀት ድጋፍ ተተክሎላቸው ወይም ከዛፍ ላይ ተጣብቀው ሊቀመጡ ይችላሉ።፡ ፀተፊዎች ተሽከርካሪዎችን ለመደምሰስ የተሰሩ ስልሆኑ በአብዛኛው የሚገኙት በመንገዶች ላይ፣ በመንገድ ዳርቻዎች፣ በጎዳናዎች፣ እና በመንገድ ጫፍ ላይ ነው። ለተወሰነ ጊዜ ሲነዳባቸው የነበሩ ምንገዶችም ቢሆኑ ፀተፊ ሊኖርባቸው ይችላል።



ስዕል 1.10
የካናዳ ፀሰፈንጂ ሲ3ኤ2 ከሾጣጣ አደጋ አድራሽ።
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢልኬ

ፀተፈንጂዎች መጠናቸው ከፀሰፈንጂዎች በጣም ይበልጣል፤ በውስጣቸው የሚገኘው የሚፈነዳ ንጥረነገርም ከባድ ነው።ቅርጻቸውም በአብዛኛው ክብ ወይም ካሬ (ስኩዌር) ሲሆኑ መጠናቸውም ከ40 ሳሜ ዲያሜትርና 16 ሳሜ ከፍታ እስከ 23 ሳሜ ዲያሜትርና 10 ሳሜ ከፍታ ይደርሳል። የሚሠሩትም ከፕላስቲክ፣ ከእንጨት ወይም ከብረት ሆኖ ቀለማቸውም ሊለያይ ይችላል። አደጋ አድራሽ ይዘታቸው ከ6 ኪግ ከፍተኛ የሚፈነዳ ንጥረነገር ሆኖ ቅርጹም ሾጣጣ ሊሆን ይችላል።

በተጨማሪም ፀተፈንጂዎች አደጋ አድራሽ ክፍል ለተራ የሚፈነዱ እቃዎች ያገለግላል። ፊዩዙ ድብቅ ወይም ከፈንጁ ውስጥ ሊሆን ይችላል። ይህም ማለት ፊዩዝ የሌላቸውን ፈንጂዎች ለማንሳት አደገኛ ይሆናል።

መደበኛ ፀተፊዎችን እንዲፈነዱ ለማድረግ በጣም ከፍ ያለ ማለትም ከ120 እስከ 150 ኪግ የሚደርስ ጫና ይፈልጋሉ። ይህ ማለት ግን ከዚህ በታች የሚመዝኑ ሰዎች በፀተፈንጂዎች ላይ መቆም ለደህንነታቸው አያሰጋም ማለት አይደለም። ፊዩዞች ከጊዜ ብዛት የተነሳ እየላሉ ሊሄዱ ወይም ሆን ተብሎ ከሚጠበቀው ክብደት በታች እንዲፈነዱ ተደርገው ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ጊዜ ፀተፈንጂዎች በስውር መልክ ተጠምደው ገና ሲነኩ የሚፈነዱ ሊሆኑ ይችላሉ። በአንዳንድ አጋጣሚዎች ደግሞ ፀሰፈንጂዎች በፀተፈንጂዎች ላይ ሆነው ሊቀመጡና የላይኛው ሲፈነዳ የታችኛውንም እንዲያፈነዳ ሆነው ሊቀመጡ ይችላሉ። ብዙውን ጊዜ ፀሰፈንጂዎች ፀተፈንጂዎች እንዳይወገዱ ለመከላከል ጥቅም ላይ ስለሚውሉ መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ይህ ፀሰፈንጂዎችን እና ፀተፈንጂዎች አብሮ የመቅበር ቴክኒክ የተለመደ ነው።

**ማስታወሻ፣**
**ያልፈነዳ ጦር መሳሪያን ከመቅረብ፣ ከመንካትና ከመቀጥቀጥ ይታቀቡ! የሚፈነዳ መሣሪያ ሳይፈነዳ መሬት ሰርስሮ ሊገባ ስለሚችል አደገኛ እንደሆነ ሊቆይ ይችላል።**





ፀተፈንጆች የሚሰሩት እንደ ታንክ ያሉ ታላላቅ ወታደራዊ ተሽከርካሪዎችን ለማሰናከል ነው። ሆኖም በታናናሽ የሲቪል ተሽከርካሪዎች ላይ የሚኖራቸው የከፋ አደጋም አሰቃቂ የተሽከርካሪ ውድመትና የተሳፋሪዎችንም የከፋ ጉዳት ወይም ሞት ያስከትላሉ።

## 1.2 ያልፈነዱ መሣሪያዎች

ያልፈነዱ ጦር መሳሪያዎች የሚባሉት የተተኮሱ፣ የተወረወሩ ወይም ከሰማይ የተጣሉ ወይም ተተኩሰው የከሸፉ ተተኳሽ መሳሪያዎች ናቸው። የሚያጠቃልሉትም አርቲለሪና የታንክ ጥይት፣ ሞርታር ጥይቶች፣ ፊዩዞች፣ ደርማሽ ቦምቦች፣ ትንሽና ትልቅ ቦምቦች ክለስተር ጥይቶችንና ሮኬቶችን እንዲሁም ሚሳየሎችን ጭምር ነው።

### ዝንብል ብረት

ዝንብል ብረት ከፈንጁ የላይኛው ክፍል ላይ የሚገኝና ከፊዩዙ ሲስተሙ ጋር የተያያዘ ቀጭን ቋሚ ብረት ነው። በዝንብል ብረቱ ላይ የሚያርፍ ግፊት ፈንጂውን ያፈነዳዋል።

ስዕል 1.11
የአልባኒያ ኤም.ኬቲ ሞዴል 72 ፀረ-ታንክ ፈንጂዎች፣ በመጋዘን ውስጥ ሊገኙ ይችላሉ፤ ኮሶቮ 2009 (እ.ኤ.አ)።
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢልኬ



የሚፈነዱ መሣሪያዎች በብዙ ምክንያቶች ሊከሽፉ ይችላሉ፡ ፊዩዞችና ጠብቀው መለኮሻዎች ሊበላሹ፣ አለአገባብ ሊገጠሙ ወይም ርጥብ አፈር ለፍንዳታ የሚፈለገውን ነገር ሲስበው ሊከሰት ይችላል። ክሽፈቱ በምንም ምክንያት ይሁን ያልፈነዱ መሣሪያዎች ለህይወትና ለጤንነት አደገኛነታቸውን እንደጠበቁ ይኖራሉ። እንዳንድ አገሮች ባልፈነዱ የጦር መሣሪያዎች ከ150 ዓመታት በላይ ሲጠቁ ቆይተዋል።

በቦምብ በተደበደቡና ለረጂም ጊዜ ጦርነት በተካሄደባቸው ቦታዎች ብዛት ባላቸው ያልፈነዱ የጦር መሣሪያዎች ሊበከሉ ይችላሉ። ከክልስተር ተተኳሾች ለምሳሌ 30 በመቶ የሚሆኑት ስልሚከሽፉ ከግጭቱ በኋላ ለአካባቢው ለአመታት የሚዘልቅ የከፋ አደጋ ሆነው ይቆያሉ። በብዙ አገሮች ያልፈነዱ መሳሪያዎች ከፈንጂዎቹ በበለጠ በብዛት የሚገኙና ይበልጥ የተሰራጩ ሊሆኑ ይችላሉ። ያልፈነዱ የጦር መሣሪያዎች ነጻ ናቸው ተብለው በሚታሰቡ ቦታዎች እንኳን ሳይቀር የስጋት ምንጭ ሊሆኑ እንደሚችሉ ልብ ይበሉ፤ በተለይ ረጂም ጊዜ የፈጀ ጦርነት በተካሄደባቸው ቦታዎች።

ያልፈነዱ የጦር መሣሪያዎች በሥርዓት የተጠበቁ ስላልሆነ በትንሽ ንክኪ ብቻ እንኳን ሊፈነዱ ይችላሉ። ሰዎች ያልፍነዱ የጦር መሳሪያዎች ባሉባቸው አካባቢዎች በእርሻ ቦታች ላይ በሚሠሩበት ጊዜ ወይም ግንባታ በሚያከናውኑበት ጊዜ ሲነኳቸው፣ ሲንቀሳቅሷቸው ወይም ሲቀጠቅጧቸው ሊፈነዱና አደጋ ሊያደርሱ ይችላሉ። አንዳንድ ያልፈነዱ መሣሪየዎች በእንቅስቃሴ ወይም በማግኔት ሃይል ምክንያት የሚለቁ ፤ ሌሎች ደግሞ በራሳቸው ጊዜ የሚበላሹ ሆነው በመሠራታቸው የተበላሹ ፊዩዞች ሊኖሯቸው ይችላሉ። ያልፈነዱ መሣሪያዎች ያሉበትን ሁኔታ በቀላሉ ለመወሰን ስለሚያስቸግር ምንጊዜም ቢሆን በጣም አደገኛ እንደሆኑ ተቆጥረው ከባለሙያ በቀር ማንም ቢሆን ከመንካት ወይም ከማንቀሳቀስ ሊታቀብ ይገባል። ያልፈነዱ ጦር መሣሪያዎች አደጋ ብዙ ጊዜ ከፈንጂዎች አደጋ የከፋ ነው፤ በውስጣቸው ያለው የሚፈነዳ ንጥረነገርና የፍንጣሪያቸው ይዘትም ብዙ በመሆኑ።

ያልፈነዱ ጦር መሣሪያዎች ብዙ ጊዜ የሚገኙት ውጊያ በተካሄደባቸው ቦታዎች ወይም የመሳሪያ ተኩስ ሊደርስባቸው በሚችሉ ቦታዎች ነው። መሳሪያዎቹ







ስዕል 1.12
77 ሚሜ x 229 ጥቅል 1906
ክሩፕ፣ ኤሰን/ጀርመን 1906-
ለቱርክ ጦርሃይል የተሰራ፣ ኮሶቮ።
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢንኬ

ስዕል 1.13
ያልፈነዳ የጦር መሣሪያ፤ ከአየር
የተወረወሩ ኤስ-24 ሮኬቶች፣
አፍጋኒስታን።
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢንኬ

ስዕል 1.14
አሮጌ የራስ ቁር (ልብስ) ብቻ?
እንዳያነሱት!
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢንኬ





ከህንጻ ውስጥ ወይም ውጭ ሊገኙ ይችላሉ። ከመሬት ውስጥ ሊቀበሩ ወይም ከፈረሱ ወይም ከተደረመሱ ህንጻዎች ስር ሊደበቁ ሁሉ ይችላሉ።

ያልፈነዱ ጦር መሣሪያዎች በዛፎች ላይ ተሰቅለው ወይም በቅርንጫፎችና በአጥሮች፣ እንዲሁም በቤት ውስጥ በቁሳቁሶች ላይ ተንጠልጥለው ሁሉ ሊገኙ ይችላሉ።

ያልፈነዱ መሳሪያዎች በተለያዩ አይነት ‹‹ወታደራዊ ቀለሞች›› ሊኖራቸው ይችላል። ካኪ፣ አረንጓዴ፣ ቡኒ፣ ቸኮሌት መልክ፣ ግራጫ ወይም ቀለም ሳይቀቡ ሊገኙ ይችላሉ። በአብዛኛው የሚሰሩት ከብረት ነው፣ ግን ከፕላስቲክም ሊሠሩ ይችላሉ። ለረጅም ጊዜ ያለከለላ ከቤት ውጭ ሲቆዩ ሊዝጉ፣ ቀለማቸው ሊለቅ፣ በከፊል ሊደበቁ፣ በጭቃና በአቧራ ሊከለሉና ለመለየት ሊያዳግቱ ይችላሉ። አደጋ የማያስከትሉና በጣም ትንሽ ቢመስሉም በጣም አደገኛነታቸውን እንደጠበቁ ይቆያሉ።

## 1.2.1 ደርማሽ ቦምቦች (ግሪኔድስ)

ግሪኔዶች በእጅ የሚወረወሩ፣ በጠመንጃ የሚተኮሱ ወይም በግሪኔድ መወርወሪያ የሚወረወሩ የሚፈነዱ መሣሪያዎች ናቸው። ግሪኔዶች ወዲያውኑ እንደተወረወሩ ወይም በተቀጠረ ስዓት ሊፈነዱ ይችላሉ። በሁለቱም ዘዴዎች ሊከሽፉ ይችላሉ። በጣም የተለመዱት የግሪኔድ አይነቶች ‹‹ለመከላከል›› የሚውሉ ናቸው። ነገር ግን ከነዚህ በተጨማሪ ‹‹ለማጥቃት›› የሚውሉ ብላስት ግሪኔዶች፣ ተቀጣጣይ ግሪኔዶች፣ ኬሚካላዊ ግሪኔዶች፣ ባለጋዝ ግሪኔዶች እና ባለጭስ ግሪኔዶች አሉ። ደንበኛ በእጅ ወይም በጠመንጃ የሚወረወር ግሪኔድ በ10 ሜትር ክልል ውስጥ የከፋ አደጋ የሚያስከትል ሆኖ እስከ 50 ሜትር ወይም ከዚያ በላይ አደጋ ማድረስ ይችላል።

በእጅ የሚወረወሩ ግሪኔዶች የአናናስ መሰል፣ ሲሊንደር መሰል ወይም ክብ ቅርጽ ሲኖራቸው መጠናቸው እስከ 10 ሳሜ ሆነው የአንድ ጎልማሳ የእጅ ጭብጥ ያክላሉ። ቀለማቸውም የተለያየ ነው። ባለዘንግ ግሪኔዶች የሚወረወሩበትን ርቀት ለመጨመር የሚያግዝ መያዣ ዘንግ ያላቸው ናቸው።

### ንጥል ጥናት

ካምቦዲያ በአለማችን በፈንጂ በጣም ከተጠቁ አገሮች አንዷ ናት፣ ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ ያልፈነዱ መሣሪያዎች በየመቱ የሚገድሉት ሰው በፈንጂዎች ከሚሞተው ሰው ይበልጣል። በተለይ ህጻናት ሁሉን ነገር ለማወቅ ካላቸው ጉጉትና ፍላጎት የተነሳ ለአደጋው በጣም ተጋላጭ ናቸው። በአዋቂዎች ላይ የሚደርሱት አደጋዎችም ያልፈነዱትን መሣሪያዎች በመቀጥቀጥና በመጎርጎር የሚከሰቱ ናቸው።

**ማስታወሻ፡ ፀረ-ተሸከርካሪ ፈንጂዎች ካሉ፣ ፀረ ሰው ፈንጂዎችም እንደሚኖሩ ይገምቱ።**

ግሪኔዶችን ለመስራት በብዛት አገልግሎት ላይ የሚለው ብረት ነበር። ነገር ግን የጋዝና የኬሚካል (የጭስ) ግሪኔዶች በፕላስቲክ ሊሰሩ ይችላሉ።

በጠመንጃ የሚወረወሩ ግሪኔዶች የሲሊነደር ቅርጽ ሲኖራቸው በአብዛኛው ክብ አፍናጫና በክንፍ መሰል ነገር የተጠበቁ ናቸው። በኋላቸው ምንም አይነት ማስፈንጠሪያ የላቸውም። ነገር ግን ካልተተኮሱ የኃለኛው ክፍል (ከጠመንጃው አፍ ላይ ለመተኮሻ ተብሎ በተቀመጠ) ልዩ ጥቅል ይቆረጣል። ግሪኔዶች በሁሉም አይነት ነገሮች ሊሞሉ ይችላሉ፤ ለምሳሌ በአፋኝ ጭስ፣አንጸባራቂ ነገር፣ አስለቃሽ ጭስ፣ በኃይለኛ የሚፈነዱ ንጥረ ነገሮች። በጠምንጃ የሚተኮስ ግሪኔድ ፍጥነቱ ዘገምተኛ ስልሆነ ፊዩዞቹ በጣም በቀላሉ ነው የሚለቁት፤ ስለዚህ ወደገሪኔድ መተኮሻ ተመንጃ ከመቅረብ መቆጠብ ያስፈልጋል።



ስዕል 1.15
40 ሚሜ በ46 ሚሜ የሆነ ኤም430ኤ1ኤች.ኢ..ዲ.ፒ ግሪኔድ። በአፍጋኒስታን የስለጠና ክልል የተገኘ - በሰላም ማስከበርና በማረጋጋት ላይ የተሰማሩ ወታደሮች ከማንኛውም ልምምድ በኋላ የተጠቀሙባቸውን የሚፈነዱ መሳሪያዎች ቅሪት ማስወገድ አለባቸው።

የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢልኬ

ልዩ አዳፕተር በመጠቀም በእጅ የሚወረወርን ግሪኔድ በጠመንጃ መተኮስ ይቻላል። ይህ ጉዳይ የጦርሜዳን ላማጽዳት ቅድመ-ግምገማ በሚደረግበት ጊዜ ግንዛቤ ውስጥ ሊገባ ይገባል።

በሮኬት የታገዙ እንደ ፒ.ጂ-7 ያሉ ፀረ-ታንክ ግሪኔዶች ርቀትን ለመጨመርና ለመቀነስ የሚያገለግል ተጨማሪ የሮኬት ሞተር አላቸው። እንዲህ አይነት ተተኳሾች ለብዙ አላማ የሚውሉ፣ በሰፊው የተሰራጩ፣ በብዙ ቁጥር የሚገኙ እና አይነታቸውም ብዙ ናቸው። ግሪኔድ ከፍተኛ ፍንዳታ በሚያስከትል ንጥረነገር ፣ በሚፈናጠር ነገር፣ ከፍተኛ ፍንዳታ ያለው ፀረታንክ (ሙቀት-ወይም በነዳጅና በአየር የሚቀጣጠል) ሊሰራ ይችላል። ቀላል ፀረ-ታንክ ተተኳሾች በጣም ቶሎ የሚለቅ ፊዩዝ አላቸው። እንዲሁም የተተው ወይም የተረሱ ተተኳሾች ከሮኬት ሞተር ማስነሻ ሊይዙ ይችላሉ።

ስዕል 1.16 & 1.17 >
(የሚቀጥለው ገጽ፣ የቀኝ ግርጌ)
በእጅ የሚወረወሩ አዲስና አሮጌ ግሪኔዶች፣ የቱንም ያህል ጊዜ መሬት ላይ ቢቆዩም ሊፈነዱ ይችላሉ። እነዚህ የሩሲያ ኤፍ1 እና የቀድሞዋ ዩጎዝላቪያ ኤም-50 የእጅ ግሪኔድ ናቸው።

የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢልኬ

## 1.2.2 የሞርታር ጥይቶች

የሞርታር ጥይቶች አብዛኛውን ጊዜ መርታር በሚባሉ ከ90 እስከ 170 ሳሜ በሚደርሱ ክፍት ብረቶች የሚተኮሱ ተተኳሾች ናቸው። ባለፉት ዓመታት ወሰብሰብ ያሉ የሞርታር አሰራሮች በመፈጠራቸው የሃዊትዘርና የሞርታርን ልዩነት በቀላሉ መለየት አይቻልም። ዘመናዊ ሞርታሮች በቀጥታ (በማነጣጠር)





ና በተዘዋዋሪ (ኢላማው ሳይታይ) ሊተኮሱና እንደማንኛውም መሳሪያ ሊጎርሱ ይችላሉ። የሞርታር አንዱ በጣም ልዩ ባህሪው የሞርታር ክብ ጥይቶች ከሌላ ጠመንጃና ከሃዊትዘር ያነሰ ፐሮፔላንት (ማስወንጨፊያ) መጠቀሙ ነው። የሞርታር ጥይቶች የሚጎረሱት ከቲዩቡ ኋላ ወይም ፊት (እንደየአይነቱ) ሆኖ የሚተኮሱት በየራሳቸው ማስወንጨፊያ ነው። የሞርታር ጥይቶች ብዙ ጊዜ ከፊት ሹል አፍንጫ፣ ከኋላ ደግሞ ክንፍ አላቸው። የብረት አካላቸው ከ45 ሚሜ እስከ እስካሁኑ 240 ሚሜ ዲያሜትር ወርድ እና ከ30 ሳሜ እስከ አንድ ሜትር በላይ የሚሆን ርዝመት አላቸው።[5] ለመጠቀም አመቺ በመሆናቸው፣ ዋጋቸው ርካሽ በመሆኑ እና ለማጓጓዝ ቀላል በመሆናቸው፣ ሞርታሮች በጣም በሰፊው አገልግሎት የሚሰጡ የጦር መሳሪያዎች ናቸው።



ስዕል 1.18
እርምጃዎን ይቆጣጠሩ፤ የከሸፈ በጠመንጃ የሚተኮስ ግሪኔድ። የዩጎዝላቪያ ኤም-60ፒኤች.ኢ..ኤ.ቲ- የጠመንጃ ግሪኔድ ከመሬት ጋር ተጣብቋል።

የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢለኬ

የሞርታር ቦምቦች ብዙ ጊዜ የሚሰሩት ከብረት በመሆኑ ሲገኙ የዛጉ ወይም ከእድሜ ብዛት ቀለማቸው የለቀቁ ሊሆኑ ይችላሉ። በሚያርፉበት ቦታ መሬቱን ጎድጓዳ ያደርጉታል፤ የተተኮሱበት ቦታም በግልጽ ይታወቃል። በተስተካከሉ መንገዶች ላይ ብዙ ጊዜ በኮንክሪቱና በላይኛው ንጣፍ ላይ ‹‹የተረጨበት ምልክት›› መሰል ነገር ይታያል።

[5] በጣም ትንሹ የሞርታር መሳሪያ የጣልያኑ ቢ.አር.ኤክስ.አይ.ኤ-ሞርታር ኤም-35 ባለ 45 ሚሜ ካሊበር ሲሆን፣ በጣም ትልቁ ደግሞ የጀርመን ካርል ባለ 600 ሚሜ ካሊበር ነው። ሁለቱም በአሁኑ ጊዜ ጥቅም ላይ አይውሉም። ነገር ግን የጦርነት ቅሪቶች በአውሮፓ ይገኛሉ።





ሞርታር ቦምቦች አደጋ የሚያደርሱበት ቦታ ስፋት እንደየአፈሙዛቸው ስፋት በጣም የተለያየ ነው። ከፍተኛ የሚፈነዳ ንጥረነገር ያለው ትንሽ ሞርታር አንድ መኪና የመደምሰስ ችሎታ ሲኖረው ትልልቅ ሞርታር በመቦች ደገሞ ከትንሽ እስከመካከለኛ መጠን ያላቸው ህንጻዎችን የመደምሰስ ችሎታ አላቸው። ከከፍተኛ የሚፈነዳ ነገር በተጨማሪ ሞርታሮች በአፋኝ ጭስና ባንጸባራቂ ነገሮች እንዲሁም በብናኝና በቦምብ ዱቄት ሊሞሉ ይችላሉ። ዘመናዊ የሞርታር ጥይት በኤሊክትሪክ በመቅረባቸው እንዲፈነዱ የሚያደርግ ወይም በፍጥነት ሊለቅ በሚችል ፊዩዝ ሊገጠምላቸው ይችላል። እንዲሁም ራስ-መር ፀረ-ታንክ ሞርታሮችም ጥቅም ላይ እየዋሉ ነው።[6]

ያልፈነዱ የሞርታር ጥይቶች ማስፈንጠሪያ ቻርጅና ከላይ የተገለጹት ነገሮችን ሊይዝ ይችላል። የሞርታር ጥይቶች በጭራሽ ሊቀረቡ አይገባም። ሞርታሮች ብዙ ጊዜ የሚተኩሷቸው ሰዎች ኢላማዎችን ሳያዩ ስለሚተኩሷቸው በተዘዋዋሪ የሚተኮሱ መሳሪያዎች ናቸው። በዚህም ምክንያት ወዴት አቅጣጫ እንደተተኮሰ ስለማይታወቅ ያልፈነዱ የሞርታር ጥይቶች ውጊያ በተካሄደባቸው ቦታዎች ሁሉ ተበታትነው ሊገኙ ይችላሉ። ያልፈነዱ ወይም የተተው የሞርታር ጥይቶች ተራ የሚፈነዱ እቃዎችን ለመስራትም ሊያገለግሉ ይችላሉ።

## 1.2.3 ክለስተር ጥይቶች፣ ጥይቶችና ቦምቦች

የክለስተር ተኳሾች ላይ ስምምነት ለመድረስ በተደረገው ዲፕሎማሲያዊ ኮንፈረንስ ውሳኔ መሠረት[7]፣ ክላስተር ተተኳሽ ማለት እያንዳንዳቸው ከ20 ኪሎግራም በታች የሚሆኑ የሚፈነዱ ጥይቶችን የሚወረውሩ ወይም የሚተኩሱ መሳሪያዎችና የነሱ ጥይቶችን የሚያጠቃልል ነው። ከዚህ በታች የቀረቡትን ግን አያጠቃልልም፥

- እሳት(ነበልባል)፣ ጭስ፣ገለባ የሚያወጡ መሳሪያዎችንና ጥይቶቻቸውን፣
- ለአየር መቃወሚያ ብቻ ተብለው የተሰሩ መሣሪያዎች፣





ስዕል 1.19
በብረት ለበስ ተዋጊ ተሽከርካሪ ላይ የተተው ሁለት ባለ 82ሚሜ ኃይለኛ የሚፈነ ንጥረነገር ኦ-832ዲ የሞርታር ጥይቶች።
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢንኬ

ስዕል 1.20
የክለስተር ቦምብ ንጣይ ሲቢዩ-87። በአንዳንድ ምድቦች ስር እስከ 800 የሚደርሱ ተተኳሾች ሊካተቱ ይችላሉ።
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢንኬ

[6] ምሳሌ 120 ሚሜ ኢንች.ኢ.ኤ.ቲ ሞርታር ጥይት።
[7] የክለስተርበተተኳሾች ላይ ስምምነት ለመድረስ የተደረገ ዲፕሎማሲያዊ ኮንፈረንስ፣ ደብሊን፣ ግንቦት 19-30 2008 እ.ኤ.አ.



1.2 ያልፈነዱ መሣሪያዎች
1.2.3 ክላስተር ተተኳሾች፣ ተተኳሾችና ቦምቦች

- ኤሌክትሪክ ወይም የኤሌክትሮኒክ ውጤት የሚፈጥሩ መሣሪያዎችና የነሱ ጥይቶች፣
- ቦታ ሳይለዩ በመደዳ ብቻ ጥቃትእንዳይደርስ ወይም ባልፈነዱ ተተኳሾች ምክንያት የሚደርስን ጉዳት ለመከላከል ሲባል የሚከተሉት ባህርያት ያሉዋቸው መሳሪያዎች፥
  - እያንዳንዱ መሣሪያ ከአስር የማይበልጡ የሚፈነዱ ጥይቶችን የሚይዝ ከሆነ፣
  - እያንዳንዱ የሚፈነዳ ተተኳሽ ከአራት ኪሎግራም በላይ የሚመዝን ከሆነ፣
  - እያንዳንዱ ተተኳሽ ነጠላ ኢላማን ነጥሎ ለማግኘትና ለማጥቃት የተሰረ ከሆነ፣
  - እያንዳነዱ የሚፈነዳ ተተኳሽ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ (መካኒዝም) በራሱ የሚፈነዳ ከሆነ፣
  - እያንዳነዱ የሚፈነዳ ተተኳሽ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በራሱ የሚነሳ ከሆነ።

ተተከዋሾችና የቦምብ ፍሬዎች ኢላማቸውን ወደሚመቱበት ቦታ የሚደርሱት በክለስተር ቦምቦች፣ በአርቲለሪ ሮኬቶች፣ በአርቲለሪ ጎራሾች አማካኝነት ነው። እነዚህ ተሸካሚዎች ኢላማቸው ወዳለበት ቦታ ሲሄዱ በአየር ላይ ሳሉ ይፈነዱና ተተኳሾቹ በሰፊ ቦታ ላይ ይበተናሉ። ተተኳሾች ፀረ-ሰው ፈንጂዎች፣ እሳት የሚተፉ ቦምቦች ወይም በተለያዩ ነገሮች የተሞሉ ትንንሽ ፈንጂዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ተተኳሾች እንደ ቴኒስ ኳስ፣ ቢራቢሮዎች ወይም የመጠጫ ቆርቆሮዎች ያሉ የተለያዩ ቅርጾችና ቀለሞች ሊኖራቸው ይችላል። በአብዛኛው ደማቅ ቀለም ያላቸው ናቸው።

ካልፈነዱ መሣሪያዎች መካከል፣ ተተኳሾች ብዙ ቦታ የተሰራጩ እና በቀላሉ የሚፈነዱ በመሆናቸው በጣም አደገኛ ስጋት ፈጣሪዎች ናቸው። ተተኳሾች ብዙ ጊዜ ስለሚከሽፉ ለብዙ ዓመታት የስጋት ምንጭ ሆነው ይቆያሉ። የክሽፈታቸው መጠንም ከአምስት እስከ ሰላሳ በመቶ እንደሆነ ከብዙ ጦር ሜዳዎች ከተደረገ ሪፖርት ተገምቷል። ይህ መጠን በተለያዩ ምክንያቶች ይወሰናል። ግን እንደአጠቃላይ የሚያርፍበት መሬት ለስላሳ በሆነ ቁጥር የመክሸፍ እድላቸው

### ንጥል ጥናት

በ2006 እስራኤል በሊባኖስ ካሉት ከሂዝቦላህ ተዋጊዎች ጋር ስትዋጋ በክለስተር መሳሪያዎች በመጠቀሟ አለምአቀፍ ወቀሳ አድርሶባታል። እስራኤል ከ34ቱ የውጊያ ቀናት በተለይ በመጀመሪያዎቹ ሶስት ቀናት ብዛት ያላቸው ክለስተር መሳሪያዎችን እንደተኮሰች ይነገራል። ሪፖርቶች እንደሚያመለክቱት ሂዞቦላህ 113 የሚደርሱ ክለስተር ሮኬቶችን ወደሰሜን እስራኤል የተኮሰ ሲሆን እስራኤል ደግሞ በበኩሏ 26 በመቶ የሚሆነውን የደቡባዊ ሊባኖስ የእርሻ መሬት ያጠቃና 13 ስኩዌር ማይል የሚደርስ መሬት ባልፈነዱ መሳሪያዎች እንደተበከለ ነው። አንድ ሪፖርት እንደጠቀሰው ከእስራኤል ክለስተር መሳሪያዎች እስከ70 በመቶ የሚሆኑት ሳይፈነዱ የከሸፉ ነበሩ።[8]

[8] ክለስተር ተኳሾች፡የኋላ ታሪክና ምንነታቸው፣ አነድሪው ፌከርት፣ የምድር ቶር ስፔሺያሊስት፣ ፓውል ኬ. ኬር ያልፈነዱ ነገሮች ተንታኝ ሚያዝያ 29፣ 2014 እ.ኤ.አ.።

ከፍተኛ ነው። ያልፈነዳ ተተኳሽ በትንሽ ንክኪ ሊፈነዳ የሚችል ነው። ይህ መሳሪያ በጣም አደገኛ በመሆኑ ማንም ሰው ሊጠነቀቀው የሚገባ ነው። ከመሬት ስር ወይም በላይ እንዲሁም በህንጻዎች ስር ሊገኝ ይችላል። አንዳንዴ በዛፎችና በአጥሮች እንዲሁም በህንጻዎች ጣሪያ ላይ ተሰቅሎ ሊገኝ ይችላል።

አንድ ቦታ በተተኳሽ መሳሪያዎች ኢላማ ተደርጎ ከነበረ፤ ይህን የሚያሳዩ ምልክቶች ማለትም የማሸጊያ መሳሪያዎች፣ ትንንሹ ፓራሹቶች ወይም በጣም ግልጽ የሆኑ ‹‹መሳሪያው ያረፈባቸው ምልክቶች›› በመሬት ወይም በህንዎች ላይ ይታያሉ። በተጨማሪም ማንኛውም በቦታው የሚገኝ ዛፍ ቅርንጫፎቹና ቅጠሎቹ ረግፈው ይታያል። ገላጣ በሆኑ ቦታዎች ላይ መሬቱ በርካታ ጉድጓዶች ይኖሩታል። በዛ ያለ እንደ ብረትና የፕላስቲክ ልባስ የመሰለ የተተወ ውድዳቂ እንዲሁም ትንንሽ ፓራሹቶች እና የኢላማው ውድቅዳቂዎች ይታያሉ።

## 1.2.4 ሮኬቶችና ሚሳይሎች

ሮኬት ወይም ሚሳይል የሚባለው የሚፈነዳ መሳሪያ ለማስነሻ የሚሆን የራሱ ሞተርና የሚፈነዳ ንጥረነገር ወይም ተሞይ (ፍንዳታ የሚፈጥር አካል) ያለው ነው። ሚሳይሎች ከሮኬቶች ጋር ተመሳሳይ ናቸው፣ ሲተኮሱ የሚጓዙበት መንገድ የተወሰነላቸው ቢሆኑም። ሮኬቶችና ሚሳይሎች ከተሽከርካሪ ላይ፣ መሬት ላይ ባሉ ላውነቸሮች ወይም ከትከሻ ላይ ሊተኮሱ ይችላሉ። ከአየር ላይ፣ ከመርከብ ወይም በባህር ውስጥ ከሚሄድ መርከብ ሊተኮሱም ይችላሉ። ሮኬቶችና ሚሳይሎች ከፍተኛ የሚፈነዱ መሣሪያዎችን ወይም በመንኮራኩር የሚጫኑ ተተኳሾችን ፤ በራሪ ጥይቶችን፣ ኬሚካላዊ ወይም ባዮሎጂካዊ መሳያዎችን ከሌሎች መሳሪያች በበለጠ ብቃት በረጅም ርቀትና ኢላማ ሳይስት ለመምታት ያገለግላሉ። የሮኬቶችና የሚሳይሎች ኃይለኛ የሚፈነዳ ንጥረነገር አደጋ የሚያደርስበት ቦታ ስፋት እንደ የተተኳሽ ተፈጥሮ በጣም ይለያያል፤ ሆኖም ሮኬቶችና ሚሳይሎች በጣም ከፍ ያለና ተሽከርካሪዎችና፣ ህንጻዎችን፣እንዲሁም አንድ መንደር ሙሉ በሙሉ የማውደም አቅም ያላቸው ናቸው።

ሮኬቶችና ሚሳይሎች በተለያየ ቅርጽና መጠን ይሰራሉ፥ አንጻረዊ በሆነ መልክ ትንሽ ከሚባለው ከአየር ወደ መሬት ከሚወረወረውና 80 ሳሜ







ስዕል 1.21
**የተለያዩ ያልፈነዱ ተተኳሾች። በጣም ያለጸና ቢ.ኤል.ዩ-97፣ ዲ.ኤም 1385፣ ፒ.ቲ.ኤ.ቢ-2.5 ኬ.ኦ. ።**
ተመፈመአ ፎቶዎች/ቶማስ ኢንኬ





አካባቢ ከሚሆነው ኤስ-5 በጣም ትልቅ እስከሆኑትና ከ15 ሜትር የሚበልጥ ርዝመት እስካላቸው የሚሳይል መሳሪያዎች ይደርሳል፤ ለምሳሌ 16.5 ሜትር እንደሚረዝመው አር.ኤስ.ዲ-10/ኤስ.ኤስ-20 ያሉ አሉ። ሮኬቶችና ሚሳይሎች የሚሰሩት ከብረት ሆኖ በብዛት የሚታወቁት ረዥም በሆነው ሲሊነደር መሳይ ቀጭን ረጅም ቅርጻቸው ነው። ሮኬት/ሚሳይል የሚጠሩት በዲያሜትራቸው ነው። ለምሳሌ፣ 122ሚሜ ቢ.ኤም-21 ሮኬት 122 ሚሜ ዲያሜትር አለው ግን እንደየአይነቱ 2.87 ሜትር ወይም ከዚህ በላይ ሊረዝሙ ይችላሉ።

ያልፈነዳ ሮኬት እና ሚሳይል በጣም አደገኞች ናቸው። ከተነካኩ ያላለቀውን የሮኬት ነዳጅ እንደገና እንዲለኮስ በማድረግ ሮኬቱን በዘፈቀደ አቅጣጫ ሊያበረው ይችላል። የተሞላው የፍንዳታ ኃይል ካለተጎዳ የፍንዳታው ኃይል ሮኬቱ ወይም ሚሳይሉ በመጀመሪያ ሲተኮስ ከነበረው ኃይል ጋር እኩል ነው፤ ሮኬቱ ወይም ሚሳይሉ አስቀድሞ ያልተተኮሰ ከሆነና በኋላ ላይ በሙሉ ሀይሉ ከፈነዳ ግን ከሚተኮስበት ጊዜ ከሚኖረው ኃይል የበለጠ ሊሆን ይችላል።

የሮኬት ነዳጅ በጣም አሲዳም፣ ቶሎ ተቀጣጣይ ስለሆነ የተጋለጠ ቆዳን ያቃጥላል፣ ጭሱን ሰዎች ወደሳንባቸው ከሳቡት ሊገድል ይችላል። የሮኬት ነዳጅ እሳት ካገኘው ሊፈነዳ ሁሉ ይችላል። አንዳንድ የነዳጅ አይነቶች አየር በማግኘታቸው ብቻ በራሳቸው ሊቀጣጠሉ ይችላሉ። በነዚህ ምክንያቶች ማንም ቢሆን ወደ ሮኬቶችና ወደሚሳይሎች መቅረብ የለበትም።

የፈነዱ ሮኬቶችና ሚሳይሎች መንገድ ለመምራትና የአይ.አር-ፈላጊውን የሚያቀዘቅዝ የታመቀ ጋዝ የተሞሉ የጋዝ ጠርሙሶች ሊኖራቸው ይችላል። በተጨማሪም መንገድ ለመምራትና መሳሪያ ለማቀባበል አደገኛ የሆኑ ፓይሮቴክኒክ ዕቃዎችም ሊኖሩ ይችላሉ።

ያልፈነዱ ሮኬቶችና ሚሳይሎች (ብዙ ጊዜ ወደትንንሽ ክፍሎች የተሰበሩት) በስስ ቅርጻቸው አማካኝነት የተሰበረ ቧንቧ መስለው ሊያሳስቱ ይችላሉ። በከባድ መሣሪያ እና በቴክኖሎጂ በበለጸጉ ኃይሎች በተደረጉ በአንዳንድ ግጭቶች ያልፈነዱ ሮኬቶችና ሚሳይሎች መጠናቸው ትልቅ ይሆናል፣ እንዲህ አይነት አጋጣሚዎች አልፎአልፎ የሚከሰቱ ቢሆኑም።







ስዕል 1.22
**ሁለት 122 ሚሜ ኃይለኛ ፍንዳታ ሮኬቶች 9ኤም.22ዩ በአፍጋኒስታን መንደር እንደተቀመጠ።**
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢንኬ

ስዕል 1.23
**የፈነዳ ፀረ-ታንክ ሚሳይል ቢ..ጂ.ኤም- 71 ኤ/ቲ.ኦ.ደብሊዩ-1ቢ። ይህ ቁራጭ እንደተሞላ የጋዝ ጠርሙስ አይነት አደገኛ ነገሮች ይይዛል።**
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢንኬ

ስዕል 1.24
**ይህ በኢራቅ ጥናት ላይ እንደተጠራው የኤስ-75 ድዊና/ ኤስ.ኤ-2. ሚሳይል ነው።**
የተመ ፎቶ

## 1.2.5 የጠመንጃ ጥይት

በአሁኑ ጊዜ ይህ ጥይት ከ20 እስከ 203 ሚሜ (8 ኢንች) የሚደርስ አፈሙዝ ላላቸው መሳሪያዎች ያገለግላል። በድሮ ጊዜ እስከ 80 ሳሜ የሚደርሱ ሰፋፊ አፈሙዞች በጥቅም ላይ ይውሉ ነበር።[9] እነዚህም እንደ አርቲለሪ ሀዊተዘር፣ ፀረ-አውሮፕላን ጠመንጃዎች፣ የታንክ ጠመንጃዎች ወይም ተራ ጠመንጃዎች ላሉ የተለያዩ አላማዎች ላሏቸው ጠመንጃዎች ያገለግላሉ።

የአርቲለሪ ጥይቶች ለረጂም ርቀት (ከ100 ኪሜ በላይ) ለመተኮስ የተሠሩና በአየር ላይ እያሉ ወይም በሚያርፉበት ጊዜ የሚፈነዱ መሳሪያዎች ናቸው። የአርቲለሪ ጥይቶች ከመሬት፣ ከባህር እንዲሁም ከአየር[10] ላይ በተተከሉ መሳሪያዎች ሊተኮሱ ይችላሉ። አርቲለሪዎች በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ሊተኮሱ ይችላሉ፣ ግን በኢላማው ርቀት ምክንያት የሚተኩሱት ሰዎች ኢላማቸውን ማየት አይችሉም። የአርቲለሪ ጥይት የማጥቃት አቅም እንደየመጠናቸው ይወሰናል።

የታንክ ጥይት መተኮሻዎች በአብዛኛው ታንክን፣ የመሬት ውስጥ መከላከያዎችን ወይም በሜዳ ላይ ያሉ ወታደሮችን ለመደምሰስ ታስበው የሚሰሩ መሣሪያዎች ናቸው። የታንክ ጥይቶች በዋናነት በቀጥታ (ወደኢላማ)የሚተኮሱ ናቸው፤ ግን ከኢላማው በጣም ለራቀ ኢላማ በተዘዋዋሪ ሊተኮሱ ይችላሉ።

የአርቲለሪና የታንክ ጥይቶች እንደሌሎች ትላልቅ ጥይቶች በኤሮዳናሚክ ቅርጽ የተሰጣቸው ሆነው አፍንጫቸው ሹል፣ አካላቸውሲሊንደር እና ስራቸው ደግሞ ጠፍጣፋ ነው። አብዛኞቹ ከብረት የተሰሩ ናቸው። የታንክ ጥይቶች ከመተኮሻቸው የኋላ ክፍል አፍንጫው ላይ ያለውን ፊዩዝ ለመውጋት የሚያገለግል ፊን የሚባል መዉጊያ ስክ ብረት (ፊን) ሊኖራቸው ይችላል።

[9] የጀርመን ምድር ባቡር ጠመንጃ ዲ.አ.አር.ኤ፣ በ2ኛው የዓለም ጦርነት ያገለገለ
[10] ኤ.ሲ.,130 ስፔክትር ባለ 105 ሚሜ ሃዊትዘር (ዩ.ኤስ.ኤ)

### ንጥል ጥናት

**በ2003 በባግዳድ ከመሬት ወደ አየር የሚተኮሱ 100 አሮጌ የተተው የሶቪት ሚሳይሎች ተገኝተዋል። በመኪና ተሳቢ ላይ ተቀምጠው 11 ሜትር ያህል የሚሆኑት እንዚህ የሚሳይል ተሳቢ መኪናዎች በአካባቢው ሰዎች ለዝርፊያ ተጋልጠው ነበር። ህጻናት ተለያዩ ቦታዎች ሲጫወቱባቸው ተገኝተዋል። እጅግ በጣም አደገኛ ቃጠሎ የሚያስከትለው ማስወንጨፊያ አንድ ህጻን አቃጥሏል። ሁሉት ምሳይሎችም በተደጋጋሚ በመቀጥቀጣቸው ምክንያት መንደዳቸው ተዘግቧል። አንዱ ደግሞ ሶስት ያህል ቤቶችን ደምስሶ በርካታ ሰዎችን ገድሏል። ከዚህ ጥፋት በተጨማሪም ሚሳይሉ ሙሉ በሙሉ ስለነደደ መጀመሪያ ቢተኮስ ሊፈጥረው ከሚችለው አምስት እጥፍ የመነን ፍንዳታ አስከትሏል።**

የኢራቅ ኤስ.ኤ-2 ሚሳይል ሪፖርት፣ ሄስ አር. ፣ የዐለም ምግብ ፕሮግራም ማናጀር/ የኤፍ.ኤስ.ዲ የፈንጅ መከላከል ግብረኃይል፣ ባግዳድ፣ ኢራቅ፣ 2003





በጠመንጃው አሰራርና አላማ ምክንያት ጥይቶችና ማስወንጨፊያው ለየብቻ ሊገጠሙ (ሊጎረሱ) ወይም በካርታ(በማቀፊያ) ሆነው ሊሰኩ ይችላሉ። ያልፈነዱ ጥይቶች ከመሬት በላይ ወይም በውስጥ ወይም በውድቅዳቂ ውስጥ ሊገኙ ይችላሉ፤ እንደሌሎች ያልፈነዱ መሣሪያዎች ሁሉ በጊዜ ብዛት ሊዝጉና ቀለማቸው ሊለቅ ይችላል ፤መለየት ሊዳግቱ ይችላሉ። አብዛኞቹ ጥይቶች ኃይለኛ የሚፈነዱ ንጥረነገሮች አሏቸው፤ የተወሰኑት ግን ነጭ ፎስፈረስ ወይም ኬሚካላዊና በዮሎጂካዊ መሳሪያ ሊኖራቸው ይችላል። የአርቲለሪ ጥይቶች እንደ ቦምብ ያሉ መሣሪያዎችንም ሊይዙ ይችላሉ። የታንክ ጥይቶች አገልግሎቱን ከጨረሰ ዩራኒየምም ሊሰሩ ይችላሉ።

ያልፈነዱ ጦር መሣሪያዎች ስለሚመዘገዙ መሬት ላይ በሚያርፉበት ጊዜ አብዛኛው ቀለማቸው ሊለቅ ይችላል። ዝገትና አቧራ ደግሞ ከጥይት ይልቅ ድንጋይ እንዲመስሉ ያደርጋቸዋል። ስለዚህ የሚጠረጠርን ነገር ሁሉ አይንኩ።

ያልፈነዱ ወይም የተተው የአርቲለሪ ጥይቶች ተራ የሚፈነዱ እቃዎችን ለመስራት ሊውሉ ይችላሉ።



ስዕል 1.25
የእንግሊዝ የ2ኛው የአለም ጦርነት ባለ12,000 ግራም ባለ ኃይለኛ ፍንዳታ ቦምብ። ከጀርመን ግድብ አጠገብ የተገኘ።
የተመረመእ ፎቶ/ቶማስ ኢልኬ.

ስዕል 1.26
(ከታች) የአርቲለሪ ጥይትና የታንክ ጥይት ምሳሌዎች።
የተመረመእ ፎቶ/ቶማስ ኢልኬ.





## 1.2.6 ቦምቦች

ቦምብ የሚባለው ብዙ ጊዜ ከአየር የሚወረወር የሚፈነዳ መሣሪያ ነው፤ ሆኖም የአርቲለሪ ሮኬቶች ተተኳሽ ሆኖ ሊቀየርም ይችላል።" ቦምቦች የተለያየ ቅርጽና መጠን አላቸው።

ቦምቦች ብዙ ጊዜ የሚሠሩት ከብረት ሲሆን ለስላሳና ከርቭ ናቸው። ቅርጻቸውም ልስስ (ኤሮዳይናሚክ) ነው። ከአየር የሚወረወሩ ቦምቦች መጠናቸው ከ 25 ኪ.ግ. እስከ 5000 ኪ.ግ. የሚደርስ ሲሆን ሦስት ሜትር ከግማሽ (12 ጫማ) የሚደርስ ርዝመት ሊኖራቸው ይችላል። ቀለማቸው ብዙውን ጊዜ ግራጭ፣ አረንጓዴ ወይም ቡኒ ነው። ቦምቦች አብዛኛውን ጊዜ ኃይለኛ የሚፈነዳ ንጥረ ነገር ይኖራቸዋል። ሆኖም ሌሎች ነገሮች ለምሳሌ የብርሃን ነፀብራቅ ፈጣሪ ነገሮች፣ ኬሚካል ውህዶች፣ ነጭ ፎስፈረስ የቦምብ መሥሪያ ሊሆኑ ይችላሉ።

እንደሌሎቹ የሚፈነዱ መሣሪያዎች ሁሉ ቦምቦችም በእድሜ እና ለሌሎች ንጥረነገሮች በመጋለጥ ያረጃሉ። ሊዝጉ፣ ቀለማቸውን ሊለቅ እንዲሁም በከፊል ሊቀበሩና በቆሻሻ ወይም በውድቅዳቂ ነገር ሊሸፈኑ ይችላሉ።

በተለምዶ ቦምብ የተወረወረባቸው ቦታዎች ምልክቶች መሬት ላይ የሚታዩ ጉድጓዶች ናቸው። ያልፈነዱ ቦምቦች በመሬት ላይ ወይም ውስጥ ሊገኙ ይችላሉ። ሳይፈነዱ እስከ 35 ሜትር ጥልቀት ሰርስረው መግባት ይችላሉ።

### ንጥል ጥናት

ከ2ኛው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ ጀምሮ በጀርመን ሀገር ከ100,000 በላይ የሚሆኑ ቦንቦች ይገኛሉ። ብዙ ጊዜ ቦምቦቹ ከ250 ኪ.ግ. በላይ ናቸው። አንዳንድ ቦምቦች ከዚህም በጣም ይበልጣሉ። 10 ቶን የሚመዝን ክብደት ያላቸው ቦምቦች ድልድዮችንና ምሽጎችን ለመደምሰስ ውለዋል።
በሺዎች የሚቆጠሩ ቦምቦች መሬት ጠልቀው በመግባታቸው ለዓመታት ሳይታወቅ ቆይተዋል።
በአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እና የምርመራ ስዕሎችና ካርታዎች በ የዐመቱ አዳዲስ ቦምቦች ይገኛሉ። በአሁኑ ጊዜ 5,500 ቦምቦች በየዐመቱ እየተገኙ ይወገዳሉ።

" ከ50 እስከ 500 ፓውንድ የሚደርሱ ቦምቦች ያሏቸው ኬ.አር.ኢ.ኤም.ኤ 1፣ ኬ.አር.ኢ.ኤም.ኤ 2፣ ኬ.አር.ኢ.ኤም.ኤ4።





## 1.2.7 ፊዩዞች

ፊዩዝ የጥይት ዋና ተግባራዊ ኣካል ሆኖ እንዲተኮስ ወይ እንዲያደርግ የተፈጠረበትን መተግበር የሚያስችለው ኣካል ነው።

ዋና ዋናዎች የፊዩዝ አይነቶችም የሚከተሉት ናቸው፥

- የምት ፊዩዝ
- የጊዜ ፊዩዝ
- የቅርበት ፊዩዝ።

ፊዩዞች ራሳቸውን የሚደመስሱበት ስርዓት ሊኖራቸው ወይም ላይኖራቸው ይችላል። ብዙ አይነት የተለያዩ ፊዩዞች ጥምረት ሊጣመሩ ይችላሉ። ለምሳሌ የጊዜና የምት ፊዩዞች በአንድ ላይ ሊገኙ ይላሉ።

ፊዩዞች በማንኛውም ተተኳሽ መሳሪያ ውስጥ በሚታሸጉ ንጥረነገሮች ላይ ይገጠማሉ። የአርቲለሪው ወይም የሞርታር ጥይቱ ጫፍ ወይም ‹‹አፍንጫ›› ሆነው ፤ የኮን (ሹል) ቅርጽ ይዘው ይገጠማሉ። ምርድ-ሰርሳሪ ፊዩዞች ስርስረው በሚገቡ እንደ ስርሳሪ ቦምብ ወይም ለፀረ-ታንክ መሳሪያዎች መሥሪያ ለሚሆኑ ደርማሽ መሳሪያዎች ውስጥ ይገጠማሉ። በሚቀበሩ ፈንጅዎች ፤ ፊዩዙ በፈንጂ የላይኛው ክፍል ወይም ከውስጥ የምትቀመጥ ትንሽ ክብ ‹‹ክዳን›› ትሆናለች። ፊዩዞች የሚታይ ስፕሪንግ ብረት ወይም ሽቦ ሊኖራቸው ይችላል።

ፊዩዝ ከተያያዘበት የሚፈነዳ መሣሪያ ወይም ጥይት ሊላቀቅና ብቻውን መሬት ላይ ወድቆ ሊገኝ ይችላል። ፊዩዝ በጣም ትንሽ፤ ግን ደግሞ በጣም አደገኛ ነው እንዲሁም ቀዛፊ ወይ ገዳይ ሊሆን ይችላል።

ፊዩዞች ትንሽ ወይም ትልቅ ሊሆኑና አሠራራቸውም በተለያዩ መርሆች ሊሆን ይችላል፦ ማለትም በመጫን፣ በመጫንና-በመልቀቅ፣ በማሽሽከርከር ወይም በማላቀቅ፣ ለብርሃን በመጋለጥ፣ ለሙቀት በመጋለጥ ወዘተ.። ፊዩዞች የተለያዩ ቀለሞችና ቅርጾች ስላሏቸው ወዲያውኑ አደገኛ ላይመስሉ ይችላሉ፤ ብዙዎቹ







ስዕል 1.27
ጥቅም ላይ ያልዋሉ (የስልጠና) ፒ-50 ኤስ.ኤች ቦምቦች፣ አፍጋኒስታን።
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢንኬ

ስዕል 1.28
የአርቲለሪና የታንክ ጥይቶች አብነት።
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢንኬ

ስዕል 1.29
በአፍጋኒስታን የተገኘ የተተወ መሣሪያ።
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢንኬ

የወታደራዊ ዕቃዎች መሆናቸው በቀላሉ ይለያሉ። ብዙውን ጊዜ ብረትና ከብረት መሠል ቀለም ያላቸው ናቸው፤ ግን አረንጓዴ፣ ቡኒ እና ሌላ ለወታደራዊ ሙያ የሚውሉ ቀለሞች ሊኖሯቸው ይችላሉ።

## 1.3 የተተወ መሣሪያ

ግጭት ተካሂዶባቸው የነበሩ ቦታዎች የትጥቅ ቋጥ፣ የመሣሪያ ማከማቻ ወይም ማጠራቀሚያ በመሆናቸው በተተው መሳሪያዎች የተሞሉ ሊሆኑ ይችላሉ። የተተወ መሳሪያ (ተመ) አገልግሎት ላይ ያልዋለ መሣሪያ ነው፤ ግን ማንም የኔ ነው ብሎ የሚቆጣጠረው ኃይል የለም። የተተወ መሳሪያ እንደ ሞርታር፣ ግሬኔድ፣ ቦምብ፣ ሮኬት፣ የአርቲለሪ ጥይቶች እና የመሳሰሉ ብዙ አይነት መሳሪያዎችን ያጠቃልላል።

እንዳንዴ በሰዎች መኖሪያ አካባቢ፣ በወታደራዊ ህንጻዎች፣ በህዝብ መገልገያ ህንጻዎች፣ በትምህርት ቤቶች፣ በመኖሪያ ቤቶች ወዘተ. አጠገብ የሚገኙ የተከማቹ መሳሪያዎች ወይም በደንብ ያልተጠበቁ የመሳሪያ ማከማቻዎች በጣም አሰቃቂ አደጋ ሊያስከትሉ ይችላሉ። በሚገባ ቁጥጥርና አያያዝ ያልተደረገላቸው መሣሪያዎች በቀላሉ ይቀጣጠሉና ድንገተኛ ፍንዳታ የሚያስከትሉ ሊሆኑ ይችላሉ። የመብረቅ መከላከያ ወይም የደህንነት ማስጠበቂያ መመሪያዎች አለመኖር፣ከፍተኛ ሙቀት እና ርጥበት የፍንዳታን ስጋት ሊጨምሩ ይችላሉ። ከእሳት የሚወጣ ኃይለኛ ሙቀትም እንዲሁ የተተወ መሳሪያን ሊያፈነዳ ይችላል። ትንንሽ የተተው መሳሪያዎች ግጭት ከቆመ ከዓመታት በኋላም ቢሆን ሊገኙ ይችላሉ። ለምሳሌ በካምቦዲያ ትንንሽ የሚፈነዱ መሣሪያዎች ክምችት ተትተው፣ ተረስተውና ጠፍተው እየኖሩ ላለፉት 30 ዓመታት በተከታታይ ይገኛሉ።

እነዚህን ቦታዎች ነጻ ማድረግ አስፈላጊ ግን ደግሞ አስቸጋሪ ተግባር ነው። ብዛታቸው ከፍተኛ የሆኑ የተተው መሳሪያዎችን ማስወገድ በጣም ውስብስብ የሆነ የወታደራዊ ኃይሎች ተዘውታሪ ኃላፊነት ነው። ይህ ስራ ከመደበኛ የፈንጂ ማመክን ፕሮግራም ኃላፊነት ውጭ ሊሆን ይችላል።





ስዕል 1.30
የተተወ 122 ሚሜ ሮኬት ለወነቸር፤ በከፊል የተቀባበለ፤ አፍጋኒስታን።
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢንኬ

ስዕል 1.31
ቀላል የጦር መሳሪያዎች በደቡብ ሱዳን የትምህርት ስጋት ሆነዋል።
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢንኬ





የተተው ወታደራዊ ተሽከርካሪዎች፣ መሳሪያዎች (እንደ አርቲለሪ ጠመንጃዎች እና ታንኮች ያሉ) እንዲሁም ህንጻዎች የተተዉ የሚፈነዱ መሳሪያዎች፣ በጣም በድንገት የሚፈነዱ የሮኬት ነዳጆች እና እንደ ኬሚካልና አገልግሎቱን የጨረሰ ዩራኒየም ያሉ ንጥረነገሮች ሊኖሩባቸው ይችላሉ። ከመሳሪያዎች አደገኛነት በተጨማሪ እነዚህ የመሳሪያ ክምችቶች በስውር ወጥመዶች ጥብቅ መሆናቸውም የተለመደ ነው።

## 1.4 ተራ የሚፈነዱ መሳሪያዎችና ስውር ወጥመዶቸ

ተራ የሚፈነዳ ዕቃ (ተፈዕ) በተለምዶ በቤት ውስጥ የሚዘጋጅና የሚፈነዳ ንጥረነገር በውስጡ የያዘ ሰዎችን ለመጉዳት ለመግደል፣ ንብረት ለማውደም ወይም ሽብር ለመፍጠር የሚውል ነው። ብዙ ጊዜ ያለፈነዳ የጦር ወይም የተተወ የጦር መሣሪያ ተለውጠው በተጎጂዎች በድንገት የሚያፈነዱቸው፣ በርቀት መቆጣጠሪያ (በሬዲዮ ወይም በማፈንጃ ገመድ) የሚፈነዱ ወይም በአጥፍቶ ጠፊ የሚፈነዱ ተፈዐ ለመስራት ይውላሉ።

ስውር ወጥመድ የሚባለው የሚፈነዳ ወይም የማይፈነዳ መሳሪያ ሆኖ ሆን ተብሎ አደጋ የማያደርስ የሚመስል ዕቃ ሲነካ ወይም ደህንነትን የማይጎዳ ድርጊት ለምሳሌ እንደ በር መክፈት፣ ወይም ቴሊቪዥን መክፈት ያለ ተግባር ሲፈጸም ጉዳት የሚያደርስ ነው። ስውር ወጥመድ ብዙ ጊዜ በራሱ በተጎጂው አማካኝነት አደጋ እንዲያደርስ የሚደረግ ሲሆን በአብዛኛው ተራ አቃዎችን ባልተለመደ ቦታ በማስቀመጥ የሚፈጸም ነው፤ በሌላ አነጋገር ካለቦታው በሚገኙ እቃዎች ነው የሚዘጋጀው።

ተፈዐ እና ስውር ወጥመድ ብዙ ጊዜ የሚዘጋጁት የጦር መሳሪያ ማግኘት በማይችሉ ወይም ተግባራቸው ትኩረት እንዳይሰጠው በሚፈልጉ እና የወታደራዊ ሓይሎች ተቃዋሚ በሆኑ ኃይሎች ነው። አንዳንዴ በወታደራዊም ሆነ ወታደራዊ ባልሆኑ ሰዎች ላይ አደጋ እንዲያደርሱ ተብለው በተሽከርካሪ ላይ፣ በመንገድ ዳር ወይም በግለሰብ ቤት ወዘተ. ውስጥ ይጠመዳሉ።

### ይህን ያውቃሉ?

የስውር ወጥመድ አጠቃቀም በአለማቀፍ የሰብአዊ መብ ህግ ቁጥጥር ይደረግበታል። በስምምነቱ ፐሮቶኮል ቁጥር 2 የውስን መሳሪያዎች ውል እንዚህ መሳሪያዎች ጥቅም ላይ ሊውሉ የማይችሉባቸውን ሁኔታዎች ይዘረዝርና ግጭቶ ከቆሙ በኋላ እነዚህን መሳሪያዎች ለመመዝገብና ለማስወገድ የሚፈለጉ መስፈርቶችን ያስቀምጣል።



ስዕል 1.32
ከድስት የተሰራ ተፈዕ፤ አፍጋኒስታን።
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢነኬ

በቤት ውስጥ የሚዘጋጁ የሚፈነዱ ንጥረ ነገሮች ጥቅም ላይ መዋል የተፈዕ መሳሪያዎችን ጉዳት የበለጠ ያደርገዋል፡፡ በአጠቃላይ በቤት ውስጥ የሚዘጋጁ የሚፈነዱ መሣሪያዎች ሰበቃ ሲያገኛቸው በቶሎ የሚፈነዱና ለንግድ ወይም ለወታደራዊ አገልግሎት ከሚውሉ መሳያዎች ያነሰ እድሜ አላቸው፡፡ምክንያቱም እነሱን ለመስራት የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃዎችና ለመስራት የሚያገለግሉ ተስማሚ መሳሪያዎች በኢንዱስትሪ የሚመረቱትን መሣሪያዎች የደህንነት ደረጃ ያህል ተሟልተው ስለማይገኙ ነው፡፡ ተፈዐን ወይም ስውር ወጥመድን መቅረብ፣ መንካት፣ ወይም ማፍረስ አይገባም፡፡

ከሞላ ጎደል ማንኛውም ዕቃ ስውር ወጥመድ ወይም ተፈዕ ለመሥራት ያገለግላሉ፡፡ ፈንጂዎች እንዳይወገዱ ለመከላከል ሲባል ስውር ወጥመድ ሊጠመድባቸው ይችላል፡፡ ስውር ወጥመዶችና ተፈዐ በየትኛውም ቦታ ሊገኙና ማንኛውንም ነገር መስለው ሊታዩ ይችላሉ፡፡ የሞቱ አስከሬኖች እንኳን ሳይቀሩ እነሱን ለማንሳት በሚሞክሩት ላይ አደጋ ለማድረስ ስውር ወጥመድ ሊጠመድባቸው ይችላል፡፡ ስውር ወጥመድና ተፈዕ በዋናነት እንዳይታወቁ መስለው እንዲታዩ ተደርገው ነው የሚሠሩት፡፡ የሚሰሩት ርዳታ አድራጊውን፣የዋሁንና ቀድሞ ደራሹን ለማግኘት ታስቦ ነው፡፡





ስዕል 1.33
እንዳይያዝ መከላከያ፣ ግሬኔድ ከተፈናጣሪ ዘንግ ስር ተቀምጧል፡፡ ፈንጂ አምካኙ ወይም ወታደሩ የፈንጂውን ፊዩዝ አስተካክሎ ዘንጉን ሲስብ ግሬኔዱን ያፈነዳዋል፤ ባልካንስ፡፡

ፎቶ/ጀርመን ጠር ኃይል

ስዕል 1.34
በሩን ከፍቶ ወደዚህ ክፍል የሚገባ ሰው ይህን ከገመድ ጋር የተያያዘ ግሬኔድ ያፈነዳዋል፣ ባልካንስ፡፡

ፎቶ/ጀርመን ጠር ኃይል





የሞርታር ጥይቶች ፣ የእጅ ግሬኔዶች እና ሌሎች መሣሪያዎች የተለያዩ ነገሮችን ማለትም እንደ ባዶ የጥይት ሳጥኖች፣በመሳሪያ መግጠሚያዎ፣ በንግድ እቃዎች የመሳሰሉትን በመጠቀም በግለሰቦች ሊሠራ ይችላል፡፡ በጣም የተለመዱት ግን በከፊል እንደጠብመንጃ እንደሚተኮስ ግሬኔድ እንዲሆኑ የሚሠሩ ሞሎቶብ ኮክቴሎች ናቸው፡፡ እንዳንዴ በአደገኛ ዕቃዎችን በዕለት ከዕለት በምንጠቀምባቸው ነገሮች ለይቶ ማወቅ ያስቸግራል፡፡





ስዕል 1.35
ከባዶ መያዛ ነገር የተሰራ ተራ በጠመንጃ የሚተኮስ ግሬኔድ እና በእጅ የሚወረወር ግሬኔድ፣ ባልካንስ፡፡

የተመረኢ ፎቶዎች/ቶማስ ኢልኬ

**ያልጣሉትን አያንሱ ! በመንገድ ላይ ከሚያገኟቸው ጠቃሚ መሣይ ነገሮች ይጠንቀቁ፡፡**




# ክፍል 2
# አደገኛ ቦታዎችን መለየት

ደቡብ ሱዳን
የተመአመአ ፎቶ

# የማስጠንቀቂያ ምልክቶችን መለየት

ፈንጂ የተቀበረባቸው ቦታዎች የተለዩ የማስጠንቀቂያ ምልክቶች ስላልተደረጉባቸው ፈንጂ ካልተቀበሩ ቦታዎች ተለይተው አይታወቁም። እንደ ህግ ፈንጂዎችን ማየት አይቻልም፤ ብዙ ጊዜ ስለሚቀበሩ፣ ወይም በመሬት ውስጥ ስለሚደበቁ።[12] ሌሎች የሚፈነዱ የጦርነት ቅሪቶች በግልጽ ይታያሉ፣ በመሬት ላይ በግልጽ የተጣሉ መሳሪያዎች፣ ያልፈነዱ የጦር መሳሪያዎች፣ ወዘተ. ስለሆኑ። ስውር ወጥመዶችና ተፈፅ በአብዛኛው የሚታዩ አይደሉም። ሆኖም ግን የአካባቢው ህዝብ ባህርይና በመሬት ላይ የሚቀመጡ ምልክቶችን መለየቱ አደገኛ ሊሆኑ ከሚችሉ ቦታዎች ለመቆጠብ ያግዛል። ይህ ክፍል አንባቢዎች የማስጠንቀቂያ ምልክቶችንና ጠቀሜታዎችን እንዲያውቁ ለማገዝ የተዘጋጀ ነው። በቋሚነት ጥንቃቄ ማድረግ አደገኛ ቦታዎችን ለመለየትና ለመራቅ ይረዳል።

## 2.1 የማስጠንቀቂያ ምልክቶች

ፈንጂዎችን የሚጥሉ ሰዎች ፈንጂዎች በዚያ ቦታ ስለመኖራቸው የሚያሳይ ግልጽ ምልክት አይተውም። ነገር ግን ሌላ ሰው ሌሎችን ሰዎች ለማስጠንቀቅ ጊዜያዊ ምልክት ሊያስቀምጥ ይችላል፤ ወይም ፈንጂ አጽጂ ድርጅቶች ህጋዊ የማስጠንቀቂያ ምልክቶች ሊያቆሙ ይችላሉ።

በሚኖሩበት አካባቢ በጣም የተለመዱ የማስጠንቀቂያ ምልክቶችን ሊያውቁና እነዚህን ምልክቶች በትኩረት መከታተል ይገባል። ነገር ግን ግልጽ ምልክቶች የሉም ማለት ቦታው ከፈንጂዎች፣ ካልፈነዱ የጦር መሳሪያዎች፣ ከሚፈነዱ የጦርነት ቅሪቶች፣ ከስውር ወጥመዶች ወይም ከተፈፅ ነጻ ነው ማለት አይደለም። ሰዎች አንዳንዴ ምልክቶችን ያነሷቸዋል፣ ምልክቶች ጊዜያዊ ሊሆኑ ይችላሉ፣ ተጠብቀው ሊቆዩ አይችሉም ይሆናል ወይም ከመጀመሪያውም ላይደረጉ ይችላሉ።

[12] ከክፍል 2 እስከ 3 ያሉት በመጀመሪያ የተወሰዱት ከዩናይትድ ኔሽን የፈንጂ ግንዛቤ ማስጨበጥና የማህበረሰብ አስተባባሪና የፕሮግራም ማናጀሮች፣ ዩኒሴፍ 1999፣ በዩኤንኤምኤኤስ 2015 የተሻሻለ የማስተማሪያ ሞጁሎች ነው።

### ይህን ያውቃሉ?

በበተሰኑ መሳሪያዎች አጠቃቀም ስምመነት (ሲ.ሲ.ደብሊዩ.) የፕሮቶሎ፤ ስምምነት ፕሮቶኮል 2 መሠረት ወታደራዊ ኃይሎች ፈንጂ የተበተነባቸውን ቦታዎች፣ፈንጂ የተቀበረባቸውን ስፍራዎች፣ ፈንጂዎችንና ስውር ወጥመዶችን መመዝገብ ይጠበቅባቸዋል። የፈንጂ ማዕቀብና የስምምነቱ ፕሮቶኮል 5 ደግሞ የማጽዳት ሥራ ከመካሄዱ በፊት ሊወሰዱ የሚገባቸው የምዝገባና ምልክት የማድረግ እርምጃዎችን ይዘረዝራል።














### 2.1.1 ህጋዊ የማስጠንቀቂያ ምልክቶች

አንዳንዴ በመንግስታት፣ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅተች፣ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ወይም በሌላ ድርጅት በአካባቢው ፈንጂዎች ወይም ሌሎች የሚፈነዱ አደገኛ መሳሪያዎች መኖራቸውም የሚያመለክቱ ህጋዊ ምልክቶች ተተክለው ያጋጥሙዎታል። እንዚህ የማስጠንቀቂያ ምልክቶች ከአገር አገር የተለያዩ ናቸው፣ ሆኖም በመደበኛነት ደማቅ ቀይ ሆነው ሶስት ወይም አራት መዓዘን ያላቸውና ከብረት፣ ከኮንክሪት ፣ ከእንጨት ወይም ከላስቲክ ሊሰሩ ይችላሉ። በፈንጂ ወይም በሚፈነዱ የጦር መሳሪያዎች የተጠቁ ቦታዎችን ለማመልከት የሚያገለግሉት በጣም የተለመዱት ምልከቶችም፥

- የአጽምና መስቀለኛ የሠሩ አጥንቶች ምልክት በቀይና ነጭ ቀለም፣ አልፎ አልፎ ደግሞ በቢጫና በጥቁር ፣ ተስሎ በእንግሊዝኛ ወይም በአካባበዊ ቋንቋ «አደገኛ ፈንጂዎች» “DANGER MINES” ተብሎ የተጻፈባቸው ሰሌዳዎች፤
- በእንግሊዝኛ ወይም በአካባቢው ቋንቋ «ፈንጂ» ወይም «የሚፈነዱ» የሚል ጽሁፍ፤
- ብዙ ጊዜ ቢጫ፣ ቀይ ወይም ሰማያዊ የተቀባ ገመድ ወይም የተዘረጋ ፕላስቲክ
- ቀይ ሶስት ማዕዘን፣ አንዳንዴ ጥቋቁር ነጠብጣቦች ወይም «ፈንጂ» ተብሎ መሃል ላይ የተጻፈበት፤
- ከእንጨት ወይም ከኮንክሪት የተሰራና በአንድ ጎን ቀይ በሌላ ጎን ነጭ የተቀባ ቋሚ። በቀዩ በኩል አደገኛ ቦታ መሆኑን ያመለክታል።


መደበኛ የሆነ ሠራዊት አንዳንዴ የተጠላለፈ ብረት ወይም ከፍ ያለ ቁመት ያለው አጥር በማጠር ወታደራዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ቦታዎች ፣ በተለይም እንደ አየር ማረፊያ፣ የመሳሪያ መጋዘን ያሉ ቋሚ ስትራቴጂካዊ ቦታዎችን ከሌላው ከአካባቢው ለይቶ ይጠብቃቸዋል። በተጨማሪም እነዚህ አጥሮች በፈንጂዎች ሊጠበቁ ይችላሉ።













ስዕል 2.1
ህጋዊ የፈንጂ ምልክት።

በህግ የጸደቁ ትክክለኛ ዕቃዎች በማይገኙበት ጊዜ የማስጠንቀቂያ ምልክቶች ተራ ምልክቶች ሊመስሉ ይችላሉ። ቀይ ወይም ሰማያዊ የተቀባ ድንጋይ የአደገኛ ነገር ማስጠንቀቂያ ሊሆን ይችላል።

ሁሉም የማስጠንቀቂያ ምልክቶች በጊዜ ርዝመት ምክንያት ጎልተው የመታየት አቅማቸው እየቀነሰ ሊሄድ ይችላል። ይህም ማለት በጣም አስተዋይ መሆን ይኖርብዎታል ማለት ነው። ምልክቶች ሊወድቁ፣ ሊዝጉ፣ ወይም በዕጽዋት ወይም በበረዶ (ለወራት ያህል) ሊሸፈኑ ይችላሉ።ጥራት በጎደላቸው ዕቃዎች የተሠሩ ምልክቶችም ቶሎ ሊጠፉ፣ ሊሰበሩ፣ ቀለማቸው ሊለቅ ይችላል። መተጨማሪም ምልክቶች ሊሰረቁ ወይም በሚገባ ላይጠበቁ ወይም ላይተኩ ይችላሉ።

የፈንጂ መከላከል ፕሮግራሞች የተጠላለፈ የሽቦ አጥር በመጠቀም የአካባቢውን ነዋሪዎች ወደአደገኛ ቦታዎች ከመግባት ሊጠብቁት ይገባል።

## 2.1.2 በህግ ያልጸደቁ (ተራ/ጊዜያዊ) የማስጠንቀቂያ ምልክቶች

ሰዎችን ለማስጠንቀቅ ከሚውሉ ህጋዊ ከሆኑ (በህግ ከጸደቁ) ምልክቶች በተጨማሪ መደበኛ ሠራዊትና ሌሎች ኃላፊነት ያለባቸው አካላት ቅኝት ያደረጉባቸውንና ሊያጸዷቸው ያቀዷቸውን አደገኛ ቦታዎች ለማመልከት ምልክቶች ሊጠቀሙ ይችላሉ። በአፍጋኒስታን እንዲህ አይነት ቦታዎች ከአደጋ ነጻ አለመሆናቸውን ለማሳየት ምልክት የሚደረግባቸው በድንጋዮች ነው። ቀይ ቀለም የተቀባ ድንጋይ ኣደገኛ ቦታን ሲያመለክት ነጭ ደሞ ቦታው መጽዳቱን ያመለክታል። ህንጻዎች፣ መንገዶች እና ዛፎችም ካርታ፣ የፈንጂ ቦታው መለያ ቁጥር ታክሎባቸው ቀይ ወይም ነጭ በመቀባት ቦታው አደገኛ ሊሆን እንደሚችልና ቅኝት እየተደረገበት እንደሆነ ሊያመለክቱ ይችላሉ።

ህጋዊ ምልክቶች በማይገኙበት ጊዜ የአካባቢው ነዋሪዎች የራሳቸውን ቴክኒክና ምልክቶች በመጠቀም አደገኛ ቦታዎችን ሊያመለክቱ ይችላሉ። እነዚህ







ስዕል 2.1 (የቀጠለ)
ህጋዊ የፈንጂ ምልክቶች።



ስዕል 2.2
አንዳንድ ወታደራዊ እቃዎች በፈንጂዎች አማካኝነት ይጠበቃሉ፤ ይህ በአፍጋኒስታን የሚገኝ በፈንጂ የታጠረ ቦታ ነው።
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ እነኬ



2.1 የማስጠንቀቂያ ምልክቶች
2.1.2 በህግ ያልጸደቁ (ጊዜያዊ) የማስጠንቀቂያ ምልክቶች

ቴክኒኮች ከአገር አገር፣ እንዲሁም በአንድ አገር ውስጥ ከቦታ ቦታ ይለያያሉ። በአካባቢያዊ ምልክቶች አጠቃቀም ቋሚና ወጥ የሆኑ መመሪያዎች የሉም፣ ግልጽነታቸውም ለአካባቢው ነዋሪዎች ብቻ ነው። ሆኖም እንዚህ ምልክቶች አደጋን አስቀድሞ ለማመልከት ከሚጠቀሙባቸው ከተለመዱ ምልከቶች መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፥

- የእንጨት ወይም የፕላስቲክ ቁራጭ በአጥር ላይ ማንጠልጠል፤
- በችካል ላይ ቆርቆሮ/ጣሳ መስቀል፤
- አነስተኛ የድንጋይ ክምር/ካብ፤
- መንገድን በድንጋይ ድርድር መዝጋት፤
- የሣር ችቦ በመንገዱ መሃል ላይ ማሰር፤
- በመንገዱ ላይ ወይም በመንገዱ ዳርቻ መስቀለኛ ሰርተው የቆሙ ዘንጎችን መትከል፤
- በዛፎች ቅርፊት ላይ የተቀረጹ ምልክቶች፤
- የተገነጠለ ቅርንጫፍ።

ጊዜያዊ በመሆናቸው ምክንያት፣ አካባቢያዊ ምልክቶች የስጋቱን ምንጭ ትክክለኛ መገኛ ቦታና የስጋቱን ምንጭ ትክክለኛ ተፈጥሮ በሚመለከት ፍንጭ አይሰጡም። ለምሳሌ በመንገድ ላይ እየተጓዙ እያለ እንዲህ አይነት ምልክቶች ቢያጋጥሙኝ ብለው ይገምቱ። የአደጋ ምንጭ የሆነው ነገር ከፊት ለፊትዎ ይሁን ወይስ ከአደገኛው ቦታ ውስጥ ገብተውበት ይሁን እንዴት ሊያውቁ ይችላሉ? ሌሎች ምልክቶች ይፈልጉና ከአካባቢው ነዋሪዎች ጋር ይመካከሩ። ብዙ ጊዜ እነዚህ ምልክቶች ሌሎችን ለምሳሌ እንደ ተሰበረ ድልድይ፣ በመንገድ ላይ ያለ ጉድጓድ የመሳሰሉ አደገኛ ነገሮችንም ለማመልከት ይውላሉ። የሚጠቁሙት ምንም ይሁን ምን እነዚህ አካባቢያዊ ምልክቶች አደጋ መኖሩን ስለሚጠቁሙ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል።




ስዕል 2.3
በህግ ያልጸደቁ ጊዜያዊ የፈንጂ ምልክቶች።
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢነኬ

**ፈንጂ እንዳለ የሚያመለክቱ ምልቶች፣ ሽቦዎች፣ ወይም ገመዶች ወዳሉባቸው ቦታዎች አይሂዱ! ሁሌም ቢሆን የፈንጂ ማስጠንቀቂያ ምልክቶችን ያክብሩ!**

**ስለ ፈንጅ/ፈጦቅ ወቅታዊ መረጃ ይኑርዎት።**

## 2.2 የማስጠንቀቂያ ፍንጮች

ፈንጂዎች፣ የሚፈነዱ የጦርነት ቅሪቶች (ፈጦቅ)፣ ተራ የሚፈነዱ ዕቃዎች (ተፈዐ) ውጊያ በተካሄደባቸው ወይም ለወታደራዊ ተልእኮ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ባላቸው ብዙ አይነት ቦታዎች ላይ ሊገኙ ይችላሉ። አብዛኞቹ እንዲህ አይነት አደገኛ ቦታዎች በህግ ተቀባይነት ባገኙ ምልክቶች አማካኝነት ምልክት ላይደረግባቸው ስለሚችል ቦታዎች አደገኛ ስለመሆንና አለመሆናቸው ሁሌም ቢሆን ፍንጭ መፈለግ ይኖርበዎታል። ከዚህ በታች የቀረቡት ምልከትቶች አደገኛ ቦታዎችን የሚመለከት መረጃ የሚሰጡ ናቸው፥

- በግልጽ የሚታዩ ፈንጂዎች፣ ፈጦቅ፣ ተፈዕ፤
- የውጊያና የወታደራዊ እንቅስቃሴ ምልክቶች፤
- በአካባቢ የሚታዩ ምልክቶች፣ የሞቱ እንስሳት፣ ያለተለመዱ ቁሳቁሶች፣ እና
- አካባቢያዊ ባህርይ።

### 2.2.1 በግልጽ የሚታዩ ፈንጂዎች፣ ፈጦቅ፣ ተፈዕ

#### 2.2.1.1 የተቀመሩ ፈንጂዎች ጫፍ፣ ሾልኮ የወጣ ብረት፣ እንጨት ችካሎች

ፈንጂዎች ለማየት በጣም አስቸጋሪ (ፍጹም የማይቻሉ ሊሆን ይችላሉ) ከመሆናቸው በተጨማሪ ፤ ሁሌም ማለት ይቻላል ሆን ተብሎ ተሰውረው ነው የሚቀመጡት፤ ችግሩን የበለጠ ለማወሳሰብ ብዙ ጊዜ መገኛቸው ይቀበራል፣ በረጃጅም ሳርና በጥቅጥር ቁጥቋጦ ይሸፈናል። ሆኖም ግን አንዳነድ ፈንጂዎች ቦታውን በአትኩሮት ለተመለከተ ሰው በግልጽ ሊታዩ በሚችል መልክ በመሬት ላይ በግልጽ ሊታዩ ይችላሉ። የአፈር መሸርሸር ወይም ሌሎች የተፈጥሮ ክስተቶች ፈንጂዎችን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ተጋልጠው እንዲታዩ ሊያደርጓቸው ይችላሉ። ፈንጂዎችን ሸፍኖ የነበረ በረዶም ሲቀልጥ ተመሳሳይ ውጤት አለው። ግን ልብ ይበሉ የአፈር መሸርሸርና ሌሎች ተፈጥሯዊ ክስተቶች
















**ስዕል 2.3 (የቀጠለ)**
**በህግ ያልጸደቁ ጊዜያዊ የፈንጂ ምልክቶች።**



ፈንጂዎች እንዲቀበሩ ሊያደርጉም ይችላሉ። ፈንጂ ይኖርበታል ብለው የሚጠረጥሩት ቦታ ውስጥ ነኝ ብለው ካሰቡና ከብረት ወይም ከፕላስቲክ የተሰራ ነገር አካል ካዩና አደጋ ሳያስከትል መለየት የማይቻል ከሆነ ቦታው በፈንጂ ወይም ባልፈነዱ የጦር መሳሪያዎች የተበከለ እንደሆነ ሊገምቱ ይገባል። ርዝመታቸው 30 ሳሜ የሚደርሱ የብረትና የእንጨት ችካሎችም ከመሬት በላይ ያሉ ፈንጂዎች ሊኖሩ የሚችሉበት እድል እንዳለ አመላካች ሊሆኑ ይችላሉ።

ፈንጂዎች ብዙ ጊዜ ብቻቸውን አይቀበሩም። ስለዚህ የአንድ ፈንጂ መገኘት ሌሎችም እንደሚኖሩ አመልካች ነው።

#### 2.2.1.2 የተተውና ያልፈነዱ መሳሪያዎች

ፈንጂ ከተቀበረባቸው ቦታዎች ይልቅ የተተውና ያልፈነዱ መሣሪያዎች ያሉባቸው ሥፍራዎች በግልጽ ሊታወቁ ይችላሉ። ሆኖም የነዚህ መሳሪያዎች መገኘት የፈንጂዎችንም መኖር ሊያመለክት ይችላል። የመሳሪያ መሸኛዎችን፣ ያልፈነዱ የሞርታርና የአርቲለሪ ጥይቶችና ግሪናዶች፣ ጥቅም ላይ ያልዋሉ መሳሪያዎችንና ጥይቶችን የያዙ ሳጥኖች በመሬት ላይ ወድቀው ሊታዩ ይችላሉ። እነዚህ ምልከቶች ውጊያ የመካሄዱ ምልክቶች ሲሆኑ ፈንጂዎችና የሚፈነዱ የጦርነት ቅሪቶች ሊኖሩ እንደሚችልም ያመለክታሉ።

#### 2.2.2.2 የተዘረጋ ገመድ ወይም ፕላስተር

የተወሰኑ የፈንጂ አይነቶች እንዲሁም ተፈዕ እና ስውር ወጥመዶች ሽቦ ወይም የኤሌክትሪክ ገመድ ይኖራቸዋል። ውጊያ እንደተካሄደበት በሚታወቅ ቦታ የሽቦ ቁርጥራጮችን ካዩ ፈንጂዎች፣ ተፈዐ ወይም ስውር ወጥመዶች አገልግሎት ላይ ውለው ሊሆን እንደሚችል ያመለክታሉ። ማስፈንጠሪያ ሽቦዎች ብዙ ጊዜ እግረኛ ይበዛባቸዋል ተብለው የሚገመቱ መንገዶችን፣ ጎዳናዎችንና መተላለፊያዎችን አቋርጠው ነው የሚዘረጉት። ያስታውሱ፣ ማስፈንጠሪያ ሽቦዎች ለማየት በጣም አስቸጋሪ በመሆናቸው አልታዩም ማለት በቦታው የሉም ማለት አይደለም።



**ስዕል 2.4**
**የተቸከሉ ፀረ-ሰው ፈንጂዎች አንዳንዴ በገልጽ ይታያሉ፣ ሽቦውን ልብ ይበሉ፣ ፒ.ኤም.አር.-ዩ፣ ባለካንስ።**
የተመ ፎቶ

**በተግባር የታገዘ ስልጠና እስካልወሰዱ ድረስ ምልክት ለማድረግ አይሞክሩ!**
**ሁሌም ከተለመደ <<ቦታቸው ውጭ>> ያሉ ዕቃዎች ሲያዩ ይጠርጥሩ! ከአደጋ ጋር አይጋፈጡ! ከተጠራጠሩ፣ ወደኋላ ይመለሱ!**

### 2.2.2.3 ዝንብል ብረትና ፊዩዞች

አንዳንዴ ያዘነበለ (ዝንብል) ብረቶች ወይም ፊዮዞችን ከመሬት ላይ ሊያዩ ይችላሉ። ይህም በአብዛኛው የፀረ-ተሽከርካሪ ፈንጂዎችን መኖር ያመለክታል። ነገር ግን የፀረ-ሰው ፈንጂዎችን በቦታው መኖርም ሊያመለክት ይችላል።

ፊዩዞች ከሚፈነዳው መሳሪያ ሊገነጠሉ ወይም ሳይገጣጠሙ እንዲሁ መሬት ላይ ወድቀው ሊገኙ ይችላሉ። ፊዩዝ በጣም ትንሽ ነው፤ ሆኖም ግን እስከ መግደል ድረስ አደጋ የማድረስ አቅም አለው። ፊዩዞች ውጊያንና፣ የፈንጂዎችንና የፈጠቅ መኖርና ያመለክታሉ።

### 2.2.2.4 የተጣሉ ፓኮዎች፣ መጠቅለያና የወታደራዊ እቃዎች ውድቅዳቂ

ተዋጊ ኃይሎች ፈንጂዎችን የሚጥሉት በችኮላ ስለሆነ ማሸጊያ ፓኮዎችን፣ የማስፈንጠሪያ ሽቦዎችን ጥቅልል፣ የፈንጂዎችን ጥብቅ መርፌዎች ይጥሏቸዋል። የወታደራዊ ዕቃ ምልክት ያለባቸው የእንጨት፣ የፕላስቲክ ወይም የብረት መያዣ ዕቃዎችን በመንገድ ላይ ወድቀው ካዩ ሁሌም ቢሆን በዚያ ቦታ ፈንጂ ሊኖር እንደሚችል ይጠርጥሩ። በተጨማሪም፣ ባለመርፌ ትንንሽ የብረት ቀለበቶች በቦታው ፈንጅ ለመኖሩ ምልቶች ሊሆኑ ይችላሉ። ባዶ የክለስተር ቦምብ መያዣዎችም በአካባቢው አደጋ ለመኖሩ ምልክቶች ናቸው።

**የሚፈነዱ የጦርነት ቅሪቶችን በፍጹም አይቅረቡ፣አይንኩ፣ ወይም አይቀጥቅጡ**





ስዕል 2.5
ለደህንነት አስጊ የሆነ ቦታን በግልጽ ሊያመለክት የሚችል የበ.ኤል.ዩ-97 ጥይት ልባስ።
የተመፈመአ ፎቶ. ቶማስ ኢንኬ

ስዕል 2.6
አብዛኛውን ጊዜ በዚህ በ82 ሚሜ ኤች.ኢ.83ኤል.ዲ የሞርታር ጥይት አደገኛ አካል ላይ ያልፈነዳ መሳሪያ ይታያል፤ አፍጋኒስታን።
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢንኬ

**ከተተው ወታደራዊ ቁሳቁሶች ይራቁ!**





## 2.3 የውጊያና የወታደራዊ እንቅስቃሴ ምልክቶች

### 2.3.1 ቦዮች፣ ምሽጎች፣ ጎድጓዶችና ጉድቦች

በወታደሮች ተይዘው የቆዩ ቦታዎች በተለይም ቦዮች፣ ምሽጎች፣ ጎድጓዶችና ጉድቦች ከጥቃት ለመከላከል ሲባል ፈንጂዎች የተቀበሩባቸው ሊሆኑ ይችላሉ። የተተው ወታደራዊ ቁሳቁሶች ጠላት እንዳይጠቀምባቸው ስውር ወጥመድ ሊጠመድባቸውም ይችላል። ያልፈነዱና የተተው መሳሪያዎች የመገኘታቸው እድልም እንዲሁ ሰፊ ነው።

### 2.3.2 የተጎዱ፣ የተተው ወይም የተደመሰሱ የሲቪልና ወታደራዊ ተሽከርካሪዎች

የተጎዱ፣ የተተውና የተደመሰሱ የሲቪልና ወታደራዊ ተሽከርካሪዎች፣ የፀረ-ተሽከርካሪ እንዲሁም የፀረ-ሰው ፈንጂዎች መኖራቸውን ያመለክታሉ። አንድ ፈንጂ ባለበት ቦታ፣ ብዙ ጊዜ ሌሎች ብዙ ፈንጂዎችም ይገኛሉ። የፍንዳታ ውጤት የሆኑ ቁርጥራጭ ብረቶችንና ውድውዳቂዎችን የሚያዩበት አጋጣሚም አለ። የተተው ተሽከርካሪዎች ስውር ወጥመድ ሊጠመድባቸውም ይችላል። ተሽከርካሪዎችም የተተወ መሣሪያ በውስጣቸው ፣ መርዛማ ነዳጅ ወይም የኬሚካል ዝቃጭ ሊኖርባቸው ይችላል። በእሳት አማካኝነት የደረሰ ጉዳት ካለም አገልግሎቱን በጨረሰ ዩራኒየም የተሰራ መሳሪያ መኖሩን ሊያመለክት ይችላል። የሚፈነዱ ንጥረነገሮች ቅሪትም እንዲሁ ሊኖር ይችላል።እነዚህ ሁሉ አደጋ ሊከሰት እንደሚችል ግልጽ አመላካቾች ስለሆኑ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል።

### 2.3.3 የተጣሉና የተተው መሳሪያዎች

የተጣሉ መሳሪያዎች በቦታው በቅርብ የተካሄደ ውጊያ መኖሩን የሚያመለክቱ ሲሆን እንደ ተተውና እንደተደመሰሱ ተሽከርካሪዎች ሁሉ አደገኛ ናቸው። አንዳንዴ መሳሪያዎች የተቀባበሉና ለመተኮስ የተዘጋጁ ሊሆኑ ይችላሉ።እንዲሁም መሳሪያዎቹ የተጎዱ ሊሆኑ ችላሉ። እነዚህን መሳሪያዎች ከመቅረብ ይቆጠቡ።







ስዕል 2.7
በባዶ ቤት ውስጥ፣ የተጣለ የትጥቅ ሳጥን፣ ባልካንስ።
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢንኬ

ስዕል 2.8
የተተወ ቦይ። ባለማስፈንጠሪያ ሽቦውን ፒ.ኤም.አር-ዩ ተፈናጣሪ ቦምብ ልብ ይበሉ፣ ባልካንስ።
የተመ ፎቶ

ስዕል 2.9
ውጊያ የመካሄዱ ምልክቶች፣ ባዶ የ75ሚሜ በ406 ሪኮይለስ ጠመንጃ ማቀፊያዎች፣ ባልካንስ።
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢንኬ

## 2.3.4 ወታደራዊ የቁጥጥር ኬላዎችና የድንበር አካባቢዎች

በተልዕኮ ላይ ያሉ ወታደሮች የያዙት ቦታ በሰፋ ቁጥር ራሳቸውን ለመጠበቅ ከነሱ ቅርብ የሆኑ ቦታዎች ላይ ፈንጂ የመቅበር እድላቸው ከፍተኛ ነው። በብዙ አገሮች ፈንጂ የተቀበረባቸው ቦታዎች በአለማቀፍ ፣ አንዳንዴም በአንድ አገር አስተዳራዊ ክልሎች (በአውራጃና በወረዳ)፣ ድንበር ላይ ሰርጎ ገቦችን ለመከላከል ነው። እነዚህ ቦታዎች ብዙ ጊዜ ከፈንጂ የሚጸዱ የመጨረሻዎቹ ናቸው፣ በተለይ በተጎራባች አገሮች ወይም የእርስበርስ ግጭቶች ሙሉ በሙሉ መፍትሄ ካልተገኘላቸው በቀር።

## 2.3.5 የወታደራዊ አገልግሎት ሰጪ ህንጻዎችና ማዘጋጃ ቦታዎች

ፈንጂዎች ብዙ ጊዜ የመከላከያ መሳሪያዎች ናቸው። ስለዚህ ማንኛውም ወታደሮች ያሉባቸው ወታደራዊ አገልግሎት የሚሰጡ ህንጻና ወታደራዊ ቁሳቁሶች የሚዘጋጁባቸው ቦታዎች ከጥቃት ለመከላከል ወይም አገልግሎት ከሰጡ በኋላ ለተቃራኒው ቡድን አገልግሎት እንዳይሰጡ ሲባል በፈንጂዎች ሊታጠሩ ወይም ስውር ወጥመድ ሊጠመድበቸው ይችላል። አጥሮች፣ በሮችና በካምፕ ውስጥ የሚገኙ መሠረተ-ልማቶች ማለትም እንደ የኃይል (የኤሊክትሪክ) ማመንጫ ጣቢያ ያሉት፣ የተጠናከር የፈንጂ ቀበራ የሚደረግባቸው ናቸው። በተጨማሪም እነዚህ ቦታዎች ብዛት ያላቸው የተተው መሳሪያዎች ክምችት ሊኖርባቸው ይችላል።

## 2.3.6 ድልድዮች፣ ግድቦችና አካባቢያቸው

ፈንጂዎች የተቃራኒ ኃይልን እንቅስቃሴ ለማቆም ወይም ለማዘግየትም ያገለግላሉ። ድልድዮችን፣ ግድቦችንና አካባቢያቸውን በፈንጅ ማጥመድ የተቃራኒ ኃይሎችን መንገድ በመዝጋት የሚፈልጓቸውን ጠቃሚ ነገሮች እንዳያገኙ ያደርጋል። ስለዚህ ከፍተኛ የፈንጂ ስጋት ባለበት አካባቢ በድልድዮች ዙሪያና አካባቢ በእግር አለመሄድ ጠቃሚ ነው።

ተፈዕዎች ብዙ ገዜ የሚቀመጡት ‹‹ተጋላጭ ቦታዎች›› ተብለው በሚጠሩ







**ስዕል 2.10**
**የተተወ ዋና የውጊያ ታንክ፤አደጋ አያደርስም? አፍጋኒስታን።**
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢንኬ

**ስዕል 2.11**
**ይህ መመልከቻ ቦታ በፈንጂ ሊከበብ ይችላል።**
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢንኬ

**ስዕል 2.12**
**ልብ ይበሉ፤ ወታደራዊ አቅርቦቶች በአጥርና በሌላም ነገር ሊጠበቁ ጥችላሉ። የቀድሞዋ ዩጎዝላቪያ።**
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢንኬ





ስፍራዎች ነው። እነዚህ ቦታዎች አንዳንዴ ‹‹ፍጥነት የሚቀነስባቸው ቦታዎች›› ተብለውም ይታወቃሉ። ድልድዮች ብዙ ፍጥነት የሚቀነስባቸው ቦታዎች ናቸው። ድልድዮች ለብዙ የሚፈነዱ መሳሪያዎች የሚሆን ሰፊ ቦታና ለምልክቶች የሚያገለግል መደበቂያ ስር ጉጦች ያሉባቸው የፍጥነት መቀነሻ ቦታዎች ናቸው። ከጥሩ የመመልከቻ ቦታዎች ያላቸውና ጥብቅ የመተኮሻ ምሽግ ጋር በመዋሃድ እጅግ በጣም አመቺ የሆኑ የአደጋ መጣያ ቦታዎች ናቸው።

## 2.3.7 ጎዳናዎችና መንገዶች

ስትራቴጂያዊ ጎዳናዎችና መንገዶች ብዙ ጊዜ የወታደሮችንና የንግድን እንቅስቃሴን ለማቆም ፈንጂ ይቀበርባቸዋል። የተጎዱና የተዘጉ መንገዶች ደግሞ ተሽከርካሪዎችን ከመንገድ ውጭ ያሉ ዳርቻዎችንና ደልዳላ ቦታዎችን እንዲጠቀሙ ያስገድዳቸዋል። የመንገድ ጠርዞችና ደልዳላ ቦታዎች ደግሞ እንደመተላለፊያ ተቆጥረው ፈንጂ ይቀበርባቸዋል። አንዳነዴ የመንገዶች መካከለኛ ቦታ በናፍጣ ዘይት እንዲርስ ይደረግና ተቆፍሮ ፈንጂዎች ወይም ተፈዕ ይቀበሩበታል። ዙሪያቸውም (ምናልባትም የማስፈንጠሪያ ገመድ ሊሆን ይችላል) በአስፋልቱ ላይ ይታያል። በተመሳሳይም የግጭት ቦታዎችን እርስ በርስ የሚያገኛኙ መተላለፊያዎች ፈንጅ ይቀበርባቸዋል።

**ስዕል 2.13**
**(ግራ) ይህ መሰናክል ምንገድ ላይ የተቀመጠው ለምንድነው? ከጠነንካራው መንገድ ወጥተው በለስላሳውና ፈንጂ ለመቅበር በሚያመቸው መንገድ እንዲነዱ ለማድረግ ነው። ከበስተግራው ሁለት ሜትር ያህል ርቆ የሚገኘውን ፈንጂ ያዩታል? የቀድሞዋ ዩጎዝላቪያ።**
የተመ ፎቶ

**ስዕል 2.14**
**(በቀኝ) መሳሪያዎችን ለግንባታ መስሪያ በጠቀም ግጭት ተካሂደባቸው በነበሩ አገሮች የተለመደ ተግባር ነው። እዚህ የሚታየው 122 ሚሜ አርቲለሪ ሮኬት የቤት ድጋፍ (ቢም) ሆኖ ነው።**
የተመፈመአ ፎቶዎች/ቶማስ ኢንኬ





ጠባብ ቦታዎች ለምሳሌ መዞሪያ ቦታዎች፣ ጠባብ መንገዶች፣ ጥቅጥቅ ያለ ደን ያለባቸው መንገዶች ጉዞን የሚያዘገዩ ናቸው። ለእይታ በሚያመችና አስተማማኝ ቦታ ላይ ሆኖ ለማጥቃት በጣም ምርጥ ቦታዎች ናቸው።

### 2.3.8 የአውሮፕላን ማረፊያዎችና የባቡር መንገዶች

እንደ ድልድዮች ሁሉ የአውሮፕላን ማረፊያዎችና የባቡር መንገዶችም ዋና የመጓጓዣ ዘዴዎችና ለወታደራዊ ስትራቴጂ ቁልፍ ቦታዎች ናቸው። ስለሆነም ብዙ ጊዜ ፈንጂ ይጠመድባቸዋል። አጥሮችና ምልክቶች ሊሰበሩና ሊወገዱ ይችላሉ፣ በሮችና በህግ የተፈቀዱ መግቢያዎች እንዲሁ ተትተው በፈንጅና በስውር ወጥመድ ሊታጠሩ ይችላሉ።

### 2.3.9 የኤሌክትሪክ ኃይልና የውሃ አቅርቦት

የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫዎችና ማከፋፈያ ጣቢያዎች በጦርነት ጊዜ ጠቃሚ የስትራቴጂ ቦታዎች ናቸው። የጠላትን የመብራት አቅርቦት መቁረጥ የመግባቢያንና የእንቅስቃሴን ሂደት በጣም ያዉከዋል። ግድቦችና የውሃ ስራዎችም ለህዝብ አቅርቦትና ጠላት እንዳይገባበት የሚፈለግን ቦታ በጎርፍ ለማጥለቅለቅ ሊያገለግሉ ይችለሉ። ስለዚህም እነዚህ በፈንጂ ይጠበቃሉ።

### 2.3.10 ጥላ ያለባቸዉ ቦታዎች፣ የፍራፍሬ ማሳዎች፣የውሃ ምንጮች፣ ጉድጓዶች እና የወንዝ ዳርቻዎች፣ ዋሻ መግቢያዎች

ወታደሮች፣ የጠላት ጦር አባላት እንዲሁም በጦርነቱ ውስጥ ያሉ ሲቪል ሰዎች እንዳይታዩ የሚደብቋቸው ከለላና መጠለያ የሚሆኗቸው ቦታዎች ያሻሉ። የውሃና የምግብ የሚያገኙባቸውን መንገድም ለማስጠበቅ ይጥራሉ። ስለዚህም እነዚህን ቦታዎች በፈንጂ አማካኝነት ይከላከሏቸዋል።

በአንድ ቦታ ላይ ብዙ ህዝብ ተሰብስቦ መገኘት፣ ከፍተኛ መጨናነቅ ያለባቸው የታወቁ የመሰብሰቢያ ቦታዎችና ስፍራዎች ለተፈፀ ጥቃት አመቺ ናቸው።

**ከመንደግ ጋር በሚገኙ ደልዳላ ቦታዎች ላይ አያሽከርክሩ**





ስዕል 2.15
የተተወ ድልድይ። የሚያሰጋ ነገር የለውም? ባልካንስ።
የተመድ ፎቶ/ቶማስ ኢንኬ

ስዕል 2.16
የ100 ሚሜ በ695 ማቀፊያ ቦርሳ ለግንባታ ዕቃነት ውሎ፣አፍጋኒስታን።
የተመድ ፎቶ/ቶማስ ኢንኬ





### 2.3.11 ግንባታ የተካሄደባቸው ሥፍራዎች

እንደ ጣሪያ ድጋፍ (ቢም) ያሉ ዕቃዎች የግንባታ ጥሬ እቃዎች ናቸው። እንዳንዴ ሰዎች እንደ ሮኬት፣ ወይም ማሽጊያዎች ያሉ ታላላቅ የሚፈነዱ የጦርነት ቅሪቶችን (ፈጦቅ) ወይም ያልፈነዱ የጦር መሳሪያዎችን እንደግንባታ ጥሬ እቃ ቤቶቻቸውን ለማጠናከር ይጠቀሙባቸዋል። በዚህ ምክንነያት እንደ ቢም፣ ደረጃ፣ግድግዳ የመሳሰሉት አደገኛ መሳሪያዎች ሊኖራቸው ይችላል።

## 2.4 አካባቢያዊ ምልከቶች የሞቱ እንስሳትና ያልተለመዱ ዕቃዎች

### 2.4.1 የመሬት ላይ ምልክቶች፥የእጽዋትና የአፈር መለወጥ

መሬት ላይ የሚታዩ ምልክቶች ፈንጂ መኖሩን ሊያመለክቱ ይችላሉ።የእጽዋቱ ቀለም በደረቁ ተክሎች ያበዙበታል። በአሸዋማ ቦታዎች ላይ የአፈሩ ቀለም የተፈጥሮ ያልሆኑ የአፈር ቀለሞች ይታዩበታል። ለተወሰነ ጊዜ ፈንጂ ተቀብሮበት የቆየ አካባቢ ከሆነ፣ በግልጽ የሚታዩ አፈሩ ከተቆፈረ በኋላ በዝናብ በኋላ በመረጋጋቱ አነስተኛ ጎድጎድ ጉድጎድ ያሉ ወጥ ሆነው ይታያሉ ይኖራሉ። በአንዳነድ አጋጣሚ ደግሞ የተቆፈረው አፈር የተቀመጠባቸው ትንንሽ የአፈር ቁልሎች ይታያሉ፤ እንዲህ አይነት ምልክቶች ቶሎ የሚጠፉ ቢሆኑም።

ፈንጁ በቅርብ ጊዜ የተቀበረ ከሆነ ፈንጂዎቹ ሲቀበሩ የተነቀሉና የተቆራረጡ ደረቅ የሳር ጭብጦች ይታያሉ። ፈንጁ በጣም በቅርብ ጊዜ የተቀበረ ከሆነ ደግሞ ፈንጁን ለመሸፈን የዋለው ርጥብ አፈር ከአካባቢው ጠቆር ብሎ ይታያል።

እንዲሁም ተፈፅ በመንገድ አጠገብ ተጋላጭ በሆነ ቦታ ላይ ሊቀበርና ተመሳሳይ የመሬት ላይ ምልክቶች ሊያሳይ ይችላል።





ስዕል 2.17
በፀረ-ሰው ፈንጂ የተመታ የተመደ መኪና፣ ማሊ።
የተመደ ፎቶ

ስዕል 2.18
የተደመሰሱ ባዶ ቤቶች ፈንጂ ወይም ስውር ወጥመድ ሊጠመድባቸው ይችላል።ኮሶቮ።
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢነኬ

## 2.4.2 የተተው መንደሮችና እጽዋት የበቀሉባቸው ቦታዎች

የተተዉ መንደሮችና ከተማዎች ወይም አገልግሎት ላይ መዋል ያቆሙ ሜዳዎች በአካባቢው ፈንጂዎች ወይም የሚፈነዱ የጦርነት ቅሪቶች ለመኖራቸው ጠንካራ ማስረጃ ይሆናሉ። ከክለስተር ቦምብ ድብደባ፣ ወይም በአርቲለሪ ከሚደረግ የቦምብ ጥቃት በኋላ አካባቢው ፈንጂዎች እንደተቀበሩባቸው ቦታዎች ሁሉ አደገኛ ብክለት ያጋጥመዋል።

## 2.4.3 የተተውና የተደመሰሱ ቤቶችና ህንጻዎች

ብዙ ጊዜ ወታደሮችና ወይም የተቃራኒ ጎራ ተዋጊ ኃይሎች ራሳቸውን ለመከላከል ቤቶችን በፈንጂ ያጠምዱባቸዋል፤ ወይም በሚተዋቸው ቤቶች ላይ ፈንጂዎችንና ስውር ወጥመዶችን አጥምደው ይሄዳሉ። ይህም በቤቶቹ መጠለያ የሚፈልጉ ወታደሮችን ወይም ተዋጊዎችን ለማታለል የሚደረግ ነው። ቤቱ በውጊያ ወቅት በግልጽ ከተጎዳ ወይም ከተደመሰሰና ማንም የማይኖርበት ከሆነ፣ ያልፈነዳ መሳሪያ በውስጡ ሊኖር እንደሚችል ከፍተኛ እድል አለው። የተተውና ብቸኛ ሆነው የሚገኙ ህንጻዎችና ቤቶች የጥይትና የመሳሪያ ማስቀመጫ ሆነው ሊያገለግሉና በፈንጂ ወይም በስውር ወጥመድ የታጠሩ ሊሆኑ ይችላሉ።

## 2.4.4 በመንገድ ላይ የሚቀመጡ የግንድ ጉማጅና ቅርንጫፎች (ለደፈጣ ጥቃት መንገድ መዝጊያዎች)

አንዳንዴ ተዋጊዎች ባለተፈቀደ ኬላ ላይ መኪኖችን ለማቆም መንገዱን ይዘጉባቸውና መኪኖችን ያስቆማሉ፤ ወይም ከመንገድ ወጥተው ፈንጂ ወይም ያልፈነዳ መሣሪያ ሊኖር ወደሚችልበት አካባቢ እንዲሄዱ ያስገድዷቸዋል።

በሌላ መልኩ ደግሞ ይህ የመንገድ መዝጊያ ሰዎች አደጋ ሊያደርስ ወደሚችል ስፍራ እንዳይገቡ ለመከላከልም ሊሆን ይችላል። አስተማማኙ ውሳኔ ሌላ ተለዋጭ መንገድ መጠቀም ነው።





ስዕል 2.19
ሁሉም በፍንዳታ ምክንያት የሚፈጠሩ ጉድጓዶች የማስጠንቀቂያ ምልክት አይኖራቸውም። አንድ የፈነዳ ፈንጂ፣ ፈጦቅ ወይም ፈተዕ ከተገኘ በአካባቢው ሌሎችም እንደሚኖሩ ይገምቱ፣ አፍጋኒስታን።

የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢነኬ

ስዕል 2.20
ብዙ ተክሎች ባሉበት አካባቢ የደረሰ ዋነኛ የክለስተር መሳሪያ ድብደባ፣ ኮሶቮ።

የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢነኬ





## 2.4.5 የፍንዳታ ጉድጓዶች

በፍንዳታ ምክንያት የተፈጠሩ ጉድጓዶች ወይም በመንገዱ (አስፋልት ላይ) በግልጽ የሚታዩ መደበኛ ጥገናዎች ብዙ ጊዜ በግልጽ የሚታዩ የፀረ-ተሽከርካሪ ፈንጂዎች ወይም የከባድ ውጊያ ምልክቶች ሊሆኑ ይችላሉ። ስለዚህም በአካባቢው ባሉ ሌሎች ቦታዎች ላይ ሲዘዋወሩ ንቃቄ ማድረግ ያሻል። ምክንያቱም ያልጸዱ ወይም ሳይገኙ ያመለጡ ፈንጂዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ ነው። በተለይም ከመንገድ ወጥተው በጎን በሚገኙ በልስልስና ደልዳላ መሬት ላይ ብዙ አይቆዩ።

የሞርታር ጥይት ድብደባ፣ የግሪኔድ ወይም የክለስተር ቦመቦች ጥቃት በዋናነት በህንጻዎች፣ በመንገዶች፣ በአስፋልት፣ ወይም በተመለመሉ ዛፎች ላይ በግልጽ የሚታይ ምልከት ይተዋሉ። አንዳንዴ ምልክቱ በአስፋልቱ ላይ የተረጨና የተቀረጸ ይመስላል።

በአስፋልት ወይም በመንገድ ላይ የተደረገ ጥገና የተቀበረ የተፈፅ ማስፈንጠሪያ ገመድ ፍንጭ ሊሆን ይችላል። በተለይ ከተጠገነው አስፋልት አልፎ ወደመንገዱ ዳርቻ የዘለቀ መስመር ነገር ካለ ለተፈፅ ማስፈንጠሪያ እውነተኛ ምልክት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

## 2.4.6 የሳር ጉቶዎች

በደረቃማ ቦታዎች፣ ፈንጂዎች የተቀበሩባቸው አንዳንድ ቦታዎች ተለይተው አረንጓዴ ይሆናሉ፣ ወይም ተክሎችና ሳሮች ይበቅሉባቸዋል። ይህም የሚሆንበት ምክንያት በብረት የታሸጉት ፈንጂዎች ማታ ማታ በጣም ስለሚቀዘቅዙና እርጥበት ስለሚፈጥሩ ነው፤ ይህም እዚያ ቦታ ላይ ተክሎች ከሌሎች የተሻለ ውሃ እንዲያገኙ ስለሚያደርጋቸው ነው።





ስዕል 2.21
ኤም፣አር፣ዩ.ዲ የተባለ የፀረ ሰው ፈንጂ በመኪና ላይ ያደረሰው ጉዳት፣ ባልካንስ፡ የተመ ፎቶ።

የተመ ፎቶ

ስዕል 2.22
ቲ.ኤም-58 የፀረ-ተሽከርካሪ ፈንጂበአፍጋኒስታን የመንገድ ዳር አደጋ ከደረሰ በኋላ።

የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢነኬ

### 2.4.7 አገልግሎት የማይሰጡና አትክልቶች የበቀሉባቸው መንገዶችና ጎዳናዎች

አንድ ቦታ አገልግሎት የማይሰጥና ተክሎች የበቀሉበት ከሆነ ለተወሰነ ጊዜ በዚያ መንገድ ማንም ሰው አልሄደም ማለት ነው። የዚህ ምክንያት ደግሞ ያልፈነዱ የጦር መሳሪያዎች ወይም ፈጦቅ ሊሆኑ ይችላሉ። አንድ ቦታ በአካባቢው ካሉ ተመሳሳይ ቦታዎች ተለይቶ ካልታረሰና ቦታው ፈንጂ ተቀብሮበታል ወይም ባልፈነዱ መሳሪያዎች ተበክሏል ብለው ይገምቱ። በተጨማሪም የተተው መሳሪያዎች ክምችት ተክሎች በበቀሉባቸው ቦታዎች ተቀብረው ሊገኙ ይችላሉ፤ አንዳነዴ በስውር ወጥመድ ወይም በፈንጂ ታጥረው። በተጠራጠሩ ጊዜ በተደጋጋሚ ሰዎች የሚጠቀሙባቸውን መንገዶች ይምረጡና ይጓዙ።

### 2.4.8 የእንስሳት ቅሪተአካልና አጽም

የአንስሳት ወይም እንዲሁ የተተወ የሰዎች አጽም የፈንጂን መኖር ሊጠቁም ይችላል። የተጎዳ እንስሳ ወይም ሰው ከተጎዳ በኋላም ቢሆን ርጅም ቦታ ሊጓዝ እንደሚችል ልብ ይበሉ። ስለዚህ ተጨማሪ ፍንጮች ይፈልጉ። አስከሬኖቹ እንደ እጅ ግሪኔድ አይነት መሳሪያ የታጠቁ ሊሆኑ እንደሚችሉና ከፍንዳታ በኋላም ቢሆን አደጋ ያለበት ሁኔታ ሊሆን እንደሚችል ልብ ይበሉ። እንዲሁም አስከሬኖችን የሚያነሱ ሰዎችን ለማጥቃት ስውር ወጥመድ ተጠምዶ ሊሆን ይችላል።

### 2.4.9 ያለቦታው የሚታይ <<እቃ>>

ግጭት እየጠካሄደ ባለበት ቦታ፣ በመንገድ ዳር ፍላጎት ሊያሳድር ወይም ዋጋ ያለው ያልተለመደ ነገር ካዩ፣ ሁሌም ቢሆን ስውር ወጥመድ ሊኖርበት እንደሚችል ያስታውሱ። ስውር ወጥመዶች ሰዎችን በማታለል ነገሮችን እንዲያንቀሳቅሱና ወጥመዱን እንዲያፈነዱት ታስበው የሚዘጋጁ ናቸው። ያዩት ዕቃ የማን እንደሆነ ካላወቁና ተጓዥ ከሆኑ ተመራጩ ነገር ዕቃውን አለመቅረብ ነው።





የተተው መሳሪያዎች ክምችት ለአደጋ የሚያጋልጥ መሳሪያ ሊኖርባቸው ይችላል ወይም ወደ አንድ በርቀት መቆጣጠሪያ የሚፈነዳ መሣሪያነት ሊለወጡ ይችላሉ። ሰዎች እንዚህን ነገሮች ለማወቅ ካላቸው ጉጉት አንጻር፣ እንዲህ አይነቱ ክስተት በጣም አደገኛ ነው።

## 2.5 የአካባቢ ሁናቴ

የአካባቢ ሁናቴ የፈንጂ ቦታዎችን፣ ባልፈነዳ የጦር መሳሪያ የተበከሉ ቦታዎችን ወይም ሊከሰቱ የሚችሉ የተፈዕ ጥቃቶችን በሚመለከት ብዙ አይነት ፍንጭዎች ሊሰጥ ይችላል። ከሌሎች ፍንጭዎች በተጨማሪ የአካባቢውን ህዝብ መመልከት አካባቢውን ፤ ህንጻዎችንና ሁኔታዎችን ለመገምገም ያግዛል።




የኮንጎ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ○
የተመፈመአ ፎቶ/ማርክ ቫልቫይነትቲ

## 2.5.1 ክልክል ቦታዎች የመንደር ፈንጅ አምካኞች

የአካባቢው ህዝብ ሊሄድበት ወደማይፈልገው የመንገድ ዳርቻዎች፣ ወደመንደሮች ወይም ወደሜዳ ወይም ወደየትኛውም ቦታ ቢሆን አይሂዱ። እንዲህ አይነት ቦታዎች የተተው፣ ጥቅም ላይ ያልዋሉ፣ ወይም ማንም የማይኖባቸው መስለው ይታያሉ። የአካባቢው ሰዎች ብዙ ጊዜ (ሁልጊዜ ባይሆንም) የትኞቹ ቦታዎች አደገኛ እንደሆኑ ያውቃሉ። ምክንያቱም ውጊያው ሲካሄድ፣ ሰዎች አደጋ ሲደርስባቸው፣ፈንጂዎች ሲቀበሩ ያውቃሉ፤ ራሳቸውም ፈንጂ በመቅበር ተሳትፈው ሊሆን ይችላል። ተመላሽ ስደተኞች ወይም የተፈናቀሉ ሰዎች በውጊያው ቦታ እንደቆዩትና የውጊያውን አደጋ እንደተጋፈጡት ነዋሪዎች አስፈላጊው መረጃ ላይኖራቸው ይችላል። በቦታው ላይ ለረጅም ጊዜ ከኖሩ ሰዎች ምክር መጠየቅ ጠቃሚ ነው።





ስዕል 2.23
በስራቀን ያልተለመደ ባዶ መንገድ? ህዝቡ ስለደፈጣ ጥቃት መረጃ ያውቅ ይሆን እንዴ? ባልካንስና አፍሃኒስታን።

የተመፈመእ ፎቶ/ቶማስ ኢነኬ

በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ ፈንጂ በማጽዳት ስራ ለይ ከተሰማሩ ድርጅቶች ምንም አይነት ድጋፍ ሳይደረግላቸው ፈንጅ የማጽዳት ሥራ ላይ የተሰማሩ ነዋሪዎችን ለማግኘት ሁሉ ይችላሉ። ከነዚህ ሰዎች ለአደጋ ሊጋለጡ ስለሚችሉ ቦታዎች መረጃ ማግኘት ይጠቅማል፤ ሆኖም ግን ከፈንጂ ማጽዳት ስራቸው መራቅ ይገባል።

## 2.5.2 የማይጠበቅ ባህርይ

የአካባቢው ህዝብ በአካባቢው ለሚታየው ለውጥ የራሱ ምላሽ ይሰጣል። አደገኛ ነገር ካለ ከሱ ይርቃሉ። ከተጠበቀው የሰው ብዛት በታች ያለባቸው ወይም ምንም እግረኛ የሌለባቸው ባዶ መንገዶች እና መደበኛ የትራፊክ ፍሰት ባለበት መንገድ በጣም አነስተኛ የትራፊክ ፍሰት መታየት በዓለማችን ያልተለመደ ክስተት ነው። ህዝብ በብዛት በሚገበይባቸው ጊዜያት ሰው የሌለባቸው የገበያ ቦታዎች እና የነዳጅ ማደያዎች ስለአካባቢው ሁናቴና ለምን እንደሆነ ጥያቄ ያስነሳል። የተፈፀ ጥቃት ወይም የደፈጣ ጥቃትም እንዲሁ በማንኛውም ሰዓት ሊከሰት የማይችል አይደለም።





## 2.5.3 የቁርጥራጭ ብረቶች ጓሮና ፍለጋ

ያልፈነዱ መሳሪያዎችና የሚፈነዱ የጦርነት ቅሪቶች በጣም ውድ በሆኑ ጥሬ እቃዎች የሚሠሩ ናቸው። ለምሳሌ የአርቲለሪ ጥይቶች ያረብ ብረት፣ ነሃስ፣ እና የሚፈነዱ ንጥረነገሮች አሉበት። የከፋ ድህነት ባለባቸውና በጣም ብዙ ያልፈነዱ/ፈጦቅ ባሉባቸው አገሮች ሰዎች ብዙ ጊዜ ብረቶችን ይሰበስቡና የመሳሪያ መሸፈኛዎችን እንደገና ይጠቀማሉ፣ እንዲሁም የሚፈነዳውን ንጥረነገር ለማውጣት ይሞክራሉ። በዚህም ምክንያት አንዳንድ የብረት ቁርጥራጭ ያለባቸው ቦታዎች ሰዎች ለአደጋ ተጋልጠው ፍለጋ ካካሄዱበትም በኋላ ያልፈነዳ የጦር መሣሪያ ወይም ፈጦቅ ሊኖርባቸው ይችላሉ።

ከዚህም በላይ ፈንጂዎችን፣ ፈጦቅ እና ያልፈነዱ መሣሪያዎችን ስለሚፈልጉ ሰዎች ታሪክ ሊሰሙ ሁሉ ይችላሉ። እንደዚህ አይነት ታሪኮች ፈንጂ ስላለባቸውና ስለተተው ቦታዎች ጠንካራ ምልክቶች ናቸው።





ስዕል 2.24
በአፍጋኒስታን የመሳሪያ መደምሰሻ ቦታ ያልፈነዳ መሣሪያ ቁርጥራጭ ሰብሳቢዎች።

የተመፈመእ ፎቶ/ቶማስ ኢነኬ

ስዕል 2.25
የብረታብረት ቁርጥራጮች ስብስብ ፈጦቅ ሊኖራቸው ስለሚችሉ አደገኛ ሊሆኑ ያችላሉ፣ አፍጋኒስታን።

የተመፈመእ ፎቶ/ቶማስ ኢነኬ



የኮንጎ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የተመረመአ ፎቶ/ማርክ ቫይላንት

# ክፍል 3
# መሠረታዊ የደህንነት ምክር

# መሠረታዊ የደህንነት ምክሮች

በገጠራማ ቦታ ወይም በአንድ የተወሰነ ቦታ በሚጓዙበት ጊዜ ከሚከተሉት ነገሮች አንዱን ካዩ፣ አደጋ ውስጥ ሊሆኑ ይችላሉ። ስለዚህ ለእርሶና አብረው ላሉት ደህንነት የመከላከያ ርምጃዎች መውሰድ አስፈላጊ ነው።

- ማንኛውም አይነት የተተወ መሳሪያ፤ ማለትም ፈንጂ፣ ፈጦቅ፣ ያልፈነዳ ጦር መሣሪያ ወይም ተራ የሚፈነዳ ነገር (ወይም የነዚህ መስሪያ የሆኑ ነገሮች)፣
- በህግ የታወቀም ይሁን ያልታወቀ የፈንጂ ማስጠንቀቂያ ፍንጭ (በችካል ላይ ያለ ጣሳ ወይም የድንጋይ ክብካብ)፣
- ጦርነት መካሄዱን የሚጠቁሙ እንደ የመዋጊያ ስፍራ ወይም የተተውና የተደመሰሱ ኅንጻዎች ወይም፣
- የአካቢው ህዝብ የሚያሳየው ያልተለመደ ባሃርይ።

ከነዚህ ስጋቶች ራስን ለመከላከል የሚሆኑ የተወሰኑ መሠረታዊ ስትራቴጂዎች አሉ። ይህ ክፍል የሚያተኩረውም ከፍተኛ አደጋ ባለባቸው ቦታዎች የሚሠሩ ግለሰቦችና ድርጅቶች ሊወስዷቸው የሚገቡ የመከላከያ እርምጃዎች ላይ ነው።

ለማጠቃለልም፣ ካለፉት ክፍሎች የተወሰዱና የስጋት ምንጮችን በአጭሩ የሚያሳዩ ጥቆማዎች ከዚህ በታች ቀርበዋል፥

- ማናቸውም በሰዎች ላይ አሰቃቂ ጉዳት የሚያደርሱና ተሽከርካሪዎችን የሚደመስሱ የሚፈነዱ አደገኛ ነገሮች፣ ፈንጂዎች፣ የተተውና ያልፈነዱ የጦር መሳሪያዎች፣ ስውር ወጥመዶች ፣ የተተው ተፈዕ ናቸው፤
- ግጭቱ ከተካሄድ በኋላም ለዐመታት የሚዘልቅ የስጋት ምንጭ ናቸው፤
- በትንሽ ንክኪ ሳይቀር ሊፈነዱ ይችላሉ፤
- በጊዜ ሂደት ቀለማቸውን ሊለውጡ፣ሊዝጉና ለተለያዩ ነገሮች በመጋለጣቸው፣ በአየር ሁኔታ ምክንያት አቀማመጣቸውን ሊለውጡ ይችላሉ፤





ስዕል 3.1
ለአልበም የሚሆን ሌላ ነገር? ተገቢ ያልሆነ አደጋ ውስጥ ራሱን ከትቶ ፎቶ የሚያሳ የአይ.ኤስ. ኤ.አፍ. ወታደር፣ አፍጋኒስታን።

የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢነኬ

ስዕል 3.2
የተተወ ወታደራዊ ቁሳቁስ። ስውር ወጥመድ ይኖርበት ይሆን? ባልካንስ።

የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢነኬ





- አብዛኞቹ አደጋ የተጋለጡ ቦታች በህጋዊ መንገዱ የተቀመጡ ምልክቶች ቀርቶ ጊዜያዊ የማስጠንቀቂያ ምልክቶች አልተደረጉባቸውም፤
- ፈንጂዎች፣ የሚፈነዱ የጦርነት ቅሪቶች፣እና (የተተው) ተራ የሚፈነዱ መሳሪያዎች ያሉበትን ቦታ ለመለየት በጣም አስቸጋሪ ናቸው፤
- በመሬት ውስጥ ተቀብረው ወይም በረጃጅም ሳሮች ፣ በዛፎት፣ በወንዞች ዳርቻ፣ በህንጻዎችና በተሽከርካሪዎች ውስጥ እንዲሁም በውሃ ውስጥ ሊቀመጡ ይችላሉ፤
- የሚገኙትም ውጊያ በታካሄደበት ቦታ ፣ ወይም በስትራቴጂያዊ የወታደራዊ ይዞታ በሁኑ ቦታዎች ነው፤
- ማንም ሰው ቢሆን ፈንጂዎች፣ የሚፈነዱ የጦርነት ቅሪቶች፣ ባለባቸው ቦታዎች ተዘዋወረ ማለት ደህንነቱ እንደተጠበቀ ነው ማለት አይደለም።

## 3.1 ለአደጋ አጋላጭ ባህርይ

ፈንጂ ማለት ለመጉዳትና ለመደምሰስ ታስቦ የተሠራ የሚፈነዳ መሣሪያ ነው። በአደገኛ ቦታ ደህንነትን የሚያስጠብቅ ባህርይን ለመረዳትና ለአደጋ መጋለጥንም ለመከላከል በጦርነት በተጎዱ ቦታዎች ላይ የሚሰሩ ሰዎች አደጋ እንዲደርስባቸው የሚያደርጉትን የተወሰኑ ባህርያት ማወቁ ጠቃሚ ነው። ክስተቱ ዝም ብሎ በእድል ወይም በድንገት የሚከሰት አይደለም። በአደገኛ ቦታዎች በሚሰሩ ሰዎች የሚደርሱ አደጋዎች የጋራ የሆኑ ምክንያቶች አሏቸው።

### 3.1.1 ሆነ ብለው ለአደጋ የሚጋለጡ ሰዎች

በዚህ ምድብ የሚካተቱ ተዎች ሆን ብለውና እያወቁ አደገኛ ወደሆነ ቦታ የሚገቡ ወይም አደገኛ የሆነን ነገር ለመንካት የሚሞክሩ ናቸው። አንድ ግለሰብ ለዚህ አደጋ ራሱን የሚያጋልጥባቸው የተለያዩ ምክንያቶች አሉ። አንዳንድ ግጭት በተካሄደባቸው ቦታዎች የሚሰሩ ሰዎች ለጓደኞቻቸውና ለቤተሰቦታቸው ለማሳየት ብለው የጦር መሳሪያዎችን ለማስታወሻነት

## ንጥል ጥናት

እ.ኤ.አ በ2003 ዓ.ም. አንድ የ31 ዓመት ጋዜጠኛ ከየፎቶ አንሺ ጋዜጠኛ ጋር ሆነው በአንድ የኩርድ ወታደር እየተመሩ በሰሜናዊ ኢራቅ በሚገኝ አንድ የጦር መሸግ በሚሄዱበት ጊዜ ጋዜጠኛው በተቀበረ ፈንጂ ላይ ቆመ። የፎቶ አንሺው ወዲያውኑ የሞተ ሲሆን፣ ጋዜጠናው እግሩ እንዲቆረጥ ያደረገ አሰቃቂ አደጋ ደረሰበት።

ይሰበስባሉ። ከሚሰበስቧቸው ነገሮች መካከልም አደጋ አያደርሱም ብለው የሚያስቧቸው ነገሮች መካከልም የፈንጂ ማስጠንቀቂያ ምልክቶች፣ የፈንጂና ያልፈነዱ ጦር መሣሪያዎች ስሪተ-አካሎች ይካተታሉ። እነዚህ ሰዎች በተጨማሪም በተደመሰሱና በተተው ታንኮችና ሌሎች ወታደራዊ መሳሪያዎች ላይ ሆነው ፎቶ መነሳት ይወዳሉ። ይህ ባህርይ በጣም የሚያበሳጭ ቢሆንም በጦርነት በተመቱ አካባቢዎች በሚሠሩ ሰዎች፣ በተለይም ልምድ በሌላቸው ሠራተኞች በጣም የተለመደ ነው። በሚዩዋቸው የተተውና የተደመሰሱ መሳሪያዎች አዲስነትም ይማረካሉ።

በምዓራባዊ አገሮች ለወታደራዊ ቁሳቁሶች በተለይም ለተለያዩ አይነት ጥይቶች ትልቅ ገበያ አለ። በተባራሪ ገበያዎች ለማቀፊያ ካርታዎች፣ለአርቲለሪ ጥይቶች (ጎራሾች)ና ፊዩዞች ከፍተኛ ዋጋ ይከፈላል። በአብዛኛው ጥይቶች ከአደገኛ ነገር ህጋዊ መንገድ አልተረጋገጠም፣ በማንኛውም ተቋምም ከሚፈነዳ ነገር ነጻ ናቸው የሚል ማስረጃ አይሰጥም።


ሌሎች ሰዎች ደግሞ ደንታ የሌላቸውና ጀብዱ ፈላጊዎች ናቸው። ስለአደጋው ምንጭና ሽፋን ሙሉ ግንዛቤ የላቸውም። አደጋ ሊከሰት ይችላል የሚለውን ሀሳብም በጭራሽ በአእምሯቸው አያስቡትም። በዚህ ምድብ ውስጥ ብዙ ጊዜ የሚካተቱትም፥

- ለረጅም ጊዜ ለአደጋ ሥጋት ተጋልጠው የቆዩ ሰዎች፤
- ስለአደጋ ስጋት ግልጽ ግንዛቤ የሌላቸው ሰዎች፤
- አደጋን ለመቆጣጠር ከሚገባው በላይ የሚታመኑ ሰዎች።

እነዚህ ሰዎች ብዙ ጊዜ በድፍረት ስሜት አደጋውን በሚገባ ከግምት ሳያስገቡ ራሳቸውን ለጉዳት ይዳርጋሉ።







ሰዕል 3.3
ይህን ታንክ መፈተሽ ለምን ያስፈልጋል?
ለደህንነት የሚያሰጋ መሳሪያ እና አገልግሎቱን በጨረሰ ዩራኒየም ጉዳት የተጋለጠ ሊሆን ይችላል።
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢነኬ

ሰዕል 3.4
በመንገድ ዳር ስለሚገኙ እንግዳ ነገሮች ይወቁ። ከኋላ በኩል ሾልኮ የወጣውን ሽቦ ልብ ይበሉ፣ ይህ ተራ የሚፈነዳ ዕቃ ነው፤ ኢራቅ።
የተመ ፎቶ

ሰዕል 3.5
በዚህ መንዳት ለደህንነት አስተማማኝ ነው? ተተኳሾችና ቦመቦች ጸድተዋል። መንዲህ አይነት ፈጦቅ በሞላበት አካባቢ እርስዎና መኪናዎ ከአስፋልቱ አለመውጣትዎን በሚገባ ያረጋግጡ።
ፎቶ/የጀርመን ኃይሎች





በሌላ ምድብ የሚገኙት ደግሞ፣ ልምድ ባላቸው ላይ የተለመደ ባይሆንም፣ ስለፈንጂ፣ ፈጦቅ እና ተፈዕ ሁሉንም ነገር እንደሚያውቁ የሚያስቡ ሰዎች ናቸው። እነዚህ ሰዎች ለወታደርነት ልዩ ስሜት( ፍቅር) ያላቸውና ለሌሎች ሰዎች ስለሙያው ያላቸውን የዕውቀት ደረጃ ላማሳየት ወይም ለማረጋገጥ የሚፈልጉ ናቸው። እንዲህ አይነት ሰዎች ብዙ ጊዜ የቀድሞ ወታደራዊ ተቋማትን መኅብኘትና ዕቃዎችን መሰብሰብ ይወዳሉ። ልብ ይበሉ ሁሉንም እናውቃለን ከሚሉ ሰዎች ይልቅ በተለምዷዊ ባህርያቸው የሚጠነቀቁ ሰዎች አደጋን ለመከላከል የተሻሉ ናቸው።

## 3.1.2 ሳያስቡት ለአደጋ የሚጋለጡ ሰዎች

ሰዎች በድንገት ወይም ግዴታ ሆኖባቸው ፈንጂዎችን፣ ፈጦቅን ወይም ተፈዕን በተደጋጋሚ የሚያገኙበት አጋጣሚ ሊከሰት ይችላል። ብዙ ሰዎች ወደአደገኛ ቦታ የሚገቡና አደገኛ ነገሮችን የሚነኩት ያለፈቃዳቸው ነው። ሥራቸው ወደአደገኛ ቦታዎች እንዲገቡ ሊያስገድዳቸው ይችላል። ለምሳሌ ስራቸው በነዚህ ቦታዎች የግንባታ ሥራ ማካሄድ ሊጠይቃቸው ይችላል። ይህም በመቆፈሪያ መሳሪያ አማካኝነት ፈንጂ ለማፈንዳት እድል ያጋልጣቸዋል። ሳያስቡት ለአደጋ የሚጋለጡ ሰዎች የኃላፊነት ስሜት ያላቸው፣ ጥንቁቅና ለራሳቸውና ለሌሎች ደህንነት የሚያስቡ ስልሆኑ የደህንነት መልእክቶችን ለመቀበልና የደህንነት ስራ ለመስራት ሲታቀድ በቀላሉ ሊደረሱ የሚችሉ ናቸው።

ሰዎች የሚያስከትለውን አደጋ በሚገባ ሳይገነዘቡት አንዳንድ ቦታዎችና ዕቃዎችን ለማወቅ ጉጉት ሊያድርባቸው ቢችልም፤ ጉጉት ሳይታሰብ ለጉዳትሊያጋልጣቸው ይችላል። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ስለ አደጋ ምንጭ ነገሮች መጥፎ መረጃ ሊያገኙ ወይም የተሳሳተ መረጃ ሊደርሳቸው ይችላል። ፈንጂዎችን፣ ፈጦቅን ወይም ተፈዕን በሚመለከት የሚነገሩና ሰዎችን ለአደጋ የሚያጋልጥ ባህርይ እንዲኖራቸው የሚያደርጉ አንዳነድ ብሂሎች አሉ። በጣም የጠለመዱት የተወሰኑት ብሂሎችም ከዚህ በታች ይቀርባሉ።

### ንጥል ጥናት

በ2003 ወደ ኢራቅ ቆይቶ የተመለሰ አንድ ጋዜጠኛ ሁለት ተተኳሾችን ለማስታወሻን ይዞወደ ቤቱ ይመለሳል። ተተኳሾችን ያገኛቸው ባግዳድ ውስጥ በቦምብ በተደበደበ ተሽከርካሪ አጠገብ ሲሆን ወደሃደሩ ከመመለሱ በፊት ለ20 ቀናት ይዟቸው ይቆያል።ወዳገሩ በሚመለስበት ጊዜ የዮርዳኖስ የጸጥታ ኃይሎች ከሁለቱ አንዱን ተተኳሽ በራጂ አማካኝነት ይገኙታል። በእጅ ፍተሸ በሚደረግበት ጊዜ ተተኳሹ ነገር ይፈነዳል። አንድ የአየር መንገዱ ሠራተኛም በአደጋው ምክንያት ወዲያውኑ ይሞታል፣ ሌሎች ሶስት ሰዎችም ይቆስላሉ። ሁለተኛው ን ተተኳሽም ጓደኛው ይዞት ስለነበር በቁጥጥር ስር ተደርጎ እንዲፈነዳ ይደረጋል። ጋዜጠኛው ተተኳሾቹ የሚፈነዱና ለደህንነት ችግር የሚፈጥሩ ናቸው ብሎ አላመነም ነበር።

## 3.2 ስለፈንጂዎችና ስለሚፈነዱ የጦርነት ቅሪቶች የተለመዱ አባባሎች

**ብሂል፡** ሲረግጡት የሚቀባበልና የረገጡበትን እግር ሲያነሱ የሚፈነዳ ፈንጂ አለ። ይህም እግርዎን ከማንሳትዎ በፊት ሌላ ከበድ ያለ ነገር ፈልገው እንዲጭኑበት እድል ይሰጥዎታል።
**እውነታ፡** ይህ የሚታየው በፊልም/ቪዲዮ ውስጥ ብቻ ነው።

**ብሂል፡** ፈንጂ ወይም ያልፈነዳ ጦር መሳሪያ የሚገኝበት ቦታ የሚያውቁ ከሆነና ለመጀመሪያ ጊዜ በሰላም ከሄዱበት፣ ከዚያ በኋላ በእርስዎ አይፈነዳብዎትም።
**እውነታ፡** በጊዜ ብዛት የተነሳ አፈሩ (በተለይም በቅዝቃዜ/በሙቀት እንዲሁም በጎርፍ ምክንያት) ሊለዋወጥ ይችላል። ስለዚህም የፈንጂው/ያልፈነዳው የጦር መሳሪያ በቶሎ የሚፈነዳ ሊሆን ይችላል።

**ብሂል፡** ከአደገኛ አካባቢ የማምለጫ አንዱ ዘዴ በፍጥነት መሮጥ ወይም መንዳት ነው፣ በዚህ መንገድ ፍንዳታን ወይም የሚፈነዳ ፈንጂን ማምለጥ ይቻላል።
**እውነታ፡** የፈንጂን ወይም የሚፈነዳን ጦርመሳሪያ ፊዩዝ ወይም የፍንዳታን ሞገድ መቅደም አይቻልም።

**ብሂል፡** እንደ እድል ሆኖ የተቀበሩ ፈንጂዎች ረጅም እድሜ የላቸውም። በመሬት ውስጥ የተወሰኑ ዓመታት ከቆዩ በኋላ ስለሚበሰብሱ ይበላሻሉ።
**እውነታ፡** አብዛኞቹ ፈንጂዎች፣ ያልፈነዱ መሳሪያዎችና ተራ የሚፈነዱ እቃዎች ለአስርት ዐመታት አደገኛነታቸውን ጠብቀው ይኖራሉ። ብዙዎቹ ከፕላስቲክ የተሰሩ ስለሚሆኑ ውሃ ሰርጎ አይገባቸውም።

**ብሂል፡** ማስፈንጠሪያ ገመዱን መቁረጥ አንድን ፈንጂ፣ ስውር ወጥመድ ወይም ተፈፅ ያመክነዋል።
**እውነታ፡** አብዛኞቹ ፈንጂዎች፣ ስውር ወጥመዶች ወይም ተራ የሚፈነዱ ዕቃዎች በማስሰንጠሪያ ገመዳቸው ላይ የሚከሰት የውጥረት መጨመርም ሆነ





ስዕል 3.6
ጉጉት፣ ማስታወሻ መውሰድና ፎቶግራፍ መነሳት? ያልጣሉትን አያንሱ።
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢነኬ

ስዕል 3.7
የአርቲለሪ ጠይት፣ የሞርታር ጥይት እና ሌሎች የሚገኑዱ መሣሪያዎች ለተፈፀ መስሪያነት ያገለግላሉ፤አፍጋኒስታን።
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢነኬ





መቀነስ ያፈነዳቸዋል። ስለዚህ ተገቢውን ስልጠና በወሰደ መሳሪያ አምካኝ ካልሆነ በስተቀር መሳሪያዎችን የማምከኛ ዘዴ የለም።


**ብሂል፡** የማይፈነዱ መሣሪያዎች የሚፈጥሩት ስጋት አናሳ ነው፣ ምክንያቱም ስለሚታዩና በቀላሉ ከመንገድ ላይ ማንሳትና ማስወገድ።
**እውነታ፡** ማንኛውንም እንደ ፈንጂ፣ ያልፈነዳ ጦር መሳሪያ ወይም ተፈፅ ያለው ነገር ሁሉ መቅረብና መንካት አይገባም። አንደ ጊዜ የተንቀሳቀሰ ቢሆንም እንኳን በተደጋጋሚ ሲነካካ ሊፈነዳ ይችላል። አንዳንድ መሳሪያ በጣም ስሱ ነው፣ በትንሽ ንክኪ ሳይቀር ይፈነዳል።

**ብሂል፡** አንድን ቦታ ማቃጠል ከፈንጂ፣ ከሚፈነዳ ጦር መሳሪያና ከተፈፅ ነጻ ያደርገዋል።
**እውነታ፡** መንደርተኞች እንደዚህ ስላሉ ብቻ አንድን ቦታ ደህንነቱ የተጠበቀ ነው ማለት አጥቻልም። እንዲያውም አንዳንድ የሚፈነዱ መሣሪያዎችን የበለጠ ለመፈንዳት ዝግጁ ሊያደርጋቸው ይችላል።

**ብሂል፡** የተተወ መሳሪያ ለአገልግሎት ዝግጁ ስላልተደረገ ለደህንነት አስጊ አይደለም።
**እውነታ፡** የተተወ መሳሪያ ብዙ ጊዜ ባለበት ሁኔታ ለረጅም ጊዜ እንዲቆይ በማያደርግ አካባቢያዊ ሁኔታ ውስጥ ነው የሚገኘው። ለሙቀት መጋለጥ መሳሪያውን የበለጠ ተጋላጭና ሊፈነዳ የሚችል ሊያደርገው ይችላል፣ ወይም ጥንቃቄ የሌለው አያያዝ የታሸጉ መሳሪያዎችን ሳይቀር እንዲፈነዱ ሊያደርጋቸው ይችላል።

**ብሂል፡** በሜዳ ላይ እንስሳት የሚንቀሳቀሱበት ከሆነ ቦታውን ከፈንጂና ከሌላ መሳሪያ ሁሉ ነጻ ያደርጉታል።
**እውነታ፡** አንዳንዴ መንደርተኞች በዚህ መልክ ፈንጂዎችንና ተመሳሳይ መሳሪያዎችን ለማጽዳት ቢጠቀሙበትም፣ ይህ ተግባር ግን አንድን ቦታ ነጻ አይደርገውም። አንዳንድ መሳሪያዎችን ሊያፈነዳቸው ይችላል፣ ግን ሁሉንም ግን ላያፈነዳቸው ይችላል።





ስዕል 3.8
ከፍተኛ የፍንዳታ ኃይል ያለው በእጅ የሚወረወር ገሬኔድ። ተቃጥሏል፣ ግን አሁንም አደገኛ ነው፤ ባልካንስ።
ተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢነኬ

ስዕል 3.9
ከነደደ 20 ሰኮንድ የሆነው የ762ሚሜ በ 51 ማቀፊያ ቦርሳ (መሳሪያ የሌለበት)።
ስልት የሆኑትን ጠርዞች ልብ ብለው ያስተውሉ።
ፎቶ/የጀርመን ኃይሎች

**ብሂል፡** ቢያንስ ለስድስት ወር ያህል አገልግሎት ሲሰጥ የምታውቀው መንገድ ከሆነ፣ ምንም አይነት የፈንጂ ወይም የሌላ መሳሪያ አደጋ ስጋት አይኖርበትም። **እውነታ፡** መንገዱ በቋሚነት አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ ፈንጂዎችና ሌሎች መሳሪያዎች ከተቀበሩበት ሊወጡ ይችላሉ። ሲሄድበት የቆየ መንገድ በዝናባማ ወራት አገልግሎት የማይሰጥ ከሆነ አሽከርካሪዎች ፈንጂዎች በተቀበሩበት የመንገዱን ጠርዝ ሊያሽከረክሩ ይችላሉ።

**ብሂል፡** ፈንዎች የሚጣሉት ወጥና ሊተነበይ በሚችል ስልት ወጥ እንቅፋት ለመፍጠር ነው።
**እውነታ፡** ደንብን ተከትለው የሚሰሩ የጦር ሰራቶች ብዙ ጊዜ ወጥ በሆነ መልክ ፈንጂችን ቢጥሉ፣ ብዙ ፈንጂ የተቀበረባው ቦታዎች በግልጽ የሚታይና የፈንጂ አደጋው የት ጀምሮ የት እንደሚጨርስ ለመገመት የሚያስችል ወጥ ስልት የላቸውም፤ በተለይ በአንድ በግጽ በሚታወቅ ቦታ ጦርነት ከማካሄድ ይልቅ የእርስ በርስ ግጭት በተካሄደባቸው አገሮች።

## 3.3 ለድርጅቶች የሚሆን ምክሮች

ድርጅቶች ከፍተኛ የፈንጂዎች፣ ያልፈነዱ ጦር መሳሪያዎችና የተፈፀ ጥቃት በደረሰባቸው ቦታዎች ፕሮክቶችን አቅደው ለመተግበር በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ እነዚህ መሳሪያዎች ከሚያስከትሉት የአደጋ ስጋት በየአካባቢው ፕሮጀክታቸውን ለመተግበር የሚሳተፉ አጋሮቻቸውን ጨምሮ ሠራተኞቻቸውን ለመጠበቅ በሚገባ ሊያስቡበት ይገባል። ይህም አስፈላጊ የሆኑ ደህንነትን የሚያስጠብቁ አሠራሮችን መከተልና ለሁሉም ሠራተኛ ማዳረስን፣ ተገቢ ስልጠና መስጠትን፣ ትክክለኛ መሳሪያዎችን ማቅረብን እና ወቅታዊ የሆነ መረጃ በየጊዜው ማቅረብን ይጠይቃል። ደህንነትን ለማስጠበቅ ሲባል በሚሰጥ ስልጠናና እቅድ አማካኝነት አንድ አደጋን መቀነስ ለፕሮጀክቱ ትልቅ ዋጋ ያስገኛል።

ደህንነትን ለማስጠበቅ የሚወሰዱ እርምጃዎች ግጭት በተካሄደባቸው ቦታዎች ለሚደረግ ነባር የጸጥታ ጥበቃ አሠራር አካል ተደርገው ሊታሰቡ ይገባል፤ ግጭቱ ካቆመ የተወሰነ ጊዜ ቢያስቆጥርም። እነዚህ እርምጃዎች ተግባራዊና





ስዕል 3.10
የጠመንጃ ባሩድ ከሸካራው መሬት ጋር ውህደት ፈጥሯል። ስለዚህ ነዚህን ቀልሆች መፋቅና በምድሩ ላይ መቆም በጣም አደገኛ ይሆናል፣ አፍጋኒስታን።
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢነኬ

ስዕል 3.11
ይህ የቢ.ኤክ.ዩ-755 የክለስተር መሳሪያ አልፈነዳም ግን እስካሁን አደገኛ ነው፤ ባልካንስ።
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢነኬ





የየአካባቢውን የስጋት ደረጃና ተፈጥሮ መሠረት ያደረጉ ሊሆኑ የሚገባቸው ሲሆኑ፣ የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፥

- ስራው በሚከናወንበት ቦታ ስላልው የፈንጂ/ፈጦቅ/ተፈፀ ስጋት ዝርዝር መረጃ መሰብሰብና መረጃዉን በየጊዜው ወቀታዊ ማድረግ። የሚታይ አጭር መግለጫ (ካርታ ወይምአደገኛ ቦታዎችን ለይቶ የሚያመለክት በራሪ ወረቀት) ማዘጋጀት ሊታሰብ ይችላል፤
- በዚህ መጽሃፍ በተካተተው መረጃ መሠረት ከስራ ቦታው ነባራዊ ሁኔታ ጋር አስማምቶ ከፈንጂ/ፈጦቅ/ተፈፀ ራስን ለመከላከል የሚያስችሉ አሠራሮችን መዘርጋት። በተለይም ተሽከርካሪና የጉዞ ሪፖርት ማድረጊያ ስልት መዘርጋት ያስፈልጋል። (በአባሪ 1 ስለ መንገድ መሪ ካርዶች የቀረበውን ይመልከቱ)፤
- ከፈንጂ መከላከል ማዕከላትና ኤጀንሲዎች፣ ከተባበሩት መንግስታት የጸጥታ ባለስልጣናት፣ ከህብረብሄራዊ የሚፈነዱ መሳሪያዎች አዋገድ ማስተባበሪያ ህዋስ እና በብሄራዊ የሰላም አስከባሪ ሃይል የሚፈነዱ መሳሪያዎች አስወጋጅ ተጠሪ ፣ ክትትል አድራጊና አሰልጣኝ አካላት ጋር፣ ከአካባቢው ፖሊስና ከህክምና ተቋማት ጋር ወቅታዊና የሰመረ ግንኙነት መፍጠር፤
- ከብሄራዊ የፈንጅ መከላከል ማዕከል ከሚገኝ ‹‹የፈንጂ መከላከል ኢንፎርሜሽን ማኔጅመንት ሲስተም ዳታቤዝ (ማጠራቀሚያ ቋት)›› ውስጥ ስላለ መረጃ መጠየቅ፤
- ከፈንጂ/ፈጦቅ/ተፈፀ የተያያዘ መረጃ ማለትም በስራ ቦታ ስለሚገኙ ደህንነታቸው ስለተጠበቁና ስለአደገኛ መንገዶች፣ ስለአደጋ ጊዜ ተጠሪ መረጃ ለሠራተኞች መስጠት፤
- ለአደጋ ሊጋለጡ የሚችሉ ሰራተኞች (አሽከርካሪዎች፣ አስተርጓሚዎችን፣ መንገድ መሪዎችን ጨምሮ) ስለ ፈንጂ/ፈጦቅ/ተፈፀ የግንዛቤ ስልጠና መውሰዳቸውንና ከፈንጂ/ፈጦቅ/ተፈፀ ደህንነትን ለመጠበቅ ለሚያገለግሉ አሠራረሮች እንግዳ አለመሆናቸውን ማረጋገጥ፤
- ስለ ፈንጂ/ፈጦቅ/ተፈፀ ራስን ለመጠበቅ የሚደረግ ዝግጁነት በጊዜ ሂደት እንደሚቀንስ መረዳትና በየጊዜው የማነቃቂያ ስልጠና መስጠት ሊያስፈልግ እንደሚችል መረዳት፤

**በፈንጂ/ፈጦቅ አደጋ ጊዜ ለእርዳታ ማንን መጥራት እንዳለብዎት እርግጠኛ ይሁኑ።**

- ሰራተኞችዎ የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ፣ በተለይም በጣር ላይ ላል ሰው፣ የመስጠት ስልጠና መውሰዳቸውን ተሸከርካሪዎችም የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታና የጣር ጊዜ እርዳታ መስጠት የሚያስችሉ መሣሪያዎች ማሟላታቸውን ማረጋገጥ፤
- ሰራተኞችና ተሽከርካሪዎች ውጤታማ ተግባቦት ማድረግ የሚያስችል መሳሪያና ካርታ የተሟላላቸው መሆኑን ማረጋገጥና አጠቃቀማቸውን በሚመለከትም ስልጠና መስጠት።

የከፋ አደጋና ከፍተኛ ተጋላጭነት ባለባቸው ቦታዎች፣ ተሽከርካሪዎች ተጨማሪ የፍንዳታ መከላከያ እንዲኖራቸው የሚያስችል ለውጥ ማድረግ። ለተሽከርካሪዎች ተጨማሪ መከላከያ ለማድረግ የሚወሰዱ እርምጃዎችን በሚመለከት አባሪ 2ን ይመልከቱ።





ስዕል 3.12
የተለመዱ መሳሪያዎች አወጋገድ ስልጠና፣ ደቡብ ሱዳን።
የተመ ፎቶ

ስዕል 3.13
ወደተተው ወታደራዊ አቅርቦቶች፣ ስውር ወጥመዶች፣ ፈንጂዎች፣ ተፈፅ እና ለደህንነት የሚሳጋ ፈጦቅ አይሂዱ፤ ይህ ጉዳይ ትንሽ ግምት ሊሰጠው አይገባም፤ አፍጋኒስታን።
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢነኬ

## 3.4 ለግለሰቦች የሚሆኑ የደህንነት ምክሮች

የተሟላ መረጃ ማግኘት፣ ስለ ፈንጂዎች፣ ያልፈነዱ መሳሪያዎችና ተፈፅ የጋራ ግንዛቤን መከተልና ተገቢ ዝንባሌን መያዝ ደህንነትን ለማረጋገጥ የሚደረገውን ጥረት በማገዝና የሰዎችን ደህንነት በመጠበቅ ረገድ ዘላቂ መፍትሄ ለመስጠት ያስችላል። ራስንና የስራ ባልደረባን ለመከላከል የሚሆኑ አንዳንድ ጥቆማዎች ቀጥሎ ይቀርባሉ።

### 3.4.1 የአጠቃላይ ደህንነት መልእክቶች

- ፈንጂዎችን፣ የሚፈነዱ የጦርነት ቅሪቶችን፣ ያልፈነዱ የጦር መሳሪያዎችን እና ተራ የሚፈነዱ መሳሪያዎችን አይንኩ ወይም አይቅረቡ፤
- ጉዞ ከመጀመርዎ በፊት ስለአደገኛ ቦታዎች መረጃ ያግኙ፤
- ወደአደገኛ ቦታዎች ዘለው አይግቡ፤የወታደራዊ አገልግሎት መጠቀሚያዎችንና ቁሳቁሶችን ያስሱ፤
- ፈንጂዎችን፣ ያልፈነዱ ወይም የተተው የጦር መሳሪያዎችን እና ተራ የሚፈነዱ መሳሪያዎችን በምንም አይነት ምክንያት አይንኩ፤





- ፈንጂዎችን፣ የሚፈነዱ የጦርነት ቅሪቶችን፣ ያልፈነዱ የጦር መሳሪያዎችን እና ተራ የሚፈነዱ መሳሪያዎችን ወይም ሌሎችን መሳሪያዎች በፍጹም አይሰብስቡ፤
- ከመደበኛ ቦታው ውጭ የሚመስል በመሬት ላይ የወደቀ ወይም በዛፍ ላይ የተንጠለጠለ ማንኛውንም ነገር አይንኩ፤
- አካባቢያዊ የሆኑ የማስጠንቀቂያ ምልክቶችን ይወቁ፣ያክብሩም፤
- ሁልጊዜም ቢሆን አደጋ ሊያስከትል እንደሚችል የሚያመለክት ማንኛውም ፍንጭ በንቃት ይከታተሉ፤
- ጠቃሚ የደህንነት መረጃዎችን ለሌሎችም ያካፍሉ፤
- ስለጉዞ እቅድዎ ለሌሎች ሰዎች መረጃ ያካፍሉ።

**አይንኩ! ይመዝግቡና ሪፖርት ያድርጉ የጦርነት ማስታዋሻዎችን አይሰብስቡ! የፈንጂ ማስጥቀቂያ ምልክቶችን በምንም አይነት ምክንያት ከቦታቸው አያንሱ!**

**ከተተው ወታደራዊ ቁሳቁሶች ይራቁ!**

### 3.4.2 ዝግጁ ይሁኑ

#### 3.4.2.1 ስለሚፈነዳ መሳሪያ/ስለተራ የሚፈነዳ ዕቃ ግንዛቤና ስለመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ ስልጠና

ስለ ፈንጂ/ፈጦቅ/ተፈፅ ግንዛቤ የሚያስጨብጥና ስለመጀመሪያ እርዳታ አደራረግ ስልጠና መውሰድዎን ፣ ከድርጅትዎ የደህንነት መደበኛ አሰራሮች ጋርም በሚገባ መተዋወቅዎን ያረጋግጡ። እንዲህ አይነት ስልጠና ካልወሰዱ እንዲሰጥዎ ይጠይቁ።

#### 3.4.2.1 የተፈላጊ አድራሻዎች መረጃ

የፈንጂ መከላከያ ማዕከላትንና ኤጀንሲዎችን፣ የተባበሩት መንግስታት የጸጥታ ኃይሎችን፣ የህብረብሄር የሚፈነዱ መሳሪያዎች አስወጋጅ ማስተባበሪያ ህዋስን፣ የብሄራዊ የሚፈነዱ መሳሪያዎች አስወጋጅ- ሰላም አስከባሪ- ታዛቢ- አሰልጣኝ- የተልዕኮ ቡድኖችን፣ የድንገተኛ አደጋ አገልግሎት ሰጪዎችን በቅርብ ያሉ የህክምና ተቋማትን፣ ዝርዝር አድራሻዎች መዝግበው ይያዙ። የድንገተኛ አደጋ ጥሪ አድራሻዎችን በየጊዜው እየተከታተሉ ያስተካክሉ።

### 3.4.2.2 የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ መስጫ መሳሪያዎች

ሁሌም ቢሆን የመጀመሪያ እርዳታ ለመስጠት የሚያገለግል መሳሪያ በመኪናዎ ውስጥ መኖሩን ያረጋግጡ። የእያንዳንዱን እቃ የመጠቀሚያ ጊዜ ገደብ፣ የሚሰራ መሆን/አለመሆን ያረጋግጡ። እንዴት እንደሚጠቀሙባቸውም በደንብ ይወቁ።

### 3.4.2.3 ግንኙነት/ተግባቦት

መገናኛ ሬዲዮ ወይም ስልክ ሳይዙ አይጓዙ፤ አጠቃቀሙንም በደንብ ይወቁ። የሚያስፈልጉዎትን ፍሪኩዌንሲዎችን የስልክ ቁጥሮችን (ለምሳሌ የፈንጅ መከላከል ኤጀንሲዎች፣ የተባበሩት መንግስታት የጸጥታ ሃይል፣ የሰላም ማስከበር ታክቲካል ስራዎች ማዕከላት- ታዛቢ፣ ወይም ማሰልጠኛና ሌላ ተፈላጊ ተለዕኮ ያለው ቡድን) ይወቁ።

### 3.4.2.4 አደገኛ ቦታዎችን የሚያመለክት ካርታ

የተለያዩ ፈንጂ አምካኝ ድርጅቶች፣ የጀኔቫ ዓለማቀፍ የሰብአዊ ፈንጂአምካኝ ማዕከል፣ ህብረብሄራዊ የሚፈነዱ መሳሪያዎች አስወጋጅ ተቋማት፣በ ብሄራዊ ደረጃ ሰላም ለማስከበር፣ ለመታዘብ፣ ስልጠና ለመስጠት፣ ሌሎች ተፈላጊ ስራዎችን ለመስራት የተቋቋሙ ማዕከላት ስለፈንጂዎች/ፈጦቅ እና ሌሎች አደገኛ ቦታዎችን በሚመለከት መረጃዎችን የያዙ ካርታዎች ሊያዘጋጁ ይችላሉ። ከተገኘ ሁለንም ከፈንጂ/ፈጦቅ እንዲሁም ሌሎች እንደ ተፈዕ የመሰለ የስጋት ምንጮችን የሚመለከት መረጃ የያዘ ካርታ ይኑርዎት። ይህን ካርታ በጉዞዎ ወቅት ሁሉ ከአካባቢው ህዝብ በሚያገኙት መረጃ መሰረት በየጊዜው ያዘምኑት።

## 3.4.3 የስጋት ምንጮችን መገምገም

ፈንጂ፣ ፈጦቅ ወይም ተፈዐ አሉባቸው ወደሚባሉ ቦታዎች ከመንቀሳቀስዎ በፊት ስለነዚህ መሳሪያዎች ዝርዝር መረጃ ይኑርዎት። በአካባቢዎች ስለነዚህ መሳሪያዎች የሚያስጠነቅቁ በህግ የተፈቀዱም ይሁኑ ያልተፈቀዱ ማስጠንቀቂያ ምልክቶችንም ይወቁ። የሚገኙ ከሆነ እነዚህን መረጃዎች ከሚከተሉት ሊያገኙ ይችላሉ፥

**ይህን ያውቃሉ?**

**የአካባቢው ነዋሪዎች የፈንጂን/ፈጦቅን ስጋት በሚመለከት ዋነኛ የመረጃ ምንጮች ቢሆኑም ፤ ብዙ አደጋዎች የሚከሰቱት እነዚህ ነዋሪዎች ስለአደጋው ስጋት ስለሚፈጥሩት ከእውነታው የተለየ ስሜት ምክንያት ነው። በአካባቢው ያለምንም አደጋ በእግር መሄድና መኪና መንዳት በመቻላቸው ስለ አካባቢው ሁኔታ የተሳሳተ ግንዛቤ ሊያዳብሩ ይችላሉ።**

**የደህንነት ግምገማ በማድረግ ረገድ የእርዳታ ሳተኞችና የውጭ ጋዜጠኞች በአካባቢው ነዋሪ የሆኑ አስተርጓሚዎች ወይም መረጃ አቀባዮች ላይ ይመሰረታሉ። የእርዳታ ሰራተኞችና ጋዜጠኞች በአብዛኛው እንዚህን የግምገማ ጥያቄዎች አይጠይቁም፣ ምክንያቱም በሚያሳጣ መልኩ ጥንቃቄ የሚያደርጉ መሆናቸው በግልጽ እንዳይታወቅባቸው ይፈልጋሉ።**





- በአካባቢው ከሚገኝ የፈንጂ መከላከል ማዕከል (ፈመማ) እና የፈንጂ መከላከል ኤጀንሲዎች፤
- ከተባበሩት መንግስታት የጸጥታ ሃይሎች፤
- ከተባበሩት መንግስታት ወታደራዊ ታዛቢ ወይም ተባባሪዎችዎች፤
- በአካባቢው ከሚገኙ መንግስታዊ ወይም መንግስታዊ ያልሆኑ የእርዳታ ድርጅቶች፤
- ህብረብሄራዊ የፈንጂ መከላከል ተቋማት፣ በብሄራዊ ደረጃ ሰላም ለማስከበር፣ ለመታዘብ፣ ለማሰልጠን ወይም ለሌሎች ተፈላጊ ተግባራት የተሰማሩና ፈንጂ በመከላከል ላይ ከሚሰሩ ማዕከላት፣ እና/ወይም፤
- ከአካባቢው ባለስልጣናት።

በተጨማሪም ከአካባቢው ህዝብ መረጃ ለመሰብሰብ ይሞክሩ፤ በዕለታዊ አኗኗራቸው ምክንያት በአካባቢው ስለሚገኙ የስጋት ምንጮች የተለያየ እውቀት ሊኖራቸው ስለሚችል ወንዶችንም፣ ሴቶችንም፣ ህጻናትንም መጠየቅዎን እርግጠኛ ይሁኑ። ሆኖም ግን፤ ወደዚያ ቦታ በየጊዜው የሚመላለሱ ሰዎች በአካባቢው ስለሚገኙ የስጋት ምንጮች መረጃ ላይኖራቸው ይችላል። በጣም በከፍተኛ ደረጃ አስጊ ወደሆነ ቦታ የሚሄዱ ከሆን ወታደራዊና ሲቪል ተቋማትን እና የአካባቢውን ነባር ነዋሪዎች የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይጠይቁና ስለስጋቱ መረጃ ያጠናቅሩ፥

- በዚህ አካባቢ በሰዎች፣ በእንስሳት ወይም በተሽከርካሪዎች ላይ አደጋ ያደረሱ የፈንጂ/ያልፈነዱ የጦር መሳሪያዎች አደጋ ተከስቶ ያውቃል? የአደጋው መንስኤ ምን ነበር (ፈንጂ፣ ያልፈነዳ የጦር መሳሪያ ወይስ ስውር ወጥመድ/ተፈዕ)? አደጋው የደረሰው መቼና የት ነው?
- ፈንጂዎች/የሚፈነዳ የጦር መሳሪያ ይኖራል ብለው የሚጠረጥሩት ቦታ የት ነው?
- በዚህ አካባቢ ውጊያ ተካሂዶ ያውቃል? የት?
- በዚህ አካባቢ የሚኖሩ/የሚሰሩ/የሚያልፉ ወታደሮች አሉ?
- በዚህ አካባቢ ፍንዳታዎች ተከስተው ያውቃሉ? የት?
- ለደህንነት አስጊ በመሆናቸው ሰው የማይገባባቸው መንገዶች፣ ማቋረጫዎች፣ ሜዳዎች፣ ጉድጓዶች፣ ወይም ቤቶች አሉ?
- ነጻ/ሰላማዊ የሚባሉት መንገዶች የትኞቹ ናቸው?

**(የቀጠለ)**

**ያስተውሱ፣ በፈንጂ በተጠቁ ቦታዎች እንዴ ከመሳሳት ሺህ ጊዜ በግልጽ በሚያሳጣ መልክ ስጉ መሆንዎ መታወቁ የተሻለ ነው። ስልፈንጂ አጭር አጭር ገለጻ ይኑርዎት፣ በአካባቢው የሚያግዝዎ አካልም ለየራሳቸው ማግኘታቸውን እርግጠኛ ይሁኑ።**



ስዕል 3.14
ድልድዮች ስትራቴያዊና ተጋላጭ ቦታዎች ናቸው። ስለ ፈንጂዎች/ያልፈነዱ መሳሪያዎችና ተፈዕ ልብ ይበሉ፤ ባልካስ።

የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢነኬ

- በአካባቢው የማትሄዱባቸው አዲስ ወይም የቀድሞ ወታደራዊ ካምፖች አሉ? የት?
- አደገኛ ቦታዎች ላይ ምልክት ታደርጋላችሁ፣ ወይስ በህግ የጸደቁ ምልክቶችን ትጠቀማላችሁ?
- ምልክቶቹ እንዴት ያሉ?

የአካባቢው ነዋሪዎች ብዙ ጊዜ ፈንጂዎችንና ሌሎች የሚፈነዱ መሳሪያዎችን ለይተው አያውቋቸውም። ሁሉንም በአንድ ላይ ቦምቦች ወይም ፈንጂዎች ብለው ሊጠሯቸው ይችላሉ። ስለዚህ የጦር መሳሪያውን አይነት መወሰን ለጉዞ እቅድዎ በጣም የጎላ ልዩነት አለው፤ በፈንጂዎች ወይም በተተኳሾች- የተበከለ አካባቢ ያልፈነዱ መሳሪያዎች ከሚገኙበት አካባቢ የበለጠ አደገኛ ነው። ሆኖም፣ ጥርጣሬ ካለዎት፣ የከፋውን አማራጭ መገመትና ከቦታው መራቅ ተመራጭ ነው። አንድ የመረጃ ምንጭ አካባቢው አደገኛ እንደሆነ ካመለከትዎ፣ ከቦታው ይጠንቀቁ!

በአካባቢው ስለሚገኝ ፈንጂ ወይም ፈጠቅ አዲስ መረጃ ካገኙ ለዋና መስሪያ ቤትዎ፣ ለአካባቢው የፈንጂ መከላከል ማዕከል፣ ለፈንጅ መከላከል ኤጀንሲዎች፣ ለተባበሩት መንግስታት የጸጥታ ኃይል፣ ለህብረብሄራዊና የሚፈነዱ መሳሪያዎች አስወጋጅ ተቋም፣ ወይም በብሄራዊ ደረጃ ለሚገነኝ ሰላም አስከባሪ፣ ታዛቢ፣ ስልጠና ሰጪ ወይም ተልዕኮ ፈጻሚ ያሳውቁ። እነሱም ለሌሎች ድርጅቶችና ለሰራተኞቻቸው ያሳውቃሉ።

እንዲሁም የጉዞ እቅድዎ የግልም ይሁን የስራ ለሌሎች መንገርን አይርሱ።

### 3.4.4 የጋራ ግንዛቤዎን ይጠቀሙበት

- በመሣሪያ እንደተበከሉ ወደሚጠረጠሩ ቦታዎች አይግቡ፤ ነጻ መሆናቸው የተረጋገጡ መንገዶችን ብቻ ይጠቀሙ።
- ፈንጂዎችን፣ ያልፈነዱ መሣሪያዎችን ወይም የሚፈነዱ መሳሪየዎችን አይቅረቡ፣ አይንኩ። ወታደራዊ መገልገያዎችንና ቁሳቁሶችን አይንኩ።
- ያልፈነዱ የጦር መሳሪያዎችን፣ የተተው የጦር መሳሪያዎችን፣ የተተው ጠመንጃዎችን ወይም ከመደበኛ ቦታቸው ውጭ የሚመስሉ ነገሮችን አይቅረቡ፤ ምክንያቱም ስውር ወጥመድ ተጠምዶባቸው ይሆናል። ግጭት ባለበት ሁኔታ ሁሉም የተተው ወታደራዊ ተሽከርካሪዎችና መገልገያዎች፣ ያልፈነዱ ጦር መሳሪያዎች፣ የተተው ጦር መሳሪያዎች ስውር ወጥመድ ተጠምዶባቸዋል ብሎ መገመት የተሻለ ነው። ስውር ወጥመዶች ስለመኖርና አለመኖራቸው ለማረጋገጥ በባለሙያዎች ጥልቅ ምርመራ መረጋገጥ አለበት። ከመሳሪያዎች የተመዘዙ ወይም ከመሳሪያዎቹ የተገናኙ ያልተለመዱ ሽቦዎችን ልብ ይበሉ። እንዲሁም የተተው መሳሪያዎች የተቀባበሉ፣ ለመፈንዳት ትንሽ የቀራቸው ወይም ባልታወቀ ሁኔታ ላይ ያሉ ሊሆኑ ይችላሉ።
- ራስዎ የጣሉት ካልሆነ በቀር ማንኛውንም ነገር አያንሱ።
- ለማን ምን ሪፖርት ማድረግ እንዳለብዎ ይወቁ። የፈንጅ መከላከል ማዕከላትና የፈንጂ መከላከል ድርጅቶች በአብዛኛው ለሰብአዊ ፍጡር አደጋ በሚደቅኑ ወይም ልማትን በሚያደናቅፉ በፈንጂ እና በሚፈነዱ የጦርነት ቅሪቶች ስጋት ላይ ስራዎች ይሰራሉ። ወታደራዊና የፖሊስ ተቋማት ደግሞ የፀጥታ ችግር በሚፈጥሩ በተተው የጦር መሳሪያዎችና በተራ የሚፈነዱ ዕቃዎች ላይ ስራዎችን ይሰራሉ።
- ምልክት በተደረገባቸውም ይሁን ምልክት ባልተደረገባቸውና ፈንጂዎች፣ ፈጠቅ ወይም ተፈፅ አሉባቸው ተብለው በሚጠረጠሩ ወይም በሚታወቁ ቦታዎች ሁሉ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። በመጽዳት ጊዜ ትንንሽ አደገኛ ነገሮች ሊታለፉ ይችላሉ። ፈንጂዎችና የሚፈነዱ መሳሪያዎች በዝናብ ወይም በመሸርሸር ምክንያት ከቦታቸው ሊንቀሳቀሱ ይችላሉ። ፈንጂዎች ወይም ፈጠቅ በሚጸዳበት አካባቢ ከሆነ የሚያጸዳውን ቡድን ከመቅረብ ይታቀቡ፤ አራሳቸው እንዲቀርቡዋቸውና ካልጠየቁዎትና የሚፈለጉ መመሪያዎችን ሁሉ ካልተከተሉ በስተቀር።
- ሬዲዮ ወይም የሞባይል ስልክ በኤሌክትሪክ አማካኝነት የሚፈነዱና ሬዲዮ-ጥብቅ የሆኑ መሳሪያዎችን ወይም የተወሰኑ ያልፈነዱ መሳሪያዎችን ሊያፈነዱ የሚችሉ ሞገዶች ይለቃሉ። ስለዚህ ያልፈነዱ ጦር መሳሪያዎች፣ ስውር ወጥመዶች ወይም ተፈፅ ካሉባቸው ከ50 ሜትር ክልል ውስጥ የሬዲዮ መገናኛና ስልክ ከመጠቀም ይታቀቡ።
- ከባድ ወይም ለረጂም ጊዜ ጦርነት በተካሄደበት ቦታ ግንባታ የሚያከናውኑ ከሆነ፣ ዱድጓድ ሲቆፍሩ፣ መንገዶችንና ቦዮችን ሊገነቡ የተቀበሩ ፈንጂዎችን ወይም የሚፈነዱ የጦር መሳሪያዎችን ከተቀበሩበት ሊያወጡ

#### የፈንጂ መከላከል ማዕከላት

**በፈንጂና ባልፈነዳ የጦር መሳሪያ ክፉኛ በተጠቁ ብዙ አገሮች መንግስታት፣ የተባበሩት መንግስታት ኤጀንሲዎች እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የፈንጅ መከላከያ ማዕከላትን ለማቋቋም እገዛ ያደርጋሉ። እነዚህ ማዕከላት የፈንጅ ማጽዳት ሥራንን በማስተባበር፣ አደገኛ ቦታዎችን በምልክት የመለየት፣ የአደጋውን ጉዳት በመቀነስና ለተጎጂዎች ጥብቃ በመቆም ሚና ይጫወታሉ።**

**እነዚህ ማዕከላት በዋናነት የሚንቀሳቀሱት ሲቪል በሆነው የመንግስት አካል ሲሆን የሰብዓዊና የልማት ድጋፍ የሚያደርጉ ናቸው። ብዙ ጊዜ የጦር መሳሪያ ከሚያጸዱ ወታደራዊ አካላት ወይም የጸጥታ ኃይሎችና ተራ የሚፈነዱ እቃዎችን ለሚያጸዳ የፖሊስ ኃይል የተለዩ ናቸው።**

3.4 ለግለሰቦች የሚሆኑ የደህንነት ምክሮች
3.4.4 የጋራ ግንዛቤዎን ይጠቀሙበት

ይችላሉ። ስለዚህ ቆፋሮውን አቁመው በአካባቢው ያሉ ሰዎችን ሁሉ ያስወጡና ለአካባቢው ባለስልጣናት ያሳዉቁ፡ ያልፈነዳውን መሳሪያ ወይም ፈንጂዎችን ለማንሳት አይሞክሩ።

- ግጭት በሚካሄድበት ወይም ከዚህ በፊት ተካሂዶበት በነበረ ቦታ ላይ ቤት ወይም ቢሮ ለመስራት ሲያቅዱ፣ የቅርብ ቦታዎች የጦር መሳሪያ ወይም የጥይት ክምችት ወይም የተተወ መሳሪያ እንደሌለባቸው በሚገባ ያረጋግጡ። ከመሳሪያ ወይም ከጥይት መጋዘን ቅርበት ያለበ ቦታ ላይ መኖር ብዙ ጊዜ ለከፋ ጉዳት ይዳርጋል፣ መጋዘኑ አሁንም እያገለገለ ከሆነ ደግሞ ለጥቃት ያጋልጣል።

**የጋራ ግንዛቤዎን ይጠቀሙ። ከተጠራጠሩ ይዘግዩ! ግጭት ባለባቸው አካባቢዎች ከመንዳትዎ በፊት ከአካባቢው ባለስልጣናት ስለ ፀረ-ተሸከርካሪ ፈንጂ ያራጋግጡ። በመንገድ ጠርዞች በፍጹም አይንዱ! በተደጋጋሚ በተነዳባቸው መንገዶች ወይም ጎደናዎች አስፋል (የመካከለኛ ክፍል) ብቻ ይንዱ። በመንገድና ጎዳና ላይ ስለሚኖሩ እንቅፋቶች ይወቁ።**

### 3.4.4.1 በተሸከርካሪ መጓዝ

- የጉዞ ማሳወቂያ ካርድ በመሙላት ለሚሰሩበት መስሪያ ቤት ስለአቀዱት ጉዞ ቀን፣ ጊዜ እና የጉዞዎን መዳረሻ ቦታዎች ያሳውቁ (የጉዞ ማሳወቂያ ካርድ በአባሪ 1 ከነአጠቃቀሙ ገለጻ ይገኛል)። ጉዞዎን ከለወጡም ለመስሪያ ቤትዎ ያሳውቁ። ማሳወቅ/መገናኘት ካልቻሉ ግን አለመሄዱ ይመረጣል። ከመድረሻ ቦታዎ በተወሰነው ሰዓት ለመድረስ ወይም ሪፖርት ማድረግ ሳይችሉ ቢቀሩ፣ ድርጅትዎ እርስዎን ፍለጋ ይመጣል።
- በተቻለ መጠን ከሌላ ሰው ጋር፣ በተለይም እርስዎ የሚደርሱባቸውን ቦታዎች ሁሉ በደንብ ከሚያውቅ ሰው ጋር፣ ይጓዙ። በሁለት ተሸከርካሪዎች መጓዝ በብዙ አጋጣሚዎች ተመራጭ ነው።
- ዲሲፕሊኑን ጠብቀው በጥንቃቄና በተገቢው ቅደም ተከተል ያሽከርክሩ። በአካባቢው እንደሚኖረው የተፈፀ አደጋ ስጋትና አገልግሎት ላይ እንደሚውሉት የኤሌክትሪክ መቃዎሚያዎች ልኬት፣ በመኪኖች መካከል ሊኖር የሚገባውን ርቀት በሚገባ ይጠብቁ፤ ወዲያውኑ መቆም ሲያስፈልግ ለመቆምም ነቅተው ይጠብቁ።
- ጉዞዎን በጠዋት ሲጀምሩ በአካባቢው የሚኖሩ ተሸከርካሪዎች መንቀሳቀስ እስኪጀምሩ ተረጋግተው ይጠብቁ። በተደጋጋሚ ጉዞ በሚደረግባቸው መንገዶች ላይ ብቻ ይጓዙ። ሲቆሙም በተሄደበት መንገድ ላይ ብቻ ይሁን። ጉዞዎን በሚገባ ያቅዱ፤ በዝናባማ ወራት ሁሉ አደገኛ መንገዶችን ከከባድ ዝናብ በኋላ አይሂዱባቸው፤ ምክንያቱም የጎደጎዱ ቦታዎች ደህንነቱ



3.4 ለግለሰቦች የሚሆኑ የደህንነት ምክሮች
3.4.4 የጋራ ግንዛቤዎን ይጠቀሙበት

የተጠበቀውን መንገድ ሊያስተውዎ ይችላሉ፤ ፈንጂዎች በዝናብ አማካኝነት ከቦታቸው ሊንቀሳቀሱ ወይም ሊፈነዱ ይችላሉ።

- በፍጹም በጨለማ አይጓዙ። የእለት ጉዞዎ ፀሃይ ከመጥለቋ ከሁለት ሰዓት በፊት መጠናቀቅ አለበት። ይህም እርስዎንም ይሁን መስሪያ ቤትዎን አደጋ ቢደርስ በሁለት ሰዓት ውስጥ የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ እንዲያደርጉ ጊዜ ይሰጣቸዋል። በተጨማሪም የፈንጂ ማስጠንቀቂያ ምልክቶችና ፍንጮዎች በጨለማ አይታዩም።
- መንገዱ ረጅም ጊዜ የሚወስድ ቢሆንም እንኳን በተቻለ መጠን፣ በተጠረጉ መንገዶች ላይ ብቻ ይጓዙ። የተጠረጉ መንገዶች ካልተጠረጉት ባነሰ ነው ፈንጂ የሚቀበርባቸው። ነገር ግን የተጠረጉ መንገዶች ጠርዞችና ጎድጓዳ ቦታዎች ፈንጂ ደብቀው ሊይዙ ስለሚችሉ- በጉድጓዶችና ከተጠረጉ መንገዶች ውጭ ከመንዳት ይቆጠቡ። መኪናዎን ለማዞር ከዋናው ምንገድ አይውጡ። መኪናዎ ከተበላሸ ወይም ጎማዎ ከተነፈሰ ወደመንገድ ዳር አይጡ፤ ይልቁንም ብዙ ጊዜ በሚሄድበት ቦታ ላይ ያቁሙና መኪናዎን ያስተካክሉ።
- በአፈር መንገዶች ላይ ሲጓዙ፣ በተደጋጋሚ በተሄደበት መንገድ ላይ ይቆዩ። የሚጓዙበት መንገድ ለመኪናዎ በቂ ስፋት ያለው ሊሆን ይገባል። ለምሳሌ የጭነት መኪናዎች ከ«ባለአራት እግር ተነጂ» መኪናዎች ይሰፋል። ስለዚህ የጭነት መኪናዎች ከመሄጃው መንገድ አልፈው ሊሽከረከሩ ይችላሉ።
- በመንገድ ላይ ያለ መሰናክል በላዩ ላይ እንዲነቁ መንገዱን ለቀው ፈንጂ ወደተቀበረበት ቦታ እንዲነዱ ለማድረግ ታስበው እንደሚቀመጡ ይወቁ። መኪና ለማሳለፍ፣ ለማለፍ ወይም መሰናክልን ለማለፍ ብለው ከመንገድ ዳር በፍጹም አይውጡ። አስፈላጊ ከሆነ ደህንነቱ የተጠበቀውን መንገድ እስከሚያገኙ ወደኋላ ይመለሱ። ከመንገድ ተንሸራትቶ መውጣትና ፈንጅ ወዳለበት ጥግ መጠጋት እንዳለም ይወቁ።
- በመኪና ውስጥ ባሉ ሰዎች መካከል ለመቃኘት የሚያስች ጠርዞትና ክፍተቶች ይኑርዎት።
- በመሬት ላይ ያሉ አመልካቾችና ምልክቶችን ይፈልጉ። በመንገድ ላይ የሚታይ ያልተለመደ ልብስ፣ ጥቂት የተሰበሰቡ ድንጋዮች ለተፈፀ ጥቃት ምልክት ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ።
- ተጋላጭ በሆኑ እንደ ድልድይ፣መገናኛ ቦታዎች ጠባብ መተላለፊያዎች፣ በዝግታ የሚታለፉ ቦታዎች ላይ ልዩ ትኩረት ያድርጉ። እነዚህ ቦታዎች







ስዕል 3.15
(የመጀመሪያዎቹ ሁለት ስዕሎች)
በተሄደበት መንገድ ክልል ብቻ ይቆዩ። ለመመለስም ግጁ ይሁኑ።ባልካንስ።
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢነኬ

ስዕል 3.16
በመንገድ ጠርዝና ዳርቻዎች በፍጹም አይንዱ። የመኪና አሽከርካሪዎች ራሳቸውን አላስፈላጊ አደጋ ውስጥ ይከታሉ።
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢነኬ

የተፈፀ ጥቃት ለማድረስ በጣም አመቺ ናቸው። ወደቀደሙት ጦር መቀመጫዎች በሚያመሩ የተዘጉ መንገዶች ላይ በፍጹም አይንዱ። የወረቀት ቦርሳ፣ የልብስ ቁራጭ፣ የእንጨት ቦርድ ሁሉ ፈንጂዎችንና ስውር ወጥመድ ያለባቸውን ተፈፀ ሊደብቅ ይችላል። በጥንቃቄና በዝግታ ይንዱ።

- ለምንም ምክንያት ቢሆን መንገዱን አይልቀቁ፤ ለማረፍም ቢሆን። በተሄደበት መንገድ ላይ ይቁሙና ከመኪናዎ በኋላ ይቁሙ።
- ለተራ የሚፈነዱ እቃዎች ጥቃት በተጋለጡ መንገዶች ከመጠቀም ይቆጠቡ። ወደነዚህ ቦታዎች ከመሄድም ይቆጠቡ ምክንያቱም ቀጣዩ የነዚህ መሳሪያዎች ጥቃት መቼ እንደሚሆን መገመት አይቻልምና።
- የደፈጣ ተዋጊ ቡድኖች ባሉበት አካባቢ ቀን ቀን ሰላማዊ የሆነ መንገድ በጨለማ ላይሆን ይችላል። ፈንጂዎች ብዙ ጊዜ ለጨለማ ጊዜ መከላከያ ተብለው ሊጠበቁ ስለሚችሉ፤ በተለይ ጧትና ማታ ወደከተሞችና ወደመንደሮች ሲገቡ ጥንቃቄ ያድርጉ። በቀላሉ ህጉን በመከተል በጠዋት ሌሎች ተሽከርካሪዎች ከፊት እንዲቀድሙዎ ይፍቀዱ። ከጨለመ በኋላ ደግሞ ለፈንጂ ጥቃት በተጋለጡ ቦታዎች አይጓዙ።
- ሁለጊዜ የመቀመጫ ቀበሮዎን ይታጠቁ። የፈንጂ ወይም የተፈፀ ፍንዳታ ተሳፋሪዉን ወደመኪናው ጣራ ሊያፈናጥረው ስለሚችል የከፋ የራስና የአንገት ጉዳት ሊያስከትል ይችላል፤ ወይም ወይም መኪናዋን ሊገለብጣትና ተሳፋሪውን በጋቢናው ውስጥ ሊያንከባልለው ይችላል። ይህ ደግሞ መሮጣጠር ሲቻል ለሚከሰት ሞት ወይም ጉዳት ይዳርጋል።
- ከመቆምዎ በፊት ቱቦዎችና ጉድጓዶች፤ ወይም ቁፋሮ መካሄዱን የሚያመለክቱ ቅሪቶች መኖራቸውን የረጋግጡ። እነዚህ ምልክቶች ባሉበት መኪናዎን አያቁሙ። በያንዳንዱ (አቅደውም ይሁን ሳያቅዱ) በሚቆሙበት ጊዜ በአባሪ A3 በቀረበው መሠረት የ5/25 ማረጋገጫ ያድርጉ።
- አሽከርካሪዎችዎ ከፈንጂ አደጋ ራስን ጠብቆ የማሽከርከር ስልጠና መውሰዳቸውን ያረጋግጡ።

### 3.4.4.2 የእግር ጉዞ

- የአካባቢው መንገድ መሪ መንግዱን እንዲመራ ያድርጉ። ቢያንስ የአምስት ሜትር ርቀት በመንገድ መሪውና በርስዎ መካከል ሊኖር ይገባል። ነገር ግን





ስዕል 3.17
እንግዳ ነገር የሚመስል በመንገድ ዳር የተተወ የሚፈነዳ መሳሪያ፤ አፍጋኒስታን።
የተመሪ.መአ ፎቶ/ቶማስ ኢ.ኬ.

ስዕል 3.18
ያልፈነዳ የጦር መሳሪያ፤ ኤ 20 ሚ.ሜ ከከፍተኛ የሚፈነዳ ንጥረነገር የተሰራ ድንጋይ መሳይ ፀረ-አውሮፕላን ፕሮጀክታይል፤ አፍጋኒስታን።
የተመሪ.መአ ፎቶ/ቶማስ ኢ.ኬ.



3.4 ለግለሰቦች የሚሆኑ የደህንነት ምክሮች
3.4.4 የጋራ ግንዛቤዎን ይጠቀሙበት

በተጓዥ ቡድኖች መካከል ሊኖር የሚገባው ርቀት 25 ሜትር ነው።

- በእጽዋት በተሸፈነ ቦታ ላይ አይራመዱ። ከዚህ ይልቅ በተጠረጉ የመንገድ ዳርቻዎችና ብዙ ሰው በተረማመደበት መንገድ ይጓዙ።
- ሁሌም ቢሆን የመገናኛ መሳሪያና የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ ማድረጊያ መሳሪያዎች ይያዙ። እነዚህንም በተሽከርካሪዎ ውስጥ አይተዋቸው። እነዚህ መሳሪያዎች መያዝ ያለባቸው ከቡድኑ መሃል ላይ ወይም መጨረሻ ባለ ሰው ነው። ከፊት በሚጓዘው ቡድን ውስጥ ባለ ሰው መያዝ የለባቸውም።
- እንቅፋቶችን በጭራሽ አያንቀሳቅሱ፤ ፈንጂ ወይም ስውር ወጥመድ ተጠምዶባቸው ይሆናልና።
- ወደተተው ህንጻዎች አይግቡ፣ በድልድዮች ስር አይለፉ፣ የተተው ቦታዎችን አይጎብኙ። ከአካባቢው ነዋሪ ጋር ይነጋገሩና ከአካባቢው ባህርይ በመነሳት ለደህንነት አስጊ ያልሆኑ ቦታዎችን ያስተውሉ።
- ፈንጂ፣ ያልፈነዳ መሣሪያ ወይም ተፈፀ የሚመስል ስጦታ አይቀበሉ።
- ለፈንጂ፣ ለፈጠቀ ወይም ለተፈፀ ጥቃት በተጋለጡ ቦታዎች የማይታወቁና ያልተለመዱ ዕቃዎችን አይንኩ። የጦር መሳታወሻዎችንም አይቀበሉ። የተተው ወታደራዊ ተሽከርካሪዎችንና መገልገያ እቃዎችን አይቅረቡ።
- በቡድኑ አባላት መካከል ቅኝት የማድረጊያ ጠርዞችና ከፍት ቦታዎች ይኑሩዎት።
- በመሬት ላይ ያሉ አመልካቾችና ምልክቶችን ይፈልጉ። በመንገድ ላይ የሚታይ ያልተለመደ ልብስ፣ ጥቂት የተሰበሰቡ ድንጋዮች ለተፈፀ ጥቃት ምልክት ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ።
- ተጋላጭ በሆኑ እንደ ድልድይ፣መገናኛ ቦታዎች ጠባብ መተላለፊያዎች፣ በዝግታ የሚታለፉ ቦታዎች ላይ ልዩ ትኩረት ያድርጉ። እነዚህ ቦታዎች የተፈፀ ጥቃት ለማድረስ በጣም አመቺ ናቸው።
- ቱቦዎችና ጉድጓዶች፤ ወይም ቁፋሮ መካሄዱን የሚያመለክቱ ቅሪቶች ባሉባቸው ቦታዎች አይቁሙ።
- እነዚህን ህግጋት በታወቁና በሚጠረጠሩ አደገኛ ቦታዎች ሁሉ በስራና በግል በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ ሁሉ ይከተሏቸው። ስለጉዞዎ እቅድ ቢያንስ ለአንድ ሌላ ሰው ማሳወቅዎን ያረጋግጡ።
- ከሁሉም በላይ ጥንቁቅ ይሁኑ።



ስዕል 3.19
በቀይና በነጭ ድንጋዮች ምልክት የተደረገበት የአፍጋኒስታን መንገድ። ነጭ ድንጋይ ባለበት ጎን ብቻ ይጠቀሙ!
የተመሪ.መአ ፎቶ/ቶማስ ኢ.ኬ.



የኮንጎ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የተመሬመአ ፎቶ/ማርክ ቫይላንት

## ክፍል 4

# የድንገተኛ አደጋ ጊዜ የአፈጻጸም መመሪያ

# የአደጋ ጊዜ ተግባራት ደንብ

## 4.1 በሚፈነዳ ነገር በተበከሉ ቦታዎች ወይም ፈንጂ ባለባቸው ቦታዎች የአደጋ ጊዜ መመሪያ

ያልፈነዱና የተተው መሳሪያዎች ባሉባቸው አካባቢዎች «አለመንካት» እና «አለመቅረብ» ደህንነትዎን የሚጠብቁ መሰረታዊ መመሪያዎች ናቸው። ያልፈነዳ የጦር መሳሪያ ካዩ ወይም በሚፈነዳ መሳሪያ ወደተጠቃ ቦታ ከቀረቡ፣ ፈንጂ ባለበት ቦታ ውስጥ ተገኝተዋል ማለት አይደልም። ባለሙያዎቹ እንዲህ አይነቶቹን ቦታዎች የጦር ሜዳዎች ነው የሚሏቸው። በነዚህ ቦታዎች እንደ ትንንሽ ቦምቦች አይነት ያልፈነዱ የጦር መሳሪያዎችና ጥይቶች በመሬት ላይ፣ በዛፍ ላይ ወይም በየትኛውም ቦታ ይገኛሉ። እነዚህ ቦታዎች ፈንጂ ከሚገኝባቸው ቦታዎች የማያንስ አደገኛነት አላቸው። ስለዚህም ከዚህ በታች የሚከተሉት መመሪያዎች ተመሳሳይ ናቸው። ተመራጩ ነገር ከነዚህ ቦታዎች መራቅ ነው። ነገር ግን የፈንጂ መከላከል ማዕከል ወይም ለሌሎች ተገቢ ባለስልጣናት ያዩትን ነገር ሪፖርት ማድረግ ስለእንደዚህ አይነት የስጋት ምንጭ ግንዛቤው እንዲኖራቸው ያደርጋል።

ፈንጂ/ያልፈነዳ ጦር መሳሪያ/ተፈፅ ማስጠንቀቂያ ፍንጭ (ለምሳሌ በግልጽ የሚታይ ፈንጂ/ያልፈነዳ መሳሪያ ወይም ፈንጂ/ያልፈነዳ መሳሪያ ሲፈነዳ የቆፈረው ጉድጓድ) ካዩ ግን፣ በአደገኛ ቦታ ውስጥ እንዳሉ ይቁጠሩ፤ ደህንነቱ አስተማማኝ በሆነ መንገድ ወይም ጎዳና ላይ መሆንዎን እርግጠኛ እስካልሆኑ ድረስ። አንዴ በእንደዚህ አይነት ቦታዎች ውስጥ ከገቡ ግን ባለሙያ ያልሆነ ሰው ሊያደርገው የሚችለው ነገር እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። ፈንጂ ባለበት ቦታ ውስጥ የሚያስፈልጉ ክሂሎችና መሳሪያዎች አጠቃቀም በአንድ ቅጽበት የሚማሩት አይደለምና።

ይህ ክፍል ራስዎን በሚፈነዳ የጦርመሳሪያ ወይም በፈንጂ መገኛ ቦታዎች ባገኙት ጊዜ ሊከተሏቸው የሚገቡ የተወሰኑ አጠቃላይ መመሪያዎችን ይዟል።



ስዕል 4.1
በስሮችና ነቅጠሎች ተሸፍኖ ለማግኘት አስቸጋሪ የሆነ ፈጦቅ፤ ባልካንስ።

የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢነኬ





### 4.1.1 የእግር ጉዞ አደጋ ጊዜ መመሪያ

ራስዎን በፈንጂ መገኛ ቦታ ውስጥ ሊያገኙ የሚችሉባቸው አጋጣሚዎች ፍንዳታ ሲከሰት ወይንም ፈንጂ ወይም የፈንጂ ምልከት ሲያዩ ነው። አንድ ሰው ከተጎዳ ለመርዳት ብለው መፍጠን የለብዎም፤ ራስዎንና በአቅራቢያዎ ያሉትን ሰዎች ሊጎዱ ይችላሉና። ራስዎን በፈንጅ መገኛ ቦታዎች ውስጥ ካገኙት፣ ተረጋግተው የሚከተሉትን መመሪያዎች ይከተሉ።

- **ፈ** ፈጥነው ይቁሙ! ቀጥ ይበሉና እግርዎን ካሉበት ቦታ አያንቀሳቅሱ።
- **ን** ንቁ! በአካባቢዎ ላሉ ሰዎች ያሳውቁ፣ ያስጠንቅቁ። የእርዳታ ጥሪ ያቅርቡ፣ ግን ሌሎች እንዳይቀርቡ ያድርጉ።
- **ጅ** ጅማሬ ቅኝት! አካባቢዎን ይቃኙ። ሌላ ምን ይታይዎታል፡ ፈንጂዎች፣ ማስፈንጠሪያ ሽቦዎች፣ የፈንጂ ምልክቶች? በቅርብ ሚገኘውን አስተማማኝ ቦታ ይለዩ፤ ለመጨረሻ ጊዜ ከአደጋ ነጻ የሆነው የነበሩበትን የሚያውቁትን ቦታ ማለትም የተጠረገ መንገድ፣ ብዙ የተሄደበት መንገድ፣ የኮንክሪት ወይም የብረት ስሪት።
- **አ** አስተውሉ! የመጡበትን መንገድ ይገምግሙ። ሁሉንም ነገር ለመቆጣጠር ይዘጋጁ።
- **ለ** ለዩ! ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ ለመሆኑ ምልክት ካላዩ ወይም የሚረግጡት ቦታ ሌላ ደህንነቱ ያልተረጋገጠ ቦታ ካልረገጡ የማይደርሱበት ከሆነ፤ አይንቀሳቀሱ። እርዳት እስከሚደርስልዎ ይጠብቁ።

እርዳታ በሚጠይቁበት ጊዜ በቂ ምላሽ ያላገኙ ሊመስልዎ ይችላል፤ ግን ትክክለኛውን የጉዞ መመሪያ ተከትለው ከሆነ፣ የጊዜ ጉዳይ እንጂ ተገቢው ስልጠና ያለው ባለሙያ እርስዎን ለመርዳት ቅርብ ነው። ሌላው አማራጭ ሞት ወይም የአካል ጉዳት ነው።

ባለሙያ ካልሆኑ ሰዎች እርዳታ ይጠንቀቁ። አደጋውን ሙሉ በሙሉ ላይገነዘቡት ወይም ባላቸው ውስን እውቀት ከሚገባው በላይ ሊመኩ ይችላሉ። ሰዎች አንዳንዴ የተጎዱ ሌሎች ሰዎችን ለማዳን ሲሉ አላስፈላጊ አደጋ ውስጥ ይከታሉ።

## 4.1.1.1 ምልክትና ሪፖርት ያድርጉ

ፈንጂ ወይም ያልፈነዳ የጦር መሳሪያ ካዩ፣ ያዩበትን ቦታ በአካባቢው ላለ የፈንጅ አማካኝ ማዕከል ወይም ለሌሎች ተገቢ ቢሮዎች (ለመንደር መሪዎች፣ ለፖሊስ፣ ለጦር መሪዎች፣ ወይም በቅርብ ለሚገኝ የፈንጅ አጽጂ ድርጅት) ከዚህ በላይ በተገለጸው መሠረት ሪፖርት ማድረግ አለብዎት።

አንዳንድ አካላት ፈንጂው ያለበትን ቦታ ምልክት በማድረግ ለሌሎቹ ስለ አደገኛው ቦታ ማመልከት እንደሚገባ ይመክራሉ። በአንዳነድ አጋጠሚዎች ግን ምልክት ማድረግ አደገኛ ሊሆን ይችላል፤ተገቢ የሆነ ምልክት መድረጊያ ነገር ማግኘትና ማስቀመጥ ስለሚያስፈልግና ይህ ደግሞ በፈንጂው ና ምናልባትም ሌሎች ፈንጂዎች ባለባቸው አካባቢዎች እንዲቆዩ ስለሚያደርግ። በተጨማሪም፣ ለሌሎች ከምልክቱ አንጻር ፈንጂው በየት በኩል እንዳለም ግልጽ ላይሆንላቸው ይችላል።

ስለ ምልክት አደራረግ ሊታወሱ የሚገባቸው የተወሰኑ ቁልፍ ነጥቦች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፥

ስዕል 4.2
አደገኛ ቦታ ላይ ምልክት ማድረግ በጥንቃቄና በአስተማማኝ ሁኔታ መከናወን አለበት፤ ባልካንስ።
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢነኬ



- የማስጠንቀቂያ ምልክት ለማስቀመጥ ወይም ለመስራት ከአስተማማኝ መንገድ አይለፉ፤
- የሚሰሩት ምልክት ለአዋቂዎችም ሆነ ለህጻናት በግልጽ የሚታይና የሚለይ መሆን አለበት። በአካባቢው የተለመደው ምልክት ማድረጊያ ምን እንደሆነ ማወቅ ይኖርብዎታል፤
- ምልክቱ ፈንጂ ባለተቀበረበት አስተማማኝ ቦታ ላይ መቀመጥ አለበት፤
- ለእያንዳንዱ ፈንጂ ምልክት አያስቀምጡ፤፤ ነገር ግን አደጋ እነዳለ ብቻ የሚያመለክት አጠቃላይ ምልክት ያኑሩ።
- ድርጅትዎ ከሚጠቀምበትን የምልክት አደራረግ ጋር ያወዳድሩት።




ስዕል 4.3
አስተማማኝ መንገድዎን በጭራሽ አይልቀቁ፤ ባልካንስ።
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢነኬ

## 4.1.1.2 የእግር ዱካን ወደኋላ መፈለግ

የእግር ዱካን ወደኋላ መፈለግ ወደፈንጂ መገኛ ቦታዎች ስንገባ የረገጥነውን መሬት የእግር ዱካችን ላይ ብቻ በመርገጥ ወደኋላ በመሄድ ከፈንጂ ቦታ የመውጣት ስልት ነው። የእግር ዱካን ወደኋላ መፈለግ ከፈንጂ መገኛ ቦታ ለመውጣት አስተማማኝ አማራጭ አይደለም። ምክንያቱም በጭቃ ላይ ካልሆነ በቀር የእግር ዱካችንን ማግኘት የሚቻል ነገር ስላልሆነ። የተወሰኑ ዱካዎች ቢገኙም እንኳን ዱካዎችን እየፈለጉ ሲቆሙ ሊወድቁ፣ ሊንገዳገዱ፣ ወይም እግርዎን ከዱካው አልፍው ሊረግጡ ስለሚችሉ በጣም አደገኛ ነው። በተጨማሪም ዝቅ ብሎ የተወጠረና ወደቦታው ሲሄዱ ያልታየ ማስፈንጠሪያ ገመድ ሊኖር እንደሚችልና አሁን ሲነካ ፈንጂውን ሊያቀጣጠልና ሊያፈነዳ እንደሚችል ይገንዘቡ።

በአንዳንድ አገሮች እርዳታ መጠበቅ ተግባራዊ ወይም አስተማማኝ ላይሆን ይችላል። የኋላ ዱካን በመከተል ከፈንጂ መገኛ ቦታ የመውጣትን ጥበብ መማር ከፈለጉ፣ ከፈንጅ መከላከል ማዕከል ወይም ከሌላ ድርጅቶች ባለሙያዎችን ማማከር እና ትክክለኛ መመሪያዎችን በተግባር መለማመድ ያስፈልጋል።

### 4.1.1.3 ጉንተላ

ጉንተላ ሌላው ከፈንጂ መገኛ ቦታዎች ወደ አስተማማኝ ቦታዎች ለመውጣት የሚያገለግል ዘዴ ነው። መሬቱን በቢላዋ ወይም በተመሳሳይ ነገር በመነካካት ፈንጂ የሌለበትን ቦታ መለየት ነው። ጉንተላ በጣም አስቸጋሪና ለባለሙያ ፈንጂ አምካኞች ብቻ በጥንቃቄና በትኩረት የሚሰጥና ብዙ ተግባራዊ ልምምድ የሚሻ አድካሚና ለጉዳት የሚያጋልጥ ዘዴ ነው። ጉንተላ በጣም ጥልቅ የሆነ ፈንጂ ፈልጎ የማግኘት እውቀትና ትክክለኛ ቁሳቁስ የሚጠይቅ ዘዴና ነው። ጉንተላን መጠቀም ከግንዛቤ ሊገባ የሚችለው ተቀባይነት ያለው ሙያዊ ስልጠና በወሰደ ባለሙያ እንጂ በሌላ በማንም አይደለም። ከላይ የተጠቀሰው ዘዴ ጥቅም ላይ የሚውለው፣ ለምሳሌ፦

- በፈንጂ መገኛ ቦታ ውስጥ ከገቡና ምንን አይነት እርዳታ ማግኘት የማይቻል ከሆነ፤
- በፈንጂ መገኛ ቦታ ውስጥ ከሆናችሁና ቀጥታ ጥቃት የሚደርስብዎ ከሆነ፤
- አንድ ግለሰብ ከተጎዳና ከፈንጂ መገኛው ቦታ መውጣት ካልቻለ፣ እንዲሁም ሌላ እርዳታ ማግኘት ካልተቻለ።

እነዚህ አጋጣሚዎች ግን የመከሰት እድላቸው በጣም አናሳ ነው። ስለ ጉንተላ የድርጅትዎ ፖሊሲ ምን እንደሚል ያረጋግጡ!

**ሁሌም ቢሆን የአደጋ ጊዜ የጥሪ አድራሻዎችን ወቅታዊ ያድርጉ**

**አደጋን እንዴት ሪፖርት ማድረግ እንዳለብዎት ይወቁ፤ ማን፣ የት፣ መቼ?ምን ያህል ጉዳተኞች?**

## 4.1.2 የመኪና ጉዞ አደጋ ጊዜ መመሪያ

ወደፈንጂ መገኛ ቦታ ገብቻለሁ በለው የሚያምኑበት ምክንያት፣ ለምሳሌ ቀድሞዎ የሄደ መኪና ፈንጂ ካፈነዳ፣ ፈንጂ ወይም የፈንጂ ምልክት ካዩ ወይም መኪናዎ ፈንጂ ካፈነዳች፣ የሚከተሉትን መመሪዎች መከተል ይገባል፦



4.1 በሚፈነዳ ነገር በተበከሉ ቦታዎች ወይም ፈንጂ ባለባቸው ቦታዎች የአደጋ ጊዜ መመሪያ
4.1.2 የመኪና ጉዞ አደጋ ጊዜ መመሪያ

**ፈ** ፈጥነው ይቁሙ! ተሽከርካሪዎን ያቁሙ! ከቦታው ለመመለስ አይሞክሩ፤ የመኪናዎን ጎማ አያንቀሳቅሱ። ቀጥ ይበሉና ከመኪናዎ ውስጥ ይቆዩ

**ን** ንቁ! በአካባቢዎ ላሉ ሰዎች ያሳውቁ፣ ያስጠንቅቁ። የእርዳታ ጥሪ ያቅርቡ፣ ግን ሌሎች እንዳይቀርቡ ያድርጉ።

**ጅ** ፈንጂዎች፣ ማስፈንጠሪያ ሽቦዎች፣ የፈንጂ ምልክቶች? በቅርብ ሚገኘውን አስተማማኝ ቦታ ይለዩ፤ ለመጨረሻ ጊዜ ከአደጋ ነጻ የሆነው የነበሩበትን የሚያውቁትን ቦታ ማለትም የተጠረገ መንገድ፣ ብዙ የተሄደበት መንገድ፣ የኮንክሪት ወይም የብረት ስሪት።

**አ** አስተውሉ! የመጡበትን መንገድ ይገምግሙ። ሁሉንም ነገር ለመቆጣጠር ይዘጋጁ።

**ለ** ለዩ! ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ ለመሆኑ ምልክት ካላዩ ወይም የሚረግጡት ቦታ ሌላ ደህንነቱ ያልተረጋገጠ ቦታ ካልረገጡ የማይደርሱበት ከሆነ፤ አይንቀሳቀሱ። እርዳት እስከሚደርስልዎ ይጠብቁ።

- ተሽከርካሪ ፈንጂ ወይም ፈጦቅ ካፈነዳ፤ በተጎጂዎች አእምሮ ወዲያው የሚመጣው ሃሳብ ከመኪና መውጣት ነው። ነገር ግን ተሽከርካሪው በእሳት ካልተያያዘ ወይም ለህይወት አስጊ የሆነ ቦታ ላይ ካላረፈ በተሽከርካሪ ውስጥ ይቆዩ። ምክንያቱም ፀረ-ሰው ፈንጂዎችን ጨምሮተጨማሪ ፈንጂዎች፣ ወይም የሚፈነዱ የጦር ቅሪቶች በቦታው ሊገኙ ይችላሉ። ከቻሉ፤በመኪና ውስጥ የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ ለሚፈልጉ ሌሎች ተጓዦች ይስጡ። በፀጥታ ይቆዩ።
- የጉዞ ማሳወቂያ ካርዶችን አጠቃቀም የሚመለከተው መመሪያ በሚገባ ከተተገበረ፣ ጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ ተገቢ ስልጠና ያለው ባለሙያ እርስዎን ለመርዳት መምጣቱ አይቀሬ ነው። ከሬዲዮ መገናኛ ውጭ ቢሆኑ እንኳን ለአደጋ ጊዜ የሚሆኑ መመሪያዎችን እስከተከተሉ ድረስ በተስማሙበት መርሃግብር መሠረት በጉዳት ወይም በቁሳቁስ ላይ በደረሰ አደጋ ምክያት በሬዲዮ መገናኛ ማረጋገጫ ካልሰጡ፣ የእርዳታ ቡድን እርስዎን ለመርዳት መንገድ ጀምሯል።
- ተሽከርካሪዎን መተው ካለብዎት ግን (ለምሳሌ ተሽከርካሪዎ ቢቃጠል)፣ ወደመጡበት ዞረው እግርዎን የመኪናዎ ጎማ ከረገጠው



ስዕል 4.4
ጉንተላ በጣም አደገኛ አሠራር ነው። ጥሩ ክሂልና ልምድ ይፈልጋል፤ ባልካንስ።
ፎቶ/የጀርመን ኃይሎች



ስዕል 4.5
በአደጋ ጊዜ ብቻ ተሽከርካሪዎን ጥለው ይውጡ፤ በጀርመን ስልጠና ላይ የታየ።
ፎቶ/የጀርመን ኃይሎች

ቦታ ላይ ካላሳረፉ በቀር መሬት አይርገጡ። አስተማማኝ መሬት ላይ እስከሚደርሱ ድረስ ጎማው በተሸከረከረበት ቦታ ላይ ብቻ አየረገጡ ይራመዱ። በተሽከርካሪው ውስጥ ሌሎች ሰዎችም ካሉ በእያንዳንዱ ተሳፋሪ መካከል የ5 ሜትር ርቀት እንዲኖር አድርገው አንድባንድ ለቀው ይውጡ።

- ከማስፈንጠሪያ ሽቦዎችም ይጠንቀቁ። የመኪና ጎማዎች ሺቦዎችን ወደመሬት ስለሚቀብሯቸው ፈንጂዎች ላይፈነዱ ይችላሉ። ወደኃላ ሲመለሱ ሽቦው ለፈናጠር ይችላል።
- ተሽከርካሪውን ከፈንጂ መገኛ ቦታ ለማውጣት የፈንጂ አጽጂ ባለሙያዎች ያግኙ፣ ካልሆነ እዚያው ይተውት።
- አንዴ ከፈንጂ መገኛ ቦታ ከወጡ፤ ሁኔታውን ለሚመለከታቸው ትክክለኛ አካላት ሪፖርት ማድረግዎን ያረጋግጡ።

### 4.1.2.1 ወደኋለ መንዳት

ወደኋላ መንዳት ከፈንጂ መገኛ ቦታዎች ላለመግባት በተነዳበት መስመር ላይ መልሶ ወደተመጣበት አቅጣጫ በመንዳት የመውጣት ስልት ነው። ይህ ዘዴጎማው የሚያርፍበተን ትክክለኛ ቦታ ማነጣጠር ካልቻሉ ወይም የመኪናው ጎማ መጀመሪያ ሲመጣ ያረፈበትን ዱካ ካላወቁት በጣም ለአደጋ የሚያጋልጥ ነው። በመንገዱ ላይ ሌሎች ተሸከርካሪዎችም የሄዱበት እና ሌሎች እንቅፋቶች ያሉበት ከሆነና የመኪናዎ ጎማ ከተነፈሰ አይቻልም ይሆናል።

## 4.2 የተፈፅ ጥቃት የአደጋ ጊዜ መመሪያ

የተፈፅ ጥቃቶች በማንኛውም ቦታ ሊከሰቱ ይችላሉ፤ ነገር ግን ከላይ እንደተገለጸው አንዳንዴ የተወሰኑ ፍንጮች ይኖራሉ። በጉዞዎ ወቅት ተፈፅ ካጋጠመዎ፣ ለጥቃት የሚያጋልጥ ቦታ ላይ ከሆኑ ወይም የጥቃቱ ሰለባ ከሆኑ ለዚህ ጉዳይ በተረጋጋና በአስተማማኝ ሁኔታ ምላሽ መስጠት ተገቢ ነው።



ስዕል 4.6
ብረት ለበስ ተሽከርካሪን ወደመንገድ ዳር መወርወር የሚችል 25 ኪጎ ክብደት ያለው ኤች.ኤም.ኢ፤አፍጋኒስታን ።
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢነኬ





### 4.2.1 ተፈፅ ሲገኝ

ከተፈፅ መሳሪያዎች በተጎጂው ወይም በሌላ ሰው ትእዛዝ የሚሰሩ ሊሆኑ ይችላሉ። በተጎጂው የሚሰሩት ተፈፅ መሳሪያዎች በፈንጂ መገኛ ቦታዎች በሚቆይበት ጊዜ ከሚሆነው ጋር አንድ አይነት ነው፤ ምክንያቱም ተፈፅ በማስፈንጠሪያ ሽቦ፣ በጫና መፍጠሪያ ሰሌዳ ወይም በፀረ-ሰው ፈንጂ ምክንያት ሊቀጣጠል ይችላል። በሌላ ሰው ትዕዛዝ የሚሰሩ ተፈፅዎች ግን የእይታ መስመርና በተጨማሪ ምልክት ማሳያ ይፈልጋሉ። ከተቻለ ለእይታ ግልጽ በሆነ መንገድ አይጓዙ ወይም ራስዎን ይከልሉ። በሁለቱም አገጣሚዎች የሚከተሉትን 5 የ‹የ› እርምጃዎችን መከተል ይገባል፥

**በትእዛዝ የሚሰራ**

**ተፈፅ በርቀት መቆጣጠሪያ አማካኝነት በሌለ ሰው እንዲፈነዳ የሚደረግበት ሂደት ነው። የሚያፈነዳው ሰው ‹ትሪገርማን› ተብሎ ይጠራል።**

**በተጎጂ የሚሰራ**

**ሰው በለዩ ላይ ሲቆምበት ወይም ሲነዳበት የሚፈነዳ ተፈፅ።**

- ያረጋግጡ፥ አይንኩ፣ በአእምሮዎ ብቻ ይመዝግቡ (በዲጂታል ካሜራ)፣ ምልክት ያድርጉ (ከተቻለ) እና ከገቡበት ቦታ ይውጡ። ካስፈንጠሪያ ሽቦ፣ ተጫና መፍጠሪያ ሰሌዳ እና ከፀረ-ሰው ፈንጂዎች ይጠንቀቁ።
- ያሉበትን ቦታ ያጽዱ፥ የማምለጫ ርቀት መሪ መሳሪያውን በመጠቀም (አባሪ A5.1 ይመልከቱ) ወይም ቢያንስ የ300 ሜትር ርቀት)።
- ያሳውቁ፡ ለሚመለከታቸው አካላት (ለመንደር መሪዎች፣ ለፖሊስ፣ ለወታደራዊ መኮንኖች፣ ወይም በቅርብ ለሚገኘው የፈንጂ አጽጂ ተቋም) ጥሪ ያስተላልፉ። መረጃ ለመላክ ባለ ዘጠኝ መስመሩን ሪፖርት ማድረጊያ ይጠቀሙ (አባሪ A5.2ን ይመልከቱ)።
- ያግዱ፥ ተሽከርካሪዎች እና እግረኛ ተጓዦች ወደ ተፈፅ እንዳይቀርቡ ይከልክሉ።
- ያቅቡ፥ የሚመለከታቸው አካላት በቦታው እስኪደርሱ አካባቢውን ይቆጣጠሩ።

ራስዎን መጠበቅ ጠቃሚ ነው። የአካባቢውን ህዝብ ባህርይ ያጢኑ፣ እንዲሁም ከሁለተኛ ደረጃ ተፈፅዎች እና በተርታ ተፈፅ ይጠንቀቁ።[13]

[13] ተርታ ተፈፅ የሚባሉተ የተለዩ አይነት ተፈፅ ሲሆኑ ከአንድ በላይ ማስነሻ ቻርጅ ያላቸውና በመደዳ (በሜትር እስከ መቶዎች ሊደርሱ ይችላሉ) ተቀምጠው በአንድ ቁልፍ አማካኝነት የሚፈነዱ ናቸው።

## 4.2.2 የተፈፅ ፍንዳታ

ባልታወቀ ወይም በተፈፅ ፍንዳታ ጊዜ ራስዎን ከአደጋ መጠበቅ ያስፈልጋል። ሁለተኛ ተራ ተፈፅ እንዲሁም የፈነዳው መሳሪያ አደጋ ካደረሰባቸው ዕቃዎች (የሚቃጠል መኪና፣ የሃይል ማስተላለፊያ መስመር) ዋና የአደጋ ስጋት ፈጣሪዎች ናቸው። ስለዚህ ራስዎን በ5/25ሜ መስፈርት (በአባሪ ሀ3 በተገለጸው መሠረት) ዙሪያዎን ከአደጋ ይጠብቁ። ከዚህ በኋላ 5ቱን የ‹የ› እርምጃዎች ይከተሉ፥

- ያረጋግጡ፥ ሁኔታውን ሁሉ ከአደጋ ነጻ ከሆነ ቦታ ላይ ሆነው ያጣሩ።
- ያሉበትን ቦታ ያጽዱ፥ የማምለጫ ርቀት መሪ መሳሪያውን በመጠቀም (አባሪ A4.1 ይመልከቱ) ወይም ቢያንስ የ300 ሜትር ርቀት)።
- ያሳውቁ፡ ለሚመለከታቸው አካላት (ለመንደር መሪዎች፣ ለፖሊስ፣ ለወታደራዊ መኮንኖች፣ ወይም በቅርብ ለሚገኘው የፈንጂ አጽጂ ተቋም) ጥሪ ያስተላልፉ። መረጃ ለመላክ ባለ ዘጠኝ መስመሩን ሪፖርት ማድረጊያ ይጠቀሙ (አባሪ A5.2ን ይመልከቱ)።



**ስዕል 4.7**
**በተፈፅ የተቃጠለ ተሽከርካሪ ቅሪት አካል፤ አፍጋኒስታን።**
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢነኬ



4.2 የተፈፅ ጥቃት የአደጋ ጊዜ መመሪያ
4.2.2 የተፈፅ ፍንዳታ

- ያግዱ፥ ተሽከርካሪዎች እና እግረኛ ተጓዦች ወደ ተፈፅ እንዳይቀርቡ ይከልክሉ።
- ያቅቡ፥ የሚመለከታቸው አካላት በቦታው ደርሰው ብድኖችን እስኪያድኑ ድረስ አካባቢውን ይቆጣጠሩ።

ወደ ፍንዳታ ቦታ ሮጠው አይሂዱ። ማንኛውንም የተፈዐ ፍንጣሪ ወይም ኢላማ አይንኩ። ለሚመለከታቸው አካላት ያገኙትን ነገር ያሳውቁ።



**ሊባኖስ**
የተመሬአ ፎቶ/ማርክ ቫይላንት

# ክፍል 5

# የአደጋ ተጎጂን መርዳት




ሊቢያ


የተመረመአ ፎቶ/ጂዮቫኒ ደፊደንቲ

# የአደጋ ተጎጂን መርዳት

ከዚህ በላይ የተገለጸውን የመሰለ አደጋ እንደተከሰተ በሚያዩበት ጊዜ፣ ለአደጋ ከማያጋልጥ ቦታ ላይ ሆነው ሌሎችን መርዳት ሊፈለግብዎ ይችላል። ይህ ክፍል አደጋ ሲደርስ በሚያዩበት ጊዜ ሌላ ርዳታ ሰጪ አካል በሌለበት ሁኔታ ሊተገብሯቸው የሚገቡ መሠረታዊ ተግባራትን ይዟል። ይህ ክፍል የድንገተኛ አደጋ የመጀመሪያ እርዳታ አሰጣጥ ስልጠናን የሚተካ፣ ወይም የህክምናና የፈንጂ አጽጂ ባለሙያዎችን ለማሰልጠን የሚውል አይደለም።

አደጋ ሲደርስ ባዩ ጊዜ የሚከተሉትን ተግባራት እንዲፈጽሙ ይመከራሉ፥

- በፀጥታ ይጠብቁ!
- ቸኩለው ወደ ተጎጂው አይሂዱ።
- በፈንጂ መገኛ ቦታ ወይም በሌላ ለደህንነት አስጊ በሆነ ቦታ ላይ ሆኖ/ሆና ለማዳን አይሞክሩ።
- ከተጎጂው ጋር ይነጋገሩ፤ እንዳይንቀሳቀስ ያስጠንቅቁት፤ እንዴት ለራሱ የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ መድረግ እንደሚችል ይምከሩት፤ ተጨማሪ እርዳታ እየመጣለት እንደሆነ ይንገሩት።
- ጊዜውን፣ ቦታውንና የተጎጂዎችን ቁጥር ልብ ይበሉ።
- የእርዳታ ጥሪ ያቅርቡ። ቦታውን ከመሳሪያ ለማጽዳትና ሰዎችን ለህክምና ለማውጣት ሁኔታዎችን ያመቻቹ። ባለዘጠኝ መስመሩን (አባሪ ሀ5.2) ይጠቀሙ።
- የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ መሳሪያን ዝግጁ ያድርጉ።
- እርዳታ እስኪደርስ ይጠብቁ።



ስዕል 5.1
የእርዳታ ጥሪ፡ የኤመ. አይ.ኤን.ዩ.አር፤ኤስ፤ኦ ወታደራዊ መኮንኖች ስማራ ላይ የስልጠና ልምምድ ላይ። የማገገሚያውን ቦታ ልብ ይበሉ፤ የምእራብ ሰሃራ ግዛት።
የተመድ ፎቶ



## 5.1 ምንነቱ ካልታወቀ ፍንዳታ ቦታ መውጣት

በፍንዳታ ምክንያት አደጋ ሲደርስ ተጎጂው ከአደጋ ነጻ ያልሆነ ቦታ ውስጥ ነው የሚገኘው።

በዚህ ጊዜ የመታደጊያ አማራጮች በጣም ውስን ናቸው። ተጎጂው ህክምና ከማግኘቱ በፊት በፈንጂ አጽጂ ቡድን ወይም በሚፈነዱ ጦር መሳሪያዎች አስወጋጅ ቡድን አማካኝነት ከቦታው መውጣት አለበት። የእርዳታ ጥሪ በሚያቀርቡበት ጊዜ፣ ለፈንጂ ማጽዳት፣ ለሚፈነዳ መሳሪያ ማስወገድ ወይም ለመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይኖርብዎታል። ስለዚህ የተሟላ የአደጋ ጊዜ አድራሻ (የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ፣ የጥሪ ምልክት፣ የስልክ ቁጥር ወዘተ.) እና ባለዘጠኝ መስመር ማስታወሻ (አባሪ ሀ5.2) መያዝዎን ያረጋግጡ።

ተጎጂው በፈንጂ መገኛ ቦታ ወይም ያልፈነዳ መሳሪያ ከሚገኝበት ቦታ ከሆነና ተጎጂውን ከስፍራው ሊያወጣ የሚችል የፈንጂ አጽጂ ቡድን የማይገኝ ከሆነ የጉንተላ ዘዴ ተጎጂውን ከቦታው ለማውጣት ሊያገለግል ይችላል (ክፍል 4ን ይመልከቱ)።

በተፈፅ ፍንዳታ ጊዜ የሁለተኛ ተፈፅ ስጋት ወይም የሌላ አይነት ጥቃት (ለምሰሌ የአልሞ ተኳሽ) የማጋጠሙ እድል በጣም ከፍተኛ ነው። ስለዚህ አካባቢውን (ለእይታ ግል የሆነውን መስመር) በጥንቃቄ ይመርምሩ። ወደ ፍንዳታው የሚያስገባውን መንገድ 5/25ሜ (አባሪ ሀ3 ይመልከቱ) በመጠቀም በማሰስ ለመውጣት አስተማማኝ የሆነ መንገድ ይፍጠሩ። ከሌሎች ለያጠቁ ከሚችሉ አካላት እይታና ከተጨማሪ ፍንዳታ ለመከላከል ከለላ ይጠቀሙ። ተጎጂውን ከመርዳትዎ በፊት ቦታውን በጣም ተጠንቅቀው ይፈትሹ።

አደጋው ከፊት ለፊት አየመራ በሚሄድ መከና ላይ ከደረሰና እርስዎ ከኋላ ያለ መኪና ላይ ከሆኑ፣ አደጋ የደረሰበት መኪና በቆመበት ቦታ ላይ ብቻ እየተራመዱ ወደ ተጎጂዎች ሊደርሱ ይችላሉ። ነገር ግን የፀረ-ተሸከርካሪ ፈንጂው ወይም የተፈፀ ፍንዳታ መኪናውን ገልብጦ ከመንገድ ሊያስወጣው ይችላል። እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ ከመንገዱ ውጭ ያሉ ቦታዎች የፈንጂ መገኛ ሊሆኑ ስለሚችሉ ወደነሱ አለማለፍ ይገባል።

## 5.2. የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ አሰጣጥ

ተጎጂው አንዴ አስተማማኝ ወደሆነ ደህና ቦታ ከወጣ በኋላ፣ ምንም አይነት የህክምና ባለሙያ በቅርብ ከሌላ፣ የህክምና እርዳታ እስከሚደርስ ድረስ በወሰዱት ስልጠና ያገኙትን ዕውቀት ሁሉ ተጠቅመው የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ ሊያደርጉ ይገባል።

የ‹‹ደመት›› ህግ ተከትለው የጀርባ አጥንት (ህብለሰረሰር) ጉዳት መኖሩን እና ይገምግሙ፣ ከተቻለ ራሱንም ያስተካክሉ[14]፥

| | |
|---|---|
| **ደ**ም ዝውውር | የሚፈሰውን ደም ያቁሙለት |
| **መ**ተንፈሻ | የአየር መተንፈሻ ክፍሎች እንዳይዘጉ ይቆጣጠሩለት |
| **ት**ንፋሽ | የመተንፈስ እገዛ ያድርጉለት |

የሚፈስ ደም ካለ ይፈልጉ። የሚፈሰውን ደም ይለዩና ያስቁሙት። በተደጋጋሚ የሚከሰተውን ማስቀረት የሚቻለው ዋና የሞት ምክንያት እስከሞት ድረስ መድማት ነው። የሚፈስ ደምን ለመቆጣጠር ከቀጥተኛ ግፊት ይልቅ ኢቀጥተኛ (ተዘዋዋሪ) ግፊት ይጠቀሙ፤ የሄሞስታቲክ ኤጀንቶችን መጠቀም ካስፈለገ ደግሞ ቶርንኪት ሊጠቀሙ ይችላሉ። በሰውነት ጫፍ ላይ የሚገኝ የደም መፍሰስ ለጊዜው ቶርንኪትን በመጠቀም በቀላሉና ቶሎ ማቆም ይቻላል። ከተቻለም በተጨማሪነት




ስዕል 5.2
የሚፈስን ደም ማቆም አስፈላጊ ነው።
የተመድ ፎቶ




ስዕል 5.3
ራስ ዘንበል/አገጭ ቀና።
የተመድ

[14] የሚከተሉት ፍንጭዎች በተመድ ውስጥ በፀጥታና ደህንነት ዲፓርትመንት ከሚሰጠው የኢ.ቲ.ቢ- ስልጠና የተወሰዱ ጽሁፎች ናቸው።





አናናልግስቲክ መገልገል ይቻልል፤ ምክንያቱም የቶርንኪቱ ህምም ከጉዳቱ ህምመት ሊበልጥ ይችላልና። ቶርንኪት ጥቅም ላይ የዋለበትን ሁኔታና ጊዜ በተጎጂው ሰው ግንባር ላይ በሚለጠፍ ማስታወሻ ውሃ በማያስለቅቀው እርሳስ ጽፎ ማመልከት የግድ ነው። ቶርንኪተ ለ6 ሰዓታት ያህል ሊያገለግል ይችላል። በአንናነድ ሁኔታዎች ደግሞ እስከ 16 ሰዓታት ሊያገለግል ይችላል። እስዚህ ጊዜ ድረስ ቶርኪቶችን መከፈት የሚቻለው ከተጨማሪ ህክምና ጋር ብቻ ነው![15]

ቶርንኪቶች የማይገኙ ከሆነ፣ ልብሱን ያነሱና ቁስሉን ይግለጡት። በእግር እና ቅልጥም ላይ ለደረሰ ጉዳት በዳሌ አካባቢ ፣ በእጅና ክንድ ላይ ለደረሰ ጉዳት ደግሞ ብብት ውስጥ ያለውን የደም ስር ይጫኑ። ቁሰሉን ተጭኖ ለማሰር ማንኛውንም አይነት የተገኘውን ማሰሪያ ይጠቀሙና ቁስሉን በጨርቅ ደህና አድርገው ይሰሩት። አሁንም ደሙ ከታሰረበት ጨርቅ አልፎ ከመጠ ተጨማሪ ልብስ ይጨምሩና ይሰሩትና በደም ስሩ ላይ ጫን አድርገው ይያዙት።

የመተንፈሻ አካሉ በምንም አይነት ባዕድ ነገር እንዳልተዘጋ ያረጋግጡ። ተጎጂው ራሱን የማያውቅ ከሆነ ራሱን ዘንበል ከአገጩ አድርጎ ቀና በማድረግ የአየር መተንፈሻ አካላቱን ይክፈቱለት። ብዙ ተጎጂ ባለበት ብዙ ቁስለኞችን በፍጥነት መርዳት ካለብዎትና የሚቻል ከሆነ የመተንፈሻ ቱቦዎች (ኦሮፋሪነጂያል ኤይርዋይስ) ያስገቡለት።

ቁስለኛው ራሱን የሚያውቅ ከሆነ፣ አየተነፈሰ መሆኑን በማየት፣ በማዳመጥና በመዳሰስ ያረጋግጡ። ይህንንም ከ10 ለማይበለጡ ሰከንዶች ያድርጉ። በአጥሩ የአተነፋፈሱን ፍጥነት፣ ሃይልና ድምጽ ይገምግሙ። ደረቱ ከሁለቱም ጎን እኩል እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ያረጋግጡ።

ተጎጂው መልስ የሚሰጥ መሆኑን ይገምግሙ። በዚህ ረገድ አራት አይነት ደረጃዎች አሉ፥

- ንቁና ግንዛቤ ያለው፡ ተጎጂው ስለ ሰዎች፣ ቦታዎች፣ ጊዜ እና ክስተቶች ግልጽ መልስ የሚሰጥበት፤

[15] ኔትዜል፣ ላዶልፍ፡ ታክቲሽ ሜዲሲን፣ ስፕሪንገር 2012

- ትዕዛዝ ብቻ ሰሚ፡ ተጎጂው በቃል ለሚነገሩት ትእዛዞች ብቻ በድርጊት ምላሽ ይሰጣል። (“አይንህን ግለጽ”, “ጣትህን አንቀሳቅስ”)፤
- ለሚሰማው ህመም ብቻ የሚመልስ፡ ቁስለኛው ሲቆነጠጥ ወይም የሚያመው ቦታ ሲዳሰስ ብቻ በድምጽ ምልሽ የሚሰጥበት፤
- ምላሽ አልባ፥ ተጎጂው ለቃልም ይሁን ለህምም ስሜት ምንም ምላሽ የማይሰጥበት።

የጀርባ አጥንት (ህብለ ሰረሰር) ጉዳት መኖሩን እንደገና ይመርምሩ። ተጎጂውን ይጠይቁ ‹‹ምንህ ጋ ነው የተጎዳኸው፣ እጅህንና አግርህን ማንቀሳቀስ ትችላለህ?››። ከተቻለ የአንገት ድጋፍ ያጥልቁለት።

የሰውነት ሙቀታቸው ዝቅተኛ የሆኑ ሰዎች ብዙ ደም የመፍሰስ ችግር ያደላባቸዋል። ቁስለኛውን ነፋስ፣ ዝናብና ብርድ እንዳያገኘው ይንከባከቡት። ሙቀትና ፀጥታ ባለበት ቦታ ያስቀምጧቸው። ሆኖም ግን ለጸሃይ ብርሃን መጋለጥ የለባቸውም። ከበረደውና ከነውጥ (ሾክ ውስጥ ከሆነ) ተጎጂውን የድንገተኛ አደጋ ብርድ ልብስ ያልብሱት። በትክክለኛው አቀማመጥ ያስቀምጡት። ምቹና ለስላሳ ልብስ ያልብሱት። ያናግሩት፣ ምን አያደረጉ እንደሆነም ያስረዱት። ተጨማሪ ርዳታም አየመጣ እንደሆነ ይንገሩት።

የዳግም ቅኝት ካደረጉ በኋላ፣ የባሰባቸውን በየተወሰነ ጊዜ እየተመላለሱ ይቆጣጠሩ።

ተጎጂው መነጋገር የሚችል ከሆነ ፣ ማለትም የመተንፈሻ አካሉ ካልተዘጋ ሀይፖትርሚያን (የሰውነትንሙቀት መቀነስን) ለመከላከል ለብ ያለ ውሃ ወይም ሌላ አልኮል የሌለበት ፈሳሽ በትንሹ ፉት እንዲል ያድርጉት።

ተጎጂውን አንዴ መኪና ላይ ከጫኑ በኋላ፣ ከሁሉም የበለጠ ቅርብ ወደሆነው የህክምና ተቋም በቀጥታ በመንዳት ያድርሱት። በቅርብ የተገኘውን የተሸለ ትራንስፖርት ይጠቀሙ። የተሻለና ፈጣን ትራነስፖርት ቆይቶ የሚመጣ ከሆነ እንዲከተልዎና እንዲደርስብዎ መመሪያ ስጡት።



5.2 የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ አሰጣጥ

በትራነስፖርት በሚወስዱበት ጊዜ በየተወሰነ የጊዜ ርቀት የተጎጂውን ደህንነት ማለትም በጉዞ ቁስሉ የታሰረበት እስራት በትክክል መቀመጡን ያረጋግጡ። የደም መፍሰስን ለመቆጣጠር የሚደማውን ነገር በጉዞ ወቅት በእጅ ተጭኖ በያዝ መቀጥል ይችላል።



ሊቢያ

የተመፈመአ ፎቶ/ጂዮቫኒ ደፊደንቲ



**የኮንጎ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ**

የተመረመአ ፎቶ

# አባሪዎች

# አባሪዎች

## አባሪ ሀ1 የጉዞ ካርዶች አጠቃቀም

### ሀ1.1 የሠራተኛን ጉዞ መከታተያ ስልት

የጉዙ ካርዶች አሰራር ን በሚገባ መጠቀም ሰራተኞች ከቦታ ቦታ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ለማወቅና ለመከታተል ውጤታማ ዘዴ ከመሆኑም ባሻገር ሰራተኞቹ በሄዱበት ቦታ መድረስ ወይም የተቀጠረላቸውን ሰዓት ባይጠብቁ ትክክለኛ እርምጃ ከመውሰድ ረገድ እገዛ ያደርጋል። ለምሳሌ የሚሆን የጉዞ ካርድ ከዚህ በታች ቀርቧል።

የጉዞ ካርዶች መሞላት ያለባቸው ወደ አደገኛ ቦታዎች በሚሄደውበ በተጓዥ ሠራተኛ ሆኖ ጉዞውን ለመከታተል ኃላፊነት በተሰጠው ሠራተኛ እጅ ይቀመጣል።

ለጉዞ ክትትል የተመደበው ሠራተኛም ካርዱን ሲቀበል ለመቀበሉ በፊርማ ያረጋግጣል። ካርዱን በየቀኑ ማየትና ማረጋገጥ በሚቻልበት በሚታይ ቦታ፣ በማስታወቂያ ሰሌዳ፣ ላይ ያስቀምጣል።

ካርዱን ተቀብሎ ለመከታተል የተመደበው ሰው የተጓዘው ሠራተኛ በሰጠው ግምታዊ የመድረሻ ሰዓት መመለስና አለመመለሱን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት። ካልደረሰም፣ የሠራተኛውን አለመድረስ የሱ የበላይ ለሆነና የሠራተኛውን ጉዞ የመከታተል ኃላፊነት ላው ባልደረባ ሪፖርት ያደርጋል።

የተጓዘው ሠራተኛም መመለሱን ሪፖርት ማድረግ አለበት። ከዘገየም የዘገየበትን ምክንያት እና አዲሱን ግምታዊ የመድረሻ ሰዓት ማሳወቅ አለበት።



ስዕል A1.1
መንገድን ማጽዳት፣ ደቡብ ሱዳን።
የተመድ ፎቶ






ጉዞው ከተጠናቀቀ በኋላ፣ የጉዞው ካርድ ለመከታተል በተመደበው ሰው ይፈረምና ከማስታወቂያ ሰሌዳ ተነስቶ ፋይል ይደረጋል።

ጦርነት ባለበት አካባቢ የሚፈነዳ የጦርነት ቅሪትን የሚያመለክቱ የጉዞ ካርዶች በአካባቢው ወዳለ የፈንጂ መከላከል ማዕከል ወይም ሌላ የሚመለከተው ባለስልጣን ሊላክ ይገባል።

### ሀ1.2 የጉዞ ካርድ


A1.2 –
Route Card
MISSION SECURITY CLEARANCE REQUEST • UNITED NATIONS
Number of vehicles
Team Leader's Name
Purpose of visit
Agency
City
Date
Hour
1. DEP
ARR
2. DEP
3. DEP
4. DEP
Plate No.
Phone No.
Agency
HF Call Sign
HF Frequency
Name
Call Sign

## ሀ1.3 የመንገድ ላይ እንቅስቃሴ መመሪያ

የሚከተለው ዶክመንት ቅንጫቢ ብቻ ነው፤ ስለፈንጂ/ስለአልፈነዳ ጦር መሳሪያ/ስለተፈፀ መሆኑ ተብሎ የተወሰነ አይደለም። ዶክመንቱ በዩኒሴፍ የተበረከተ ነው። ከጉዞ ካርድ ጋር የተዛመደ ነው (ያለፈውን ገጽ የመልከቱ)።

### ሀ1.3.1 የመንገድ ጉዞ ቅድመ ዝግጅት

ጥብቅ/አስተማማኝ ናቸው በሚባሉ ቦታዎች እንኳ ሳይቀር በተሽከርካሪ መጓዝ በመካኒካል ችግር፣ በግጭትነና መገልበጥ አደጋ፣ በተራ ወንጀሎች እና በመኪና ስርቆት ምክንያት በሚፈጠር ችግር አደጋ የበዛበት ነው። ይህ አደገኛነት ግን ፣ ከተቻለ፣ ከሌሎች ተሽከርካሪዎች ጋር በቡድን በመሄድ ሊቀንስ ይችላል።

#### ሀ1.3.1.1 የቡድን መሪ ኃላፊነቶች

ማንኛውም የመንገድ ተልዕኮ ተልዕኮውን የሚያስተባብርና የሚመራ አንድ ሰው ያስፈልገዋል። ይህ ሰው «የቡድን መሪ» ተብሎ ይታወቃል። የሚከተሉት ተግባራት ጉዞ ከመጀመሩ በፊት ሊከናወኑ ይገባል፥

- ለጉዞ የሚያገለግሉ ተሽከርካሪዎች የተሟላ ዝርዝር የምዝገባ (ታርጋ) ቁጥራቸውን፣ የእያንዳንዱ ተሽከርካሪ ሹፌር፣ በቡድን ጉዞው የእያንዳነዱ ተሽከርካሪ ተራ ማዘጋጀት፤
- የኤሌክትሮካውንተር መለኪያ (ኢ.ሲ.ኤም) ጥቅም ላይ ከዋለ፣ የእያንዳነዱን ተሽከርካሪ ተራ የሚያሳይ ዕቅድ በማውጣት የኢ.ሲ.ኤም አረፋዎች ከብድኑ ጋር እንዲገጥሙ ማድረግ፤
- በቡድን ጉዞው የሚሳተፉ ሰዎችን የተሟላ ዝርዝር ያዘጋጁ፣ ኃላፊነትም መስጠት፤
- ለመንገዱ ፀጥታ ማረጋገጫ መገኘቱን ማረጋገጥ፤
- የሚጎበኙ ቦታዎችን በሚመለከት አሁን ያሉበትን ሁኔታ (መለከዓምድር፣ የአየር ሁኔታ፣ የሚገኙ አገልግሎቶች፣ በመንገድ ላይና በመድረሻው ቦታ ችግር ቢያጋጥም የሚጠሩ ሰዎች ዝርዝር ወዘተ.) የሚመለከት የተሟላ መረጃ መኖሩን ማረጋገጥ፤
- ወዳንድ ቦታ ጉዞ በሚደረግበት ጊዜ፣ በአካባቢው ተሰሚነት ካላቸው አካላት ጋር (የመንደር መሪዎች፣ ፖሊስ፣ የጦር መኮንኖች፣ በቅርብ ያለ የፈንጅ አጽጂ ድርጅት ወይም ህብረብሄራዊ የሚፈነዳ ፈንጅ በማስወገድ/ብሄራዊ የሚፈነዱ ነገሮች በማስወገድ የተሰማሩ ሰላም አስከባሪ- ታዛቢ- አሰልጣኝ- የልዩ ተልእኮ ቡድኖች) ስል ጉዞውና ስለአካባቢው የፀጥታ ሁኔታ መነጋገር፤
- በአደጋ ጊዜ የሚገለገሉባቸው መመሪያዎች(ለምሳሌ ለህክምና መውጣት የሚሆኑ) ዝግጁ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤
- በፀጥታ ኃይሎች መታጀብ የሚያስፈልግ መሆኑን መወሰን። አጀብ ካስፈለገ በተቻለ መጠን አስቀድሞ ግን ቢያንስ ከጉዞው መነሻ 48 ሰዓት አስቀድሞ መጠየቁን ማረጋገጥ፤
- በመኪና ውስጥ በተሳፋሪዎች መካከል የሚኖር ጠርዝና ቅኝት አንዲኖር ማድረግ፤
- ለተሳፋሪዎች ሁሉ ሰለጉዞው ገለጻ መስጠት።

#### ሀ1.3.1.2 የጉዞ ዕቅዱን ማጎልበት

ለጉዞ ከመነሳት በፊት በተቻለ መጠን ስለ ጉዞው ብዙ መረጃ መሰብሰብ አስፈላጊ ነው።

- ምርምር ያድርጉ። ስለ መንገዱ ሁኔታ የሚቻለውን መረጃ ሁሉ ይሰብስቡ። በዚያ መንገድ በቅርብ የሄዱትን ሰዎች ያነጋግሩ፤
- የፀጥታ ስጋት ሊሆኑ ስለሚችሉ ችግሮች ወቅታዊ የሆነ መረጃ ይኑርዎት፤
- የሚሄድበትን መንገድ ልኬት (ርቀት) ይከፋፍሉትና እያንዳነዱ ክፍል የሚደረስበትን ሰዓት ይገምቱ። ተጓዡ ቡድን ለእረፍት የሚያርፍበትን ቦታ አስቀድመው ይወስኑ፤
- አደጋ፣ ብልሽት ቢያጋጥም ሊተገበር የሚችል (ቀላል) የመጠባበቂያ እቅድም እንዲሁ ያዘጋጁ።

- የሚተገበረውን እቅድ ለማቋረጥ ምን እንደሚደረግ የሚያሳይ አሠራር በእቅዱ ውስጥ ሊካተት ይገባል፤
- ከጨለመ በኋላ አይጓዙ። በመንገድዎ እደርስበታለሁ ብለው ያቀዱት ቦታ ላይ በጊዜ (ሳይመሽ) መድረስ እንደሚችሉ ያረጋግጡ፤
- የመኪናዎ ክብደትና ከፍታ በድልድዩ/ማሹለኪያ ቦታ ከተቀመጠው ልክ እንደማያልፍ ያረጋግጡ፤
- ተጓዥ ቡድኑ ለጉዞ ከመነሳቱ በፊት ማብራሪያ እንደተሰጠው ያሳውቁ።



ስዕል A1.2
በትንሽ ወንዝ ላይ የሚገኝ አነሸራታች መሬት፤ ደቡብ ሱዳን

የተመድ ፎቶ

### ሀ1.3.1.3 መገናኛዎች

በመንገድ ላይ የሚያገለግሉ የተመድ መኪናዎች የኤች. አፍ. እና የቪ.ኤች. ኤፍ. ሬዲዮ አላቸው። በቡድን ጉዞ፣ የኤች. ኤፍ. እና የ ቪ.ኤች. ኤፍ. ሬዲዮ ሊኖር ይገባል። የቪ.ኤች. ኤፍ. ሬዲዮው ቀላል ቻነል የሚሰራ ሊሆን ይገባል። [ ይህ ዘዴ ከቪ.ኤች. ኤፍ ሬዲዮ ወደ ቪ.ኤች.ኤፍ ሬዲዮ በቀጥታ የሚደርግ ግንኙነት ነው- በዚህ እሳቤ ከአንድ ተሽከርካሬ ወደሌላው ተሽከርካሪ ማለት ነው።][16]

ጉዞ ከመጀርዎ በፊት፤ የሚከተለው የመገናኛ እቅድ አስፈላጊ ነው፥

- የሬዲዮ መገናኛውን ይፈትሹ። የመጀመሪያውና የመጨረሻው መኪናዎች የሬዲዮ መገናኛ ያላቸው መሆኑን ያረጋግጡ፤
- የኤሌክትሮኒክ ካውንተር ሜዝር የሬዲዩ መገናኛን ያውካል። ተጨማሪ የመግባቢያ ምልክቶች መብራቶች ወይም እጅ/ባንዲራ ሊዘጋጅ ይገባል፤
- የሬዲዮ ሞገድን ልክ (ፍሪኬንሲ) ይሞክሩ፤
- ከዋና ጣቢያው ጋር የሬዲዮ መሞከሪያ ጊዜ መርሃግብሩን ይጠብቁ፤
- የማንኛውም የመገናኛ ጥሪ ምልክቶችን፣ የሞባይል ጥሪ ቁጥሮችን[17]፣በሚገባ ማወቅዎንና ሌሎችንም የሚያስፈለጉ ልዩ መመሪያዎችን በሚገባ ማወቅዎን ያረጋግጡ፤

[16] «ሲምፕሌክስ»፡-ማስተላለፉ በ«ሪፒተር» ውስጥ አያልፍም እንዲሁም የሚጠቀመው አንድ ፍሪኩየንሲ ብቻ ነው። «ዱፕሌክስ» አንድ ለመቀበልና አንድ ለመላክ በአጠቃላይ ሁለት ፍሪኩየንሲዎችን ይጠቀማል። ይህ ስርዓት በሪፒተር ስለሚያልፍ ለቪኤችኤፍ ረጅም ሽፋን ይሰጠዋል።
[17] ልካል - የራስ ጥሪ፣ እያንዳንዱን ሬድዮ ለመጥራት የሚጠቀም ቁጥር –ብዙ ጊዜ ከሌላ ቪኤችኤፍሬድዮ።





- በሬዲዮ መገናኛዎች ላይ የሚሠሩ ሠዎች ከላይ የተጠቀሱትን ነገሮች በሙሉ እንዲሁም በሬዲዮ ሲያስተላልፉ በግልጽና በአጭሩ ማውራት እንዳለባቸው ማወቃቸውን ያረጋግጡ፤
- የሬዲዮ መገናኛዎች ጉዞ ከመጀመሩ በፊት ነው መዘጋጀት (መቋቋም) ያለባቸው። እንዲሁም የሬዲዮ-መገኛ ሪፖርቶች (እንደያመቺነቱ) ታዋቂ ቦታ በታለፈ (በተደረሰ) ቁጥር በየሰዓቱ መላክ ይኖርባቸዋል። ዋናው ጣቢያ በተሽከርካሪ ወይም በኤጀንሲ አማካኝነት እያንዳንዱ ሪፖርት ሊደርሰው ይገባል። ጉዞው ሲጠናቀቅም ለዋናው ጣቢያ ማሳወቅ ያስፈልጋል።

### ሀ1.3.1.4 የአሽከርካሪ ኃላፊነትና ተሽከርካሪ ማሟላት ያለበት መስፈርት

ዓለምአቀፍ ተልዕኮዎች ሁለት ተሳፋሪ ብቻ የመይዙ ዝቅተኛው የደህንነት ደረጃዎችን ያሟሉ ተሽከርካሪዎች ይፈልጋሉ። 18 በብሄራዊ ደረጃ ያሉ ሠራተኞች ግን፣ አብዛኛውን ጊዜ፣ ሶስት ሰዎች ቢሳፈሩበት በሚመረጥ ዝቅተኛውን ደረጃ ባሟላ አንድ ተሽከርካሪ ይጓዛሉ። ሆኖም አንዳንዴ ባለሁለት ተሳፋሪ ዝቅተኛውን ደረጃ ያሟላ አንድ ተሽከርካሪ ለብሄራዊ ደረጃ ሠራተኞች ግዴታ የሚሆንበት ጊዜ አለ፤ የፀጥታው ሁኔታ የሚያስገድድ ከሆነና በብዙ ድርጅቶች ስብሰባ የተወሰነ ከሆነ። በቡድን ጉዞ የሚያገለግሉ መኪናዎች በሚገባ ጥበቃ የተደረገላቸውና ለመንገድም ብቁ መሆን አለባቸው። ሠራተኞችም፥

- ሁሉም ተሽከርካሪዎች ለሚሄድበት መልከዓምድር ተስማሚ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፤
- ሁሉም ተሽከርካሪዎች በትክክል ምልክት የተደረገባቸው መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው (ለምሳሌ የተመድ ባንዲራና አርማ መጠቀም መቻሉን መወሰን)፤
- እያንዳንዱ መኪና የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ መስጫ፣ የእሳት ማጥፊያ፣ የውሃ ጀሪካን፣ ነዳጅ ጀሪካን፣ ተለዋጭ ጎማ፣ ጃክ እና ተፈላጊ መሳሪያዎች የተሟሉለት መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፤

[18] ኤምኦኤስኤስ፥ ዝቅተኛው የደህንነት አሰራር መስፈርት የዩናይትድ ኔሽን የፖሊሲ ሰነድ። የኤምኦኤስኤስ ጥቅም የዩኤን የመስክ ተግባራትን ለማከናዎን የሰራተኞችን ደህንነት ከፍ ለማድረግና ችግርን ለመቀነስ ዝቅተኛ መስፈርት ማስቀመጥ ነው።

- ተሽከርካሪዎች ለጉዞ በጥሩ ሁኔታ ላይ መሆናቸውን ማረጋገጥ እና ሁሉም ጥገና እና ጎማ ለመቀየር የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ መሟላታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፤
- ሁሉም ተሽከርካሪዎች ጉዞ ሲጀምሩ ነዳጃቸው ሙሉ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፤
- ተጓዡ ቡድን ለማስተባበር የማያስቸግር መሆኑን፣ አጃቢዎች የሚያስፈልጉ ከሆነም ካሉት አጃቢዎች ብዛት ጋር ተመጣጣኝ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፤
- የሽብርተኝነት/የጦርነት ሥጋት ባለባቸው አገሮች ግጭት ባለባቸው ወይም በሌሎች አደገኛ ቦታዎች አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች የሚከተሉትን ተጨማሪ ነገሮች ማሟላት አለባቸው፥
    - ለአሽከርካሪውና ለተሳፋሪዎች ለእያንዳነዳቸው የተሟላ ብረት ጠብረት ልብስ፤
    - ቦሊስቲክ ብርድልብስና ከመኪናው መስታወት ጋር የሚገጠም ፍንዳታ የሚቋቋም ስፋን፤
- እንደየ ስጋት ምንጩ ተፈፅ አይነት፣ ማፈኛ መሳሪያም ሊያስፈልግ ይችላል።

#### ሀ1.3.1.5 ገለጻ

ለሁሉም የጉዞ ተሳታፊዎች ስለ ጉዞው ሁኔታ/ተልእኮ ጉዞው ከመጀመሩ በፊት እንደሚከተለው ገለጻ ሊደረግላቸው ግድ ነው፥

- ለተሳታፊዎች በሙሉ የየራሳቸውን ኃላፊነት መገንዘባቸውን፣ የቡድን ጉዞውን መመሪያ እና ተለዋጭ (መጠባበቂያ) እቅዶችን በሚመለከት ገለጻ መስጠት፤
- የቡድኑ የጉዞ ፍጥነት ከመንገዶቹ ሁኔታና ከዘገምተኛው ተሽከርካሪ ጋር ትክክልኛ መሆኑን ማረጋገጥ አላባቸው፤
- በመኪና ውስጥ በሚገኙት ተጓዦች መካከል ለቅኝት የሚሆኑ ክፍት ቦታዎችና ማዕዘኖች መኖራቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፤



ሀ1 የጉዞ ካርዶች አጠቃቀም
ሀ1.3 የየመንገድ ላይ እንቅስቃሴ መመሪያ

- የመንገድ ትራፊክ ህግጋትንና ባህርይ በሚመለከት ምክር መስጠት አለባቸው፤
- ሊደርሱ ስለሚችሉ አደጋዎች/ጉዳቶች መናገር አለባቸው፤
- ስለሚከተሉት ነገሮች መመሪያዎችን መስጠት አለባቸው፥
    - መደበኛ የፍተሻ ቦታዎችና የተዘጉ መንገዶች ላይ ሲደረስ መደረግ ያለባቸው ነገሮች፤
    - ብልሽ ቢያጋጥም ስለሚወሰዱ ርምጃዎች፤
    - የተፈፅ፣ የደፈጣና የሽምቅ ጥቃት ቢያጋጥም ስለሚደረጉ ተግባራት፤
- ተጓዥ ቡድኑ በፀጥታ ሓይሎች አጀብ የሚንቀሳቀስ ከሆነ፣ የተጓዥ ቡድኑ አዛዥ አጃቢው ሃይል ስለጉዞው እቅድ፣ መንገድ፣ ፍጥነትና ሌሎች ዝርዝሮች ማወቁን ማረጋገጥ አለባቸው፤ እንዲሁም፤
- አደጋ በደረሰ ጊዜ፣ ተጓዥ ቡድኑ ምን ማድረግ እንዳለበት ማወቁን ማረጋገጥ አለባቸው።



ስዕል A1.3
ማነቆ ስፍራዎች ጥቃት ለመጣል ጥሩ ዕድል የሚፈጥሩ ናቸው፤ ባልካንስ
የተመረመአ ፎቶ/ቶማስ ኢነኬ

### ሀ1.3.2 ስለመንገድ ጉዞ ባህርያት

የመንገድ ትራፊክ፣ በተለይ በከተሞች ውስጥ፣ በጣም ወሳኝ ነገር ሊሆን ይችላል። በጉዞው ውስጥ ከኋላ ለሚሆኑ መኪኖች ከፊት እየመሩ ያሉትን ተሽከርካሪዎች ለመከተልና የሁኔታውን የተሟላ ምስል ለማግኘትና ሳይጠበቅ ለሚከሰቱ ነገሮችም ቶሎ ምላሽ ለመስጠት አስቸጋሪ ሊሆንባቸው ይችላል።

የቡድን ጉዞን አነዳድ ለማሻሻልና አስተማማኝ ለማድረግ፥
- በስርዓት ይንዱ፤
- በተሽከርካሪዎች መካከል እንዲኖር በተወሰነው ርቀት መሠረት (ኤሌክትሮ ካውንተር ሜዠር መሠረት)፤
- ቀበቶዎን ይሰሩ።

ከፊት ያለው (መሪው) ተሽከርካሪ በሬዲዮ የሚከተለውን ያሳውቃል፥

- በመገናኛ መንገዶች ላይ የሚሄድበትን አቅጣጫ፤

- ልዩ የሆኑ ነገሮች (እንደ እንቅፋቶች፣ የተጨናነቅ ስፍራዎች፣ ማነቆ ስፍራዎች እና፤
- በአደጋ ጊዜ የመገናኛ ቦታዎች።

የኋለኛው (መጨረሻው) ተሽከርካሪ ደግሞ የሚከተለውን ያስታውቃል፥

- የመገናኛ መንገዱ፣ የተጨናነቀው ቦታ፣ ማነቆው ቦታ መታለፉን፣
- የሌሎች ተሽከርካሪዎች ያለተፈለገ ጣልቃ ገብነት፣ እና
- የቴክኒክ ችግሮች፣ የመኪና ብልሽት።

## አባሪ ሀ2 ለተሽከርካሪ ተጨማሪ መከላከያ ለመስጠት የሚወሰዱ እርምጃዎች

ተራ ተሽከርካሪዎች የጠረ ተሽከርካሪን ፈንጂ እና የተፈፅን ፍንዳታ መቋቋም አይችሉም።ስለዚህ ተመራጩ መንገድ የፈንጂዎች/ያልፈነዱ ጦር መሳሪያዎች/የተፈፅ ጥቃት ከደረሰባቸው ቦታዎች መራቅ ነው። በአጠቃላይ እንዲህ አይነት የሚፈነዱ መሳሪያዎች አሉበት ተብሎ በሚጠረጠሩ መንገዶች ምንም አይነት ጉዞ ሊካሄድ አይገባም።

ይህ መርህ እንዳለ ሆኖ ግን፣ አንዳንዴ የፈንጂ ጥቃት መከላከያ የተገጠመላ መኪና መግዛት ወይም ለመደበኛ ተሽከርካሪዎች ተጨማሪ ከፈንጂ የሚከላከል መሣሪያ ሊገጠምላቸው ይችላል። የዋና ጽህፈት ቤትዎ እና ተገቢው ስልጠና ያላቸው ሠራተኞች ምክር ያስፈልጋል።

ባለሙያዎች እንዲተገበሩ የሚመክሯቸው እርምጃዎች የሚከተሉተን ያጠቃልላል፥

- ሆን ተብሎ የፈንጂ መከላከያ እንዲኖራቸው ተደርገው የተሠሩ ተሽከርካሪዎችን ለምሳሌ ካስፐር እና ዎለፍ ተሽከርካሪዎችን መግዛትን

### ንጥል ጥናት

ከጥቂት ዓመታት በፊት በምስራቅ አንጎላ ሙሉ ተሳፋሪዎችን ጭኖ የነበረ ላንድ ክሩዘር መኪና በፀረ ተሽከርካሪ ፈንጂ በመመታቱ ሰባቱ ሰዎች ሲሞቱ ስድስቱ ደግሞ ቆስለዋል።

የፍንዳታው አደጋ አይቀሬ ቢሆንም ተሳፋሪዎች የመቀመጫ ቀበቶዎችን አጥልቀው ቢሆን ኖሮ ግማሽ ያህሉ የሞቱት ሰዎች ሊተርፉ ይችሉ ነበር ተብሎ ይታመናል። ምክንያቱም አብዛኞቹ የሞቱት በፍንዳታው ምክንያት መኪናዋ ወደአየር ስትወረወርና ስታርፍ ከመኪናው የውስጥ አካል ጋር በመጋጨታቸው ነው።



ሀ2 ለተሽከርካሪ ተጨማሪ መከላከያ ለመስጠት የሚወሰዱ እርምጃዎች

ከግንዛቤ ማስገባት። የተሽከርካሪው v- ቅርጽ ያለው የተሽከርካሪ የስረኛው ክፍል ፍንዳታ ለመከላከል ዋና ነገር ነው።

- በልዩ ሁኔታዎች፣ አካላቸው (ቦዲያቸው) ስስ ለሆኑ መኪናዎች መከላከያ ሊገጠምላቸው ይችላል። ይህ ተጨማሪ መከላከያ የፈንጂ መከላከያ ተገጥሞላቸው የሚሠሩ መኪናዎችን ያህል የመከላከል ብቃት የለውም፤ ሆኖም የፍንዳታን ተጽእኖ ለመቀነስ ይረዳል። የሚገጠሙ የመከላከያ አይነቶችም የሚከተሉት ናች፥
  - የ «ባልስቲክ ብርድልብስ» ወይም ከፖሊከሰርቦኔት ወይም ከናይለን ሴራሚክ የተሰራ የብረት ልባስ መግጠም። ከነዚህ አማረጮች አንዱን ከመምረጥዎ በፊት የእያንዳንዱን ቴክኖሎጂ ጥቅምና ጉዳት ያመዛዝኑ።
  - የሚሽከረከር ብረት ጉማጅ መግጠም። ተጓዦች ከመኪናው ኋላ የሚቀመጡ ከሆነ ከበስተኋላው በኩል የሚሽከረከሩ የብረት ጉማጆት ይገጠማል። ተሳፋሪዎች ከኋላ ወንበሮች ላይ ተቀምጠው ከአራት ቦታ ላይ ከወንበሮቹ ጋር ሊታሰሩ ይገባል። እያንዳነዱ መቀመጫ ቢያንስ የየራሱ ቀበቶ ያለው መሆኑን ይረጋግጡ።
  - ፍንዳታ የሚቋቋም ሽፋን መግጠም። መስኮቶችን ፍንዳታ ሊቋቋም በሚችል ሽፋን መሸፈን በፍንዳታ ጊዜ እንዳይርዱ ያደርጋቸዋል።

- ሁሉንም ተሽከርካሪዎች የእሳት ማጥፊያና የህክምና መስጫ መሳሪያዎች እንዲኖራቸው ያድርጉ።
- በተሽከርካሪዎች ውስጥ የሚጫነውን ነገር በጥብቅ ይከታተሉ። በተሽከርካሪ የተጫኑ አስተማማኝ ያልሆኑ እቃዎች በፈንጂ ጥቃት ጊዜ የጉዳት መጠን ይጨምራሉ። ነዳጅ የያዙ ቆርቆሮዎች በፍጹም በመኪና ውስጥ ሊጫኑ አይገባም።
- በተሽከረካሪዎች ላይ የኤሌክትሮ ካውንተር መለኪያ መግጠም በሬዲዮ እንዲፈነዱ የሚደረጉ ተፈፅን ለመከላል ያስችላል። ሆኖም ይህ የሚሆነው ትክክለኛ የፍሪኩዌንሲ ምርመራ ከተደረገና ባለሙያውም ጥሩ ስልጠና ካለው ነው።



ስዕል A2.1
ከመኪና ውስጥና ውጭ የሚገኝ የባልስቲክ ብርደልብስ ውጤት። በመኪናው የውስጥ ክፍል ምንም አይነት ፍንጣሪ አልተገኘም። አፍጋኒስታን።

ፎቶዎች/የጀርመን ጦር ኃይሎች

## አባሪ ሀ3 5/25 ሜትር ፍተሻ

የተፈፀ አደጋ ስጋት ባለበት ቦታ እየነዱ ከነበረና ማቆም ካለብዎ (ያቆሙበት ምክንያት ምንም ይሁን ምን) የ5/25 ፍተሻ ምድረግ ይኖርብዎታል። ለአፍታ ብቻ የሚቆሙ ከሆነ ተሳፋሪዎች ከተሽከርካሪው በ5 ሜትር ዙሪያውን ከመሳሪያ ማጽዳት አለባቸው። ለረጅም ጊዜ የሚቆሙ ከሆነ በ25 ሜትር ርቀት ዙሪያውን መጽዳት አለበት።

ከመቆምዎ በፊት ያስተውሉ። ቱቦዎችና ጉድጓዶች፣ የቁፋሮ ምልክቶች፣ የተለወጠ የአፈር ቀለም በመሬቱ ላይ መኖራቸውን ይፈልጉ። ውድቅዳቂና ቆሻሻ ነገሮች ብቻ ሳይሆኑ ማንኛውም በግልጽ የሚታይ ነገር ሁሉ አደገኛ ሊሆን ይችላል። ጣሪያዎችን፣ ግድግዳዎችንና መኪናዎችን ይመልከቱ። የመቆሚያ ቦታዎችና በግልጽ ለማየትና መሄጃ መስመሮች በግልጽ ለመታየታቸው ጥንቃቄ ያድርጉ።

ተሽከርካሪውን እንዳቆሙ አይውረዱ፤ ስልታዊ የሆነ ምልከታ (በ360 ዲግሪ ከስር እስከላይ ይቃኙ)። ቱቦዎች፣ ጉድጓዶችና ከላይ የተጠቀሱት ሌሎች ነገሮች ስለመኖራቸው እንደገና ያረጋግጡ። እያንዳንዱ ተሳፋሪ የየድርሻውን አቅጣጫ የመቃኘት ኃላፊነት አለበት።

ከዚህ በኋላ ይውረዱ፣ ግን ሞተር አያጥፉ። በግራ በኩል ያሉ ተሳፋሪዎች በግራ በኩል በቀኝ ያሉ ደግሞ በቀኝ በኩል ይቆጣጠሩ። ሆኖም የሚቆጣጠሩ ቦታ ድንበር ላይ ስልታዊ በሆነ መልክ የጋራ ቁጥጥር የሚደረግበት ይሁን። በሮችን ይዝጉና ተሽከርካሪውን ከጉዳትና ከማንኛውም በቦታው ካለ በግልጽ ከሚታይ አደገኛ ነገር (በተሽከርካሪው ስር ሁሉ) ይጠብቁ። ለመኪናው ቅርብ የሆኑ ቦታዎችን ሁሉ ያስተውሉ። የሚያደርጉት ሁሉ የሚከታተል ሰው (አስፈንጣሪ፣ ተቋሚ) አለ?

ከተጠራጠሩ ሌሎችን ይጠይቁ።

የ5 ሜትር ፍተሸ ይጀምሩ። ከተሽከርካሪው በ5 ሜትር ራዲየስ ፍለጋ ያካሂዱ። በፍለጋው ከአንድ ሰው በላይ ከተሳተፈ ፣ አንዱ ወደሌላው ድንበር ገባ አያሉ ይፈልጉ። መፈለግ የሚኖርባች በግልጽ የሚታዩ የለያዩ አቅጣጫዎችን ነው።







**ስዕል A3.1**
**በቆሙ ቁጥር የ5/25 ሜትር ፍተሸ ያድርጉለ አፍጋኒስታን።**

የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢነኬ





እንደገና የመኪናውን ስር ይመልከቱ። እንደገና የ25 ሜትር ፍተሸ ያካሂዱ።

በቁጥቋጦዎች ዙሪያ ያሂዱና አካባቢውን ከሌሎች ቦዎች ይለዩት። ካስፈለገ ፍተሻ ያካሂዱበት። የደፈጣ ጥቃት ምልከቶችን ይፈልጉ። አጠራጣሪ ነገሮችን አይቅረቡ። ማጉሊያ መነጸሮችንና ዲጂታል ካሜራዎችን ተጠቅመው ነገሮችን ለማጣራት ይሞክሩ።

## አባሪ ሀ4 ሌሎች የስጋት ምንጮች

### ሀ4.1 አገልግሎቱን የጨረሰ ዩራኒየም

አገልግሎቱን የጨረሰ ዩራኒየም በጣም ጥቅጥቅ ያለ (ከፍተኛ ደንሲቲ ያለው) ነው፤ ጥቅጥቅታው 19,050 ኪግ/ሜ³ ሆኖ የ 11.340ኪግ/ሜ3 ጥቅጥቅታ ካለው እርሳስ (ሊድ) 1.67 ጊዜ ያህል ይበልጣል። ከ 2% ሞሊብዴኑም ወይም 0.75% ቲታኒየም ጋር ሲጣመርና የተለየ ሙቀት ሲሰጠው እንደ ተንግስተን ካርባይድ ጠንካራ ይሆናል። አገልግሎቱን የጨረሰ ዩራኒየም ርካሽ ነው። ከተመሳሳይ ተንግስተን በ20 በመቶ ያነሰ ዋጋ አለው። አገልግሎቱን የጨረሰ ዩራኒየም መርዛማ ነው። በረጅም ጊዜ ሲቆይ የከፋ የጤና ጉዳት አለው።

እንደሌሎቹ የዩራኒየም ማበልጸጊያ ተረፈምርቶች ሁሉ አገልግሎቱን የጨረሰ ዩራኒየም ተንግስተንን ጨምሮ ከፍተኛ ጥቅጥቅታ ካላቸው ከሌሎች መሳሪያዎች ሁሉ በ1960ዎቹ ዋጋው ያነሰ ነበር። ከሱ ቀጥሎ ተፈላጊ የነበረው ተንግስተን ከቻይና ይገኝ ነበር። ሆኖም አገልግሎቱን የጨረሰ ዩራኒየም ክምችት ከ500,000 ቶን በላይ ስለነበር እሱን ከማከማቸት ይልቅ መጠቀሙ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ነበረው። ስለዚህም ከ1970ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ ዩናይትድ ስቴትስ፣ የቀድሞዋ ሲቬት ህብረት፣ እንግሊዝ እና ፈረንሳይ አገልግሎቱን የጨረሰ ዩራኒየም ክምችታቸውን ለኪነቲክ ሃይል መሰርሰሪያነት መጠቀም ጀመሩ።

በተጨማሪም አገልግሎቱን የጨሰ ዩራኒየም ታንኮችና ሌሎች ወታደራዊ ተሽከርካሪዎችን ለማልበስ፣ ለአውሮፕላን ስቴብላይዘር መስሪያነት፣ እና ለመወዳደሪያ ጀልባዎች መስሪያ ይገለግላል።

እንደ ብረት ለበስ ተሽከርካሪ ባለ ጠንካራ የሆነ ነገር ላይ ካረፈ፣ የሹል ዓፉ አፍንጫ ይሰነጠቅና ስለት ሆኖ ይቀመጣል። ሲያርፍ የሚፈጥረው ግጭትና ተከትሎ የሚለቀው የሙቀት ኃይል ፐሮጀክታይሉ እንደ አቧራ እንዲበታተንና በፓይሮፎሪክ ባህርይው ምክንያት አየር ላይ ሲሆን እንዲነድ ያደርገዋል። አገልግሎቱን የጨረሰ ዩራኒየም መሠርሠሪያ የብረት ለበስ ተሽከርካሪን የውስጥ አካል ዘልቆ ሲገባ እሳት ይፈጥርና ብዙ ጊዜ ጥይቶችንና ነዳጅን በመለኮስ ሰዎቹን ገድሎ ተሽከርካሪውንም ሊያፈነዳው ይችላል።

የተተኮሰ አገልግሎቱን የጨረሰ ዩራኒየም መሰርሰሪያ በልዩ የሙቀት ኃይል አማካኝነት የተዘጋጀ (ሲነትርድ ሜታል) ስለሆነ፣ ፐሮጅቸተይሉ አቧራ ሆኖ እስከሚያልቅ ድረስ አቧራ ያወጣል። ይህም ማንኛውንም ለማስታወሻ ተብሎ የተቀመጠ አገልግሎቱን ከጨረሰ ዩራኒየም የተመረተ መሰሪያን ሁሉ ለጤና በጣም አደኛ ያደርገዋል።

አንዳንድ ጊዜ አገልግሎቱን የጨረሰ ዩራኒየም ቀለሙ ጥቁር ወይም አረንጓዴ የሆነ ቆሻሻ መሳይ የዝቃጭ አቧራ አለው። አቧራው ሳይታይ ቢቀር ዩራኒየሙ የሚቦን ዝቃጭ የለውም ብለው ግን እንዳያስቡ።

አገልግሎቱን የጨረሰ ዩራኒየም ወደውስጥ ሊተነፈስ፣ ሊዋጥ ወይም በተቆረጠና በተጫረ አካላችን አማካኝነት ወደሰውነታችን ውስጥ ሊገባ ይችላል። አገልግሎቱን የጨረሰ ዩራኒየም ከሰውነታችን ውጭ እስከሆነ ድረስ፣ ባለሙያዎች ጉዳቱ የሚያሳስብ እንዳልሆነ ይቆጥሩታል።

አገልግሎቱን ከጨረሰ ዩራኒየም አደጋ ከመጋለጥ ራስን ለመከላከል ከሚያስችሉ ድንጋጌዎች መካከል የሚከተሉት ይጠቃለላሉ፥

- ጉዳት በደረሰበት ወታደራዊ ቁሳቁስ ውስጥ አይግቡ ወይም አይነጠልጠሉ፤
- የወታደራዊ ዕቀዎችን ውድቅዳቂ፣ የጥይት ማሸጊያዎችን፣ ያልፈነዱ መሣሪያዎችን የተተው ወይም የተጎዱ ወታደራዊ ተሽከርካሪዎችን አይንኩ ወይም አይቅረቡ፤
- የጦርነት ማስታወሻ መሳሪያዎችን አይሰብስቡ።

## ንጥል ጥናት

**እ.ኤ.አ. በ1991 ዓ.ም. በተካሄደው የገልፍ ጦርነት አገልግሎቱን የጨረሰ ዩራኒየም በብዛት ጥቅም ላይ ውሎ ነበር። ወደ አንድ ሚሊዮን ከሚደርሱ የዩራኒየም የተሠሩ ጥይቶች ተተኩሰዋል። ይህም መጠናቸው ወደ340 ቶን የሚያደርስ ነው። በባልካንስ በ1980ዎቹ የተተኮሱት አገልገሎት የጨረሱ ዩረኒየሞች 11 ቶን ነበሩ።**

**በቅርቡ በተካሄደው የገልፍ ጦርነት በግምት 75 ቶን የሚደርሱ አገልግሎቱን በጨረሰ ዩራኒየም የተሠሩ የጦር መሣሪያዎች በዩናይትድ ስቴትስ ጦር ሠራዊት አገልግሎት ላይ ውለዋል።**

ክርስቲያን ሳይንስ፣
www.csmonitor.Com/2003/0515/

**ይህ ቢሆንም ግን አገልግሎቱን በጨረሰ ዩራኒየም የሚደርሱ ዘላቂ የጤና እክሎች እስካሁን ውስን ናቸው፤ አገልግሎቱን የጨረሰ ዩራኒየም የሚያስከትለው የጤና ችግርም እንዲሁ በከፍተኛ ደረጃ እያወዛገበ ነው።**





አገልግሎቱን ከጨረሰ ዩራኒየም ጋር ከተነካኩ፥

- አፍዎን ይሸፍኑ፤
- ቦታውን ለቀው ይወጡ፤
- እጅዎንና ፊትዎን በሳሙና ይታጠቡ፤
- ልብስዎን ይጠቡ።

ከዚህ በተጨማሪ የበለጠ ሁሉን አቀፍ መረጃ በሚከተለው የኢንተርኔት አድራሻ ማግኘት ይቻላል፥ en.wikipedia.org/wiki/Depleted_uranium
በአሁኑ ጊዜ በመቶዎች የሚቆጠሩ ማጣቀሻዎች ተካትተዋል።



ስዕል A4.1
በተተውና በተደመሰሱ ተሽከርካሪዎች አማካኝነት ከሚደርሱ ጉዳቶች አንዱ አገልግሎቱን በጨረሰ ዩራኒየም የሚደርስ ብክለት ነው። አፍጋኒስታን።
የተመፈመአ ፎቶ/ቶማስ ኢነከ

## ሀ4.2 ባዮሎጂካዊና ኬሚካላዊ መሣሪያዎች

ባዮሎጂካዊ መሳሪያዎች ሰዎችን ሊያሳምሙ ወይም ሊገድሉ የሚችሉ ጀርሞችንና ሌሎችን ባዮሎጂካዊ ነገሮችን እንዲበትኑ ተደርገው የተሠሩ ናቸው። ብዙ ባዮሎጂካዊ አጥቂ-ንጥረነገሮች ሰዎችን ያሳምሙ ዘንድ በትንፋሽ የሚሳቡ፣ በተቆረጠ ቆዳ የሚገቡ ወይም የሚበሉ መሆን አለባቸው። አንዳንድ እንደ ፈንጣጣ ቫይረስ ያሉ ባዮሎጂካዊ መሣሪያዎች በጣም ተላላፊ ስለሆኑ እርስዎ ከተጋለጡ ወደሌሎችም ያስተላልፋሉ።

ኬሚካላዊ መሣሪያዎች ደግሞ ሰዎች ወደውስጥ ሲተነፍሷቸው፣ በቆዳቸው ሲነኳቸው ወይም በአካባቢው ሲገኙ ሊመርዙ የሚችሉ መርዛማ ጋዞችን፣ ፈሳሾችን ወይም ጠጣር ነገሮችን የሚያመነጩ ናቸው።ብዙ ኬሚካላዊ መሳሪያዎች ቆዳን ያቃጥላሉ።

ኬሚካላዊና ባዮሎጂያዊ መሣሪያዎች ብዙ ጊዜ የሚወረወሩት በሚሳይል፣ በሮኬት፣ በአየር ቦምብ፣ በአርቲለር ጥይት እና ከአየር በሚረጩ ታንኮች አማካኝነት ነው። እንዲሁም የተተውና የተደመሠሱ የባዮሎጂካዊና የኬሚካላዊ መሳሪያ ማምረቻዎች ተመሣሳይ የአደጋ ስጋት ሊያመጡ ይችላሉ።

የኬሚካላዊና ባዮሎጂካዊ መሣሪያዎች አጥቂ-ንጥረ ነገር ውዲያውኑ የሚሰራጭ ሲሆን፤ የተተው መሳሪያዎች አሠራር ግን ለረጅም ጊዜ አደገኝነታቸውን ይዞ ሊቆይ ይችላል። ተመራጩ ምክር ከመሣሪያዎች መጋዘን፣ ከተተው የሚፈነዱ መሣሪያዎች፣ ከአጠራጣሪ ፈሳሾች እና መያዣዎች መራቅ ነው።

የኬሚካላዊና የባዮሎጂካዊ መሣሪያዎች ስጋት የመኖሩ ምልክቶች፦

- ከአየር ላይ የሚመነጩ ጋዞች፤
- ያልተለመዱ ፈሳሾችና መያዣዎች፤
- የማይታወቅ አይነት ሽታ፤
- የብዙ ሰዎች አይን ማልቀስ፣ መብረክረክ፣ ጭንቅ ጭንቅ ማለት፣ ለመተንፈስ መቸገር፤ ቅልጥፍና ማጣት፤
- ብዙ ሰው መታመም ወይም የወፎች ሞት፣ ትንንሽ እንስሳትና አሳዎችም እንዲሁ ለጥርጣሪ ምንጭ ናቸው። እንዲሁም፤
- የእርስዎ ወይም የጓደኛዎ በድንገት መታመም።

በአየር ላይ በቅርብ የሚታይ እንግዳና አጠራጣሪ ነገር መታየቱን ካወቁ፦

- የኬሚካል፣ ባዮሎጂካል፣ ራዲዮሎጂባለና ኑክሌር መከላከያ ጭንብል (ሲ.ቢ.አር.ኤን ጭንብል) ይጠቀሙ፤
- በፍጥነት ንጹህ አየር ያግኙ፤
- መሣሪያው ያረፈበትንና ኬሚካሉ የሚመጣበትን ቦታ ቶሎ ለማወቅ ይሞክሩ፤
- ከቦታው ለመራቅ አፋጣኝ ርምጃ ይውሰዱ፤ ከማነኛውም አደገኛ መሳሪያ ርቀው ይቆዩ፤
- አየርን ማጣራት በሚችሉ፣ ግን መተንፈስ በሚያስችሉ መሸፈኛዎች አፍዎንና አፍንጫዎን ይሸፍኑ፤
- መሳሪያው እርስዎ ባሉበት ህንጻ ውስጥ ከሆነ፣ ከተቻለ በተበከለው ቦታ ሳይልፉ ህንጻውን ለቀው ለመውጣት ይሞክሩ፤
- ከህንጻው መውጣት ወይም የኬሚካል ጥቃት ምልክት ባዩበት ቦታ ሳያልፉ ንጹህ አየር ማግኘት ካልቻሉ፣ በተጫለ መጠን ለመራቅ መሞከር የተሻለ ሊሆን ይችላል፤



ሀ4 ሌሎች የስጋት ምንጮች
ሀ4.2 ባዮሎጂካዊና ኬሚካላዊ መሣሪያዎች

- በሳሙናና በውሃ ይታጠቡ፤
- የሚመለከታቸውን አካላት ለማግኘት ይሞክሩ (ለምሳሌ፤ የፈንጂ መከላከል አጀንሲዎች፣የተባበሩት መንግስታት የፀጥታ ሃይሎች፣ የሰላም ማስከበር ታክቲካል ማዘጋጃ ማዕከላት- ታዛቢ- ወይም አሰልጣኝ- ተልዕኮ ተጠባባቂዎች)።

አይንዎ የሚያለቅስ፣ ቆዳዎ የሚቆጣ፣ ትንፋሽዎ የሚያስቸግርዎ ከሆነ፣ ለኬሚካል መሳሪያ ጥቃት ተጋልጠው ይሆናል። ለንዲህ አይነት መሳሪያ ተጋልጫለሁ ብለው የሚያስቡ ከሆነ፦


- አይጠጡ፣ አይመገቡ ወይም አያጭሱ፤
- ወዲያውኑ ይታጠቡ፤
- ቧንቧ፣ ፋውንቴይን፣ ወይም ሌላ የውሃ መገኛ ይፈልጉና ከተቻለ በሳሙና ይታጠቡ ኬሚካሉ ቆዳዎን እንዳይነካው ተጠንቅቀው፤
- የድንገተኛ አደጋ የህክምና እርዳታ ያግኙ።

ለባዮሎጂካል መሳሪያ ጥቃት ተጋልጫለሁ ብለው ካሰቡ፦

- አይጠጡ ወይም አይመገቡ፤
- የጀርሞችን መስፋፋት ለመከላከል ንጽህናዎን ይጠብቁ፤
- እጅዎን በተደጋጋሚ በውሃና በሳሙና ይታጠቡ፤
- ምግብና መገልገያ መሳሪያዎችን ከሌላ ጋር አይጋሩ
- ሲስሉና ሲያስነጥሱ አፍዎንና አፍንጫዎን ይሸፍኑ፤
- ጤና ነክ መረጃዎችን ለሌሎች ሰዎች ያካፍሉ፣ በተለይም ተጨባጭ ሁኔታውን ለመረዳትና ምን ማድረግ እንዳለባቸው ድጋፍ የሚፈልጉት፤
- የህክምና ምክር ያግኙ።

ለተጨማሪ ምክር en.wikipedia.org/wiki/CBRN_defense
የሚለውን የኢንተርኔት አድራሻ ይጎብኙ።


## አባሪ ሀ5 ከአደገኛ ቦታ የማምለጫ ርቀት መመሪያ








## አባሪ ሀ6 እነ ዘጠኛ



# አባሪ ሀ7 መፍትሔ ቃላት

ይህ መፍትሔ ቃላት በዚህ መጽሀፍ ውስጥ ጥቅም ላይ ለዋሉ ሙያዊ ቃላት ቀላል ማብራሪያ (ገለጻ) ይሰጣል። አላማው አንባቢውን ለመርዳት እንጂ እ.ኤ.አ. በ1980 ዓ.ም በተደረገው የተወሰኑ መሳሪያዎች አጠቃቀም ስምምነትና የዚህ ስምመነት አባሪ በሆነው ፕሮቶኮል፣ ወይም እ.ኤ.አ. በ1997 በተደረገው የፀረ-ሰው ፈንጂዎችንና ሌሎችን አውዳሚ መሳሪያዎች ከመጠቀም፣ ከማከማቸት፣ ከማምረት እና ከማዛወር በሚከለክለው ስምምነት (በተለምዶ የፀረ-ሰው ፈንጂ ማዕቀብ ስምምነት ወይም የኦታዋ ስምምነት ተበሎ በሚታወቀው) ውስጥ የሚገኙትን ቃላት ህጋዊና ሙያዊ ገለጻ ለመተካት ወይም ለመለወጥ አይደለም።

**የተተወ ተፈዕ (ቅሪት ረፈዕ ተብሎም ይታወቃል)**

የተተወ ተራየሚፈነዳ እቃ ደረጃውን ጠብቆ (በመደበኛነት ያልተመረተ) እና ለተፈለገው አገልግሎት ያልዋለና ማንም የሚቆጣጠረው የኔ ነው ባይ አካል የሌለው መሳሪያ ነው። የሚፈነዱ ንጥረነገሮች፣ ፊዩዞች እና ሌሎች ክፍሎች በቤት ውስጥ የተሰሩ ስለሚሆኑ የተፈዕ መሳሪያዎች በጣም አደገኛና ጥብቅ አይደሉም። በማንኛውም አይነት ንክኪ ወይም በአካባቢያቸው መለዋወጥ ብቻ ሊገነቡ ይችላሉ። ተፈዕ መሳሪያዎች የተተው የጦር መሳሪያዎችንና የጥይት ማጠራቀሚያ ቦታዎችን ለመከላከልም ያገለገላሉ።

**የተተው የሚፈነዱ መሳሪያዎች**

የተተው መሳሪያዎች የሚባሉት አገልግሎት ያልሰጡ ግን የሚቆጣጠራቸው የኔ ነው ባይ የሌላቸው የሚፈነዱ መሳሪያዎች ናቸው። እነሱም የሞርታር ጥይቶችን፣ ግሪኔዶችን፣ ቦምቦችን፣ ሮኬቶችን፣ ጥይቶችን፣ የአርቲለሪ ጥይቶችን ወዘተ. ያጠቃልላሉ። እንዳንዴ የተተው መሳሪያዎች በውጊያ ጊዜ ተመልሶ ለመውሰድ ተብለው የተተውና የጠፉ ትንንሽ የጥይት ማጠራቀሚያዎችንም ሊወክሉ ይችላሉ።



**ስዕል A6.1**
**ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ሰባ ዓመት በኋላ ያልጸዳ የፈንጂ ስፍራ፤ ጀርመን**

ፎቶ በማርከስ ሽዌይስ





**ፀረ-ሰው ፈንጂ**

አንድ ወይም ብዙ ሰዎችን ለመጉዳት ወይም ለመግደል የሚሠራ ፈንጂ ነው። ፀረ-ሰው ፍንጂዎች ብዙ ጊዜ የሚፈነዱት ሰው ሲቆምባቸው ወይም ማስፈንጠሪያ ሽቧቸው ሲነካ ነው። ሆኖም በጊዜ ሂደት ወይም በቁጥጥር ስር በተደረገ ዘዴ ሊፈነዱ ይችላሉ። ፀረ-ሰው ፈንጂዎች እንዳይነሱ በሚያደርግ ዘዴ ሊጠመዱ ይችላሉ፤ እንዲሁም ከፀረ-ተሽከርካሪ ፈንጂ ጋር በአንድ ላይ ሊቀበሩ ይችላሉ።

**ፀረ-ተሽከርካሪ ፈንጂ**

ብዙ ጊዜ ፀረ-ታንክ ፈንጂ ተብለው የሚጠሩት ፀረ-ተሽከርካሪ ፈንጂዎች ታንኮችን ጨምሮ ተሽከርካሪዎችን ለማሰናከልና ለመደምሰስ የተሠሩ ናቸው። እንደ ፀረ-ሰው ፍንጂዎች ሁሉ ፀረ-ተሽከርካሪ ፈንጂዎች በግፊት (በጣም ከፍተኛ ክብደት ቢፈልጉም) ወይም በርቀት መቆጣጠሪያአማካኝነት፣ እንዲሁም በማግኔት ኃይል ተጽእኖ ወይም ግድል ብረት (ቀጥ ያለ ማስፈንጠሪያ ሽቦ መሳይ ነገር) ንቅናቄ ሊፈነዱ ይችላሉ። ፀረ-ተሽከርካሪ ፈንጂዎች እንዳይነሱ በሚያደርግ ዘዴ ሊጠመዱ ይችላሉ፤ እንዲሁም ከፀረ-ሰው ፈንጂ ጋር በአንድ ላይ ሊቀበሩ ይችላሉ።

## ስውር ወጥመድ

በተለምዶ አደጋ የማያደርስ እቃ ሲነካ ወይም አደጋ የማያስከትል ድርጊት ለምሳሌ በር መክፈት፣ ቴሌቪዥን መክፈት የመሰለ ድርጊትሲፈጸም አደጋ እንዲያደርስ ተደርጎ የተጠመደ የሚፈነዳ ወይም የማይፈነዳ መሳሪያ ነው። የሚፈነዱ ስውር ወጥመዶች በሙሉ ተራ የሚፈነዱ ዕቃዎች (ተፈዕ) ተብለው ይጠራሉ።

## ከባቢ ፈንጂ

በማስፈንጠሪያ ሽቦ አማካኝነት የሚፈነዳ ፀረ-ሰው ፈንጂ ሲሆን የሚፈነዳው በተወሰነለት ከፍታ በአየር ላይ ሆኖ ወደ ሁሉም አቅጣጫ የሚፈናጠር ነው።

### የሚፈነዱ የጦርነት ቅሪቶች

ማንኛውም ከውጊያ ተርፎ የቀረና የመፈንዳት አቅም ያለው መሳሪያ ሁሉ ነው። ይህም ያልፈነዱ መሳሪያዎችን፣ የተተው መሳሪያዎችን፣ ስውር ወጥመዶችን፣ ተፈፅ መሳሪያዎችን እና በአንዳንድ አጋጣሚዎች ደግሞ የተተውና የተደመሰሱ ወታደራዊ ተሽከርካሪዎችንና ቁሳቁሶችን ያጠቃልላል። አለማቀፋዊ በሆነ አነጋገር፣ የሚፈነዱ የጦርነት ቅሪቶች (ፈጦቅ) ፈንጂዎችን አያጠቃልሉም፤ ፈንጂዎችና የጦርነት ቅሪቶች በተለያዩ አለማቀፋዊ ጉባኤዎች አማካኝነት ስምምነት ስለተደረገባቸው፡ ፀረ-ሰው ፈንጂ ማዕቀብ ስምመነት እና የተወሰኑ ጦር መሳሪያዎች አጠቃቀም ስምምነት (ፕሮቶኮል 5)።

### ፊዩዝ

ፊዩዝ የተተኳሽ መሳሪያ አካል ስትሆን በምንገለገልበት ጊዜ እንዳለ እንዲቀመጥ ሲፈለግ ደግሞ እንዲፈነዳ ለማድረግ የምትጠቅም ናት።

### ተራ የሚፈነዳ ዕቃ

ተራ የሚፈነዳ መሣሪያ (ተፈዕ) የሚባለው ደረጃውን ያልጠበቀ ዕቃ ሆኖ ብዙ ጊዜ በቅርብ ከሚገኙ ነገሮች የሚሠራ ነው። የሚያካትተውም የሚፈነዱ ነገሮችን፣ የኪሚካላዊ፣ ባዮሎጂያዊ፣ራዲዩሎጂያዊና ኑክሌራዊ ውህዶች ሆነው የመደምሰስ፣ ጉዳት የማድረስ ወይም የመርዛማነት ባህርይ ያላቸውን ሁሉ ነው። ከፍተኛ የጥራት ደረጃ፣ በተከታታይ የሚመረቱ መሆናቸው፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር መጠቀማቸው እና መሠል ለውጦች የተፈዕ መሳሪያዎችን አደገኛነት የከፋ አድርገውታል።

### ፈንጂ መከላከል

ፈንጂዎች፣ የሚፈነዱ የጦርነት ቅሪቶች እና ተራ የሚፈነዱ መሳሪያዎች ቅሪት በሲቪል ነዋሪቆች ላይ የሚያደርሱትን ስጋት ለመቀነስ የሚሰሩ ተግባራት ናቸው። ፈንጂ መከላከል ብዙ ጊዜ ተደጋጋፊ የሆኑ አምስት ተግባራትን ያጠቃልላል፥





- ጉዳትን መቀነስና ግንዛቤን መፍጠር፤
- ማንንም ከማንም ሳይለዩ ጉዳት የሚያደርሱ ፈንዎችንና መሳሪያዎች ላይ ማዕቀብ ለመጣል የማሳመን ስራ፤
- የፈንጂ፣ ፈጦው እና ተፈዕ ተጎጂዎችን መርዳት፤
- ፈንጂ ማጽዳትና የሚፈነዳ የጦር መሳሪያን ማስወገድ፤
- የተከማቹ ፈንጂዎችን ማውደም።

ፈንጂ መከላከል ተፈዕ መሳሪያዎችን የማስወገድና የማውደም ተግባርን አያጠቃልልም። ብዙ ጊዜ የእነዚህ መሳሪያዎች ስጋት መፍትሔ የሚፈለግለት እንደ ፖሊስ ባሉ በፀጥታ ኃይሎች ነው።

### የፈንጂ መከላከል ማዕከል

በአንድ አገር ውስጥ የፈንጂ መከላከልን ስራ የሚያስተባብርና የሚቆጣጠር ማዕከል ነው። እነዚህን ማዓከላት ብዙ ጊዜ መንግስታት ወይም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ይመሯቸዋል።

### ፈንጂን ማመልከት

የተደራጀ ፈንጂ የተቀበረባቸውን ቦታዎች የማመልከት ተግባር። ፈንጂ ስለመኖሩ ሰዎችን ለማስጠንቀቅ መደበኛ፣ በቀላሉ የሚለዩ የማስጠንቀቂያ ምልክቶች ፈንጂ ባለባቸው ቦታዎች ዙሪያ ይቀመጣሉ።

### ቅሪት ተፈዕ

የተተወ ተፈዕን ይመልከቱ።

### ዝንብል ብረት

በፈንጂ የላይኛው የፊዩዝ ክፍል ላይ የሚያያዝና ቋሚ ወይም ችካል ብረት ነው። በዝንብል ብረት ላይ የሚያርፍ ግፊት ፈንጁን ያፈነዳዋል።

### ማስፈንጠሪያ ሽቦ

ፀረ-ሰው ፍንጂን ወይም ስውር ወጥመድን ለማፈንዳት የሚውል ቀጭን የማያንጸባርቅ ወይም ቀለም የተቀባ ሽቦ ነው። ማስፈንጠሪ ሽቦ ብዙ ጊዜ ከመሬት ላይ ዝቅ ብሎ ነው የሚቀመጠው። የሚያልፍ ሰው ሲቆምበት የሚፈነዳውን ነገር ያቀጣጥላል።

### ያልፈነዳ መሳሪያ

የሚፈነዱ መሳሪያዎች ሆነው ገና ሳይፈነዱ የቀሩ ናቸው። ያልፈነዳ መሳሪያ የተተኮሰ፣ የወደቀ፣ ወይም የተወነጨፈ ነገር ግን እንደታሰበው ሳይፈነዳ የቀረ ነው።





## አባሪ ሀ8 የሚዘወተሩ ምኅጻረ ቃላት

| | |
|---|---|
| ተመ | የተተወ መሳሪያ |
| ተመድ | የተባበሩት መንግስታት ድርጅት |
| ተመፈመአ | የተባበሩት መንግስታት የፈንጂ መከላከል አገልግሎት |
| ተፈዕ | ተራ የሚፈነዱ ዕቃዎች |
| እ.ኤ.አ | እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር |
| ደመት | ደም ዝውውር፣ መተንፈሻ፣ ትንፋሽ |
| ፈጦቅ | የሚፈነዱ የጦርነት ቅሪቶች |

## አባሪ ሀ9 የተጨማሪ መረጃ ምንጮች

አጠቃላይ መረጃ ማግኘት፥

www.mineaction.org/unmas
www.gichd.org
www.peaceopstraining.org
www.jmu.edu/cisr/index.shtml

ቴክኒካዊ ምክር ለማግኘት፥

www.un.org/disarmament/un-saferguard/guide-lines
www.mineactionstandards.org

ስለጥይት ልዩ መረጃ ለማግኘት፥

www.cat-uxo.com
www.rwd-mb3.de
www.lexpev.nl

እንዲሁም ሌሎችን ምንጮች መጠቀም ይቻላል...



## በአደጋ ጊዜ የሚያገለግሉ አድራሻዎች

ይህን ቦታ በአደጋ ጊዜ የሚሆኑ የሚከተሉትን ተቋማት አድራሻዎችን ዝርዝር ማለትም ስልክ ቁጥር እና/ወይም የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ለመጻፍ ይጠቀሙበት፥

የፀጥታ መኮንኖች፣ የህክምና ማዕከላት፣ የሬዲዮ ክፍል ኦፕሬተሮች፣ የፈንጂ መከላከል ማዕከላት፣ ዋና መስሪያ ቤቶች፣ ወዘተ።

# ማስታወሻዎች



# ማስታወሻዎች

UNMAS


የተባበሩት መንግስታት
የተባበሩት መንግስታት የፈንጂ
መከላከል አገልግሎት (የተመፈመአ)
ኒውዮርክ, NY 10017 ዩ.ኤስ.ኤ

ኢሜይል፥ MINEACTION@UN.ORG
ደረ ገጽ፥ WWW.MINEACTION.ORG